# መጽሐፈ ኪዳን

## ኪዳን ዘ፫ቱ ጊዜያት
## ትምህርተ ኅቡዓት

የመንበረ ጸባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል
የድርሰት ክፍል ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፹፫ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን. ነ. ዘኢትዮጵያ በ፴፩ኛው ዘመነ መንግሥት ይህ መጽሐፍ ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት ለ፪ኛ ጊዜ ታተመ ።

## መ ቅ ድ ም ።

ይኸ መጽሐፈ ኪዳን የተባለው የጸሎት መጽሐፍ ከትልቁ መጽሐፈ ኪዳን ተወጣጥቶ ለጸሎት ለትምህርት አገልግሎት ይውል ዘንድ በቤተ ክርስቲያናችን የተወሰነ ነው ።

ከዚህ ከ፪ቱ ክፍሎችም ፩ኛው የ፫፡ ጊዜያት ኪዳን ሲሆን ፤ በቤተ ክርስቲያናችን በሌሊት ፤ በነግህ ፤ በሠርክ እንዲደርስ ከመመደቡ ሌላ ቄስ ሁኖ ይኸን በየዕለቱ የማይጸልይ አይገኝም ። ፪ኛው ክፍል ደግሞ ትምህርተ ኅቡዓት የሚባለው ሲሆን ፤ ማንኛውም ክርስቲያን በየዕለቱ የሚጸልየው ፤ በተለይ በምሥጢረ ቍርባን ጊዜ የሚነበብ ፤ በሰሙነ ሕማማት ጊዜ የሚተረጐም ፤ በዘመነ ስብከት ግን በዜማ የሚደርስ ጸሎት ነው ። ፪ቱም ዓይነት ጸሎቶች ለምእመናን ጠቃሚ መሆናቸውን በማመን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለየራሳቸው አሳትመዋቸው ነበር ፤ ከዘመኑ ብዛትና ከመጻሕፍቱም ተፈላጊነት የተነሣ ለዓይነት እንኳን ተፈልገው የማይገኙ ሁነዋል ። አሁንም ምእመናኑ በጥብቅ የሚፈልጓቸው ስለሆነ ለጸሎትም ፤ ለትርጕም ሥራ ረድቶ ፍላጎታቸውን እንዲያረካ ለአያያዝም እንዲመች በማለት ሁለቱንም በ፩ ጥራዝ አድርገን አሳትመነዋል ።

በትርጕሙ ሥራ ላይ ከቀድሞው ምንም ያሻሻል ነው ፤ የለወጥነው ነገር የለም ፤ ያኑ ጥንት የታተመውን መልሰን ማሳተም ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ምእመናን በጸሎት በትምህርት እንዲጠቀሙበት እምነታችን ፍጹም ነው ።

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
የድርሰት ክፍል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፩ ኪዳን ዘ፫ቱ ጊዜያት

## ምዕራፍ ፩ ኪዳን ዘሌሊት ።

ኪዳን ዘነግህ ይኸን ኪዳን መላእክት ተናግረውታል ቢሉ ፤ ለይኩን ብርሃን ባለ ጊዜ ነውና ነግህ የተመቸ ። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ተናግረውታል ቢሉ ፤ ሞትከኑ መንሥኢሆሙ ለምውታን ፤ ደከምከኑ መጽንዒሆሙ ለድኩማን እያሉ ሲገንዙት ወአንበሰበሰ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ እንዲል ዓይኖቹን ግልጽልጽ አድርጎ ለምን ሞትከኑ መንሥኢሆሙ ለምውታን ደከምከኑ መጽንዒሆሙ ለድኩማን እያላችሁ ትገንዙኛላችሁ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ እያላችሁ ገንዙኝ እንጂ ብሏቸው በዚህ ጊዜ ተናግረውታል ። አንድም ደከምከኑ ሞትከኑ ሳይሉ ሲገንዙት ወአንበሰበሰ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ እንዲል ዓይኖቹን ግልጽልጽ አድርጎ እንደሩቅ ብእሲ ፤ እንዲያውን ዝም ብላችሁ ትገንዙኛላችሁ ፤ ቅዱስ እግዚአብሔር ፤ ቅዱስ ኃያል ፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እያላችሁ ገንዙኝ እንጂ ብሏቸው በዚህ ጊዜ ተናግረውታል ። አንድም ዘመነ ወንጌልን ነግህ እያለው ይሄዳልና ። አንድም ቀሳውስት በንቅወተ ዶርሆ ይጸልዩበታልና አያይ፡ የሚነጋ ስለ ሆነ ነግህ አለው ። እስመ ንቅወተ ዶርሆ ይሰብክ ምጽአተ ብርሃን እንዲል ። አንድም በቁሙ በነግህ ይጸልዩ

www.ethiopianorthodox.org

በታልና ነግሀ ባለው አብነት በናቱ በመጽሐፈ ኪዳን ኅሀተ ሙቀተ ይለዋል ።

፩/ ቅዱስ እግዚአብሔር ፤

፩/ ልዩ ገዥ ፤ ጌትነቱ እንደ ነገሥታት በጉልበት ፤ እንደ ካህናት በሀብት ፤ እንደ ጣዖት በሐሰት አይደለምና ልዩ አለ ።

፪/ ቅዱስ ኃያል ፤

፪/ ልዩ ኃያል ። ሐተታ ኃይል መልአካዊ ፥ ኃይል ሥጋዊ ፥ ኃይል መንፈሳዊ አለ ፤ ኃይል መልአካዊ ፥ ወነሥአ አሐዱ መልአክ ኃያል ወጽኑዕ ዓቢየ ዕብነ ከመ እንተ ማኅረፅ ወወገረ ውስተ ባሕር ወይቤ ከመዝ ትትገደፍ ባቢሎን ዓባይ ሀገር ያለው ነው ። ኃይል ሥጋዊ እንደ ጌዴዎን ፤ እንደ ባርቅ ፤ እንደ ዮፍታሔ ፤ እንደ ሶምሶን ነው ፤ ኃይል መንፈሳዊ ፥ እንደ አብርሃም ነው ፤ ወይቤ ዝኩ አብርሃም ኢሞዓኒ ሰይፈ ጸላኢ እንዲል ።

፫/ ቅዱስ ሕያው ፤

፫/ ልዩ ሕያው ፤ ሐተታ ። ሕይወት እንስሳዊ ፥ ሕይወት ሰብአዊ ፥ ሕይወት መልአካዊ አለ ። ሕይወት እንስሳዊ በተፈጥሮ ይሰጣል ፤ በሞት ይነሣል ፤ እንደ ተነሣ ይቀራል ። ሕይወት ሰብአዊ በተፈጥሮ ይሰጣል ፤ በሞት ይነሣል ፤ በትንሣኤ ዘጉባኤ ይመለሳል ። ሕይወት መልአካዊ በተፈጥሮ ይሰጣል ፤ እንደ ተሰጠ ይቀራል አይነሣም ። አንድም ፤ ቅዱስ ፤ ንጹሕ ፤ ጽኑዕ ፤ ክቡር ፤ ልዩ ሲል ነው ። ሐተታ ንጹሕ አለው ፤ ሰውን ንጹሕ ቢሉት



ጽድቅም ፤ ኃጢአትም ይሰማማዋል ፤ እንደነጭ ልብስ ፤ ነጭ ልብስ ፤ ጥቁር ቀለም ፤ ቀይ ቀለም ቢቀቡት ሁሉን ይቀበላል ፤ ሰውም አንድ ጊዜ ወደኃጢአት ፤ አንድ ጊዜ ወደጽድቅ ሲል ይኖራልና ። ወኢለሐኰከ ዘእንበለ ጽነት ከመ ኢይኩን ሠናያቲከ ፤ ዘእንበለ ፍዳ ወኢርእየ ከመ ትኩን ዘትትሌዓል እምኔሁ እምቅድመ ከዊን ዳግማዊ እስመ እግዚአብሔር አዘዘ ይትወከፉ ጠባይዓት ዘይትገበር ቦን እንዲል ፤ ለእርሱ ባሕርይ ግን ጽድቅ እንጂ ኃጢአት አይስማማውምና ፤ ለእሳት ባሕርይ ውዕየት እንጂ ቍረት ለውኃ ባሕርይ ቍረት እንጂ ውዕየት እንዳ ይስማማው ። እስመ ንጹሐት እማንቱ ጠባይዓቲሁ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ ነውር እንዲል ። ጽኑዕ አለው ሰውን ጽኑዕ ቢሉት በሕማም በሞት ይለወጣል ። ኀልፊት ውላጤ ይስማማዋል ፤ ንሕነሰ ንጠፍዕ ወኢንሄሉ ወቅሩብ ሙስናሃ በዲበ አንቀጽ ። እማንቱሰ ይትኃጐላ እንዲል ። በእርሱ ግን ይህ ሁሉ የለበትምና ፥ አንተሰ አንተ ክመ ወዓመቲከኒ ዘኢየኃልቅ አንተሰ ትሄሉ ለዓለም ፥ እስመ ስምኩ መለኮት ዘዲበ ህላዌሁ ሠናይ ወኢይትነትን እምዘሀሎ እስመ አነ አምላክ ዘኢይትዌለጥ እንዲል ፤ ክቡር አለው ፤ ሰውን ክቡር ቢሉት ከአፍአ ባገኘው ገንዘብ ነው እንጂ የባሕርይ አይደለም ። ምንት ብከ ዘኢነሣእከ እምካልዕከ ወምንት ብከ ዘኢኮነ ውሁበ ለከ እንዲል ። እርሱ ግን ከባሕርዩ ያገኘው ነውና ባዕል ዘኢይሌቅሕዎ እግዚእ ዘኢይግእዝዎ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ ዘኢይሠይምዎ ፤ ስብሐቲሁ ዘእምነቤሁ ፣ ወውዳ
ሴሁ እምዚአሁ እንዲል ። ልዩ አለ ፤ ከእርሱ በቀር ፈጥሮ
የሚገዛ የለምና ። ቅዱስ ኃያል ፤ ኃያል ዘአልቦ ድካም
እንዲል ። ቅዱስ ሕያው እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ
እንዲል ፤ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ፤ ቅዱስ ኃያል ወልድ ፤
ቅዱስ ሕያው መንፈስ ቅዱስ ዘተወልደን አሳልፎ ለወ
ልድ ይቀጽሏል ። አንድም ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ።
ቅዱስ ኃያል መንፈስ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ሕያው ወልድ
ነው ። ዘኢይመውት አለ በባሕርዩ ሞት የለበትምና ።

ዘተወልደ ፤

አሁን የተመቸ ።

እማርያም እምቅድስት ድንግል ፤

እምና እም አንድ ወገን ፤ ንዕድ ክብርት ከምትሆን ከእ
መቤታችን የተወለደ ። ሐተታ ዘተወልደ እንደ ወን
ጌል ።

ተሣሃለነ እግዚኦ ፤

መላእክት ተናግረውታል ቢሉ ፤ አቤቱ ራርተህ ጸጋ
ህን ስጠን ። ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ተናግረውታል ቢሉ ።
አቤቱ ራርተህ ሥርየተ ኃጢአትን ስጠን ። ከአካሉ ተሰ
ምቷል ቢሉ ፤ አቤቱ ራርተህ አድነን ። ቅዱስ እግዚአብ
ሔር ፤ ቅዱስ ኃያል ፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እን
ዳለፈው ።

ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ፤

በዮርዳኖስ የተጠመቀ ። ሐተታ ፤ እንደ ወንጌል ።



ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ፤

በመስቀል የተሰቀለ ሐተታ ። እንደ ወንጌል ፣ ዕፀ
መስቀልን ከዚህ ይሰበስባል ። ሳአል ልጁ ታመመበት
ፈላስፎችን ሰብስቦ ልጄን አድኑልኝ አላቸው ፤ የማ
ይቻላቸው ሆነ ። እነሱ ለእኛስ አይቻለንም የንስር
ዕንቍላል አስመጥተህ ከግንብህ አግብተህ ዝጋበት ።
ንስር ልጁ ከዚያ እንዳለ ዐውቆ ከገነት ዕፅ ቆርጦ አም
ጥቶ ከግንቡ ላይ ይጥለዋል ፤ ግንቡ ይሰነጠቃል ዕንቍ
ላሉን ይዞ ይሄዳል ፤ በዚህ ልጅህ ይፈወስልሃል አሉት።

ንጉሥ ላስፈልግ ባለ ጊዜ የሚቸግረው የለምና አስ
ፈልጎ አምጥቶ ከግንቡ አግብቶ ዘጋበት ። ንስር ዕንቍ
ላሉ ከዚያ እንዳለ ዐውቆ ከገነት ዕፅ ቆርጦ ፤ አምጥቶ
ጣለበት ግንቡ ተሰነጠቀ ። ዕንቍላሉን ይዞ ሔደ ፤
በዚያ ልጁ ተፈውሶለታል ። ይህም ዕፅ ገባሬ ተአምራት
ነው ፤ ወደ ዮርዳኖስ ሲሄድ ሰዎች አግኝተውት በጽንፈ
ዮርዳኖስ ተክለውታል ። ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሲሠራ
አስቈርጦ አምጥቶታል ፤ መቃን ቢያደርጉት አጥሮባቸው
ጉበን ቢያደርጉት ረዝሞባቸው እንዳይቈርጡት እንጨቱ
መልካም ነውና አሳዝኖዋቸው ከደጅ ወድቆ ሲኖር ንግ
ሥተ አዜብ ታምሪን የሚባል ነጋዴ ወዳጅ ነበራት የሰ
ሎሞንን ጥበብ እያመጣ ይነግራታል ፤ ሂጄ ልረዳው
ብላ መቶ ኻያ መክሊተ ወርቅ ፤ ዝባድ ተንከራ ዘኢ
ትዮጵያ ይለዋል ሉል ፤ በወዲያ የማይገኝ ባገራችን የሚ
ገኝ ሽቱ ገጸ በረከት ይዛ ሂዳለች ። ስትሄድም በየመን

ገዱ እያስዘራች ሄዳለች ፤ ስትመለስ ሥንቅ እንዲሆናት
ነው ። ከእግሯ እንደ ምዳቋ ቀንድ ፤ እንደ አህያ ሰኰ
ናም ቢሉ ያለ ነበራት ብላቴናው አይቶ ገብቶ በዘመ
ንህ የማይመጣ የለም እንዲህ ያለች ሴት መጥታለች ፤
አለው ፤ ግቢ በላት አለው ። ስትገባ ይህ ገባሬ ተአም
ራት ዕፅ ከደጅ ወድቆ ይኖራል ብትራመደው ደኅና ሁና
ለች ፤ በዓይኑ መዓት አየው ፤ ንጉሥ ሳላይ አልነገርሁ
ህም ጠይቀህ ቅጣኝ አለው ። ጠየቃት ፤ እውነት ነበረ
ብኝ ፤ ነገር ግን ከደጅህ የወደቀ ገባሬ ተአምራት ዕፅ
አለ እሱ ፈወሰኝ እንጂ አለችው ። እሱ አንድ ብር እሷ
አንድ ብር ይሸብቡታል ። ከእሳቸውም በኋላ የተነሡ ነገሥ
ታት ኻያ ስምንት ናቸው ፤ አንድ አንድ ብር ይሸብቡታል ።
ወርቁን ለይሁዳ ሰጥተው በእንጨቱ ጌታን ሰቅለውታል
ሐረገ ወይን ዘእምኃሲሶን ይትገዘም ወበኅልኅታ ይተከል
ሐረገ ወይን ኮነ መድኃኒትየ ዘእምኀበ እግዚአብሔር
እንዲል ። አንድም ሰሎሞን አዋጅ ነግሮ ዘመተ ሁሉ
ሲረዳው ንስር ሳይረዳው ቀረ ፤ በበቀል የንስሩን ግል
ገል ከግንቡ አግብቶ ዘጋበት ። ንስር ግልገሉ ከዚያ እን
ዳለ ዐውቆ ፤ ከገነት ዕፅ ቈርጦ አምጥቶ ከግንቡ ጣለው
ግንቡ ተሰነጠቀ ፤ ልጁን ይዞ ሔደ ፤ ይህን ቤቱን
ሲሠራ ሠረገላ አድርጎ ሠራው በዚህ ምክንያት ልቡሳነ
ሥጋ አጋንንት እየተገለጹ ይታዩታል ፤ እያሠረ ህንድ
ያግዛቸው ነበረ ፤ በዚህ ሰቅለውታል ። አንድም ከመ
ቃብረ አዳም የበቀለ ዕፀ ዘይት ፤ ሎጥ በዕንባው ያለመ



ለመው ዕፅ ፤ ታቦተ ጽዮን የመጣችበት ዕፀ ድንባዝ ፤
ጌታ በፍኖተ ቢታንያ የረገማት ዕፀ በለስ ፤ ዘኪዎስ የወ
ጣበት ዕፀ ሰግላ ነው ። በዚህ ሁሉ እንደምን አድር
ገው ይሰቅሉታል ቢሉ አቋሙ አንድ ነው ፤ አግዳሚ
ውን ከዚህ ሁሉ ሰብስበው በብረት ጠርቀው ሰቅለው
ታል ፤ ይህም በግብፃውያን የእጅ መስቀል ይታወቃል
ግብፃውያን የእጅ መስቀል ሲይዙ ከብዙ ዕፀዋት ሰብ
ስበው በሙሻ ዘር አያይዘው ነውና ።
ተሣሃለነ እግዚኦ ፤ እንዳለፈው ።
ቅዱስ እግዚአብሔር ፤ ቅዱስ ኃያል ፤ ቅዱስ ሕያው
ዘኢይመውት ፤ እንዳለፈው ።
ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት ፤
በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ ። ሐተታ
እንደ ወንጌል ።
ዓርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ፤
በክብር በሥልጣን በቅዳሴ ፤ በብርሃን ዓረገ ።
ወነበረ በየማነ አቡሁ ፤
ባባቱ ዕሪና ኖረ ። ነበረም ብሎ ቢናገር ቦታ ተወ
ስኖበት አይደለም ፤ በምልዓት በክብር ሲል ነው ። እስመ
ብሂለ የማን ይመርህ ኀበ ተዋሕዶቶሙ በክብር እንዲል ።
ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ፤
ዳግመኛ በክብር በሥልጣን በቅዳሴ በብርሃን ይመጣል።
ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ፤
ሕያዋንን ፤ ሙታንን ይገዛ ዘንድ ። አንድም በሕ
ያዋን ፤ በሙታን ይፈርድ ዘንድ ። ሐተታ ጻድቃንን

www.ethiopianorthodox.org

ሕያዋን አላቸው ፤ በነፍስ ሕያዋን ናቸውና ። አንድም በነፍስ ሕያዋን የሚሆኑበትን ሥራ ይሠራሉና ። አንድም የሕያው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናቸውና ፤ ኃጥአንን ሙታን አላቸው ። በነፍስ ሙታን ናቸውና ። በነፍስ ሙታን የሚሆኑበትን ሥራ ይሠራሉና ፤ አንድም የሞት የዲያብሎስ ማደሪያ ናቸውና ። አንድም ኃጥአንን ሕያዋን አላቸው ፤ ጸላእትየሰ ሕያዋን ወይሄይሉኒ እንዲል ፡ ጻድቃንን ሙታን አላቸው ምውት አነ በኀበ ዓለም ፤ ዓለምኒ ምውት ፤ በኀቤየ እንዲል ፤ አንድም ኃጥአንን ሕያዋን ሙታን አላቸው ፤ ሕያዋን አላቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ፤ ሙታን አላቸው ፤ ከዕለተ ምጽአት በኋላ ። አንድም ሕያዋን አላቸው ፤ በዚህ ዓለም ፤ ሙታን አላቸው በወዲያው ዓለም ። አንድም ሕያዋን አላቸው በሥጋ ፤ ሙታን አላቸው በነፍስ ፤ ጻድቃንን ሕያዋን ሙታን አላቸው ። ሙታን አላቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ሕያዋን አላቸው ከዕለተ ምጽአት በኋላ ። አንድም ሙታን አላቸው በሥጋ ፥ ሕያዋን አላቸው በነፍስ ። አንድም ሙታን አላቸው በዚህ ዓለም ፤ ሕያዋን አላቸው በወዲያው ዓለም ተሣሃለነ እግዚኦ ፤ እንዳለፈው ።

፩/ ስብሐት ለአብ ፤

፩/ ለአብ ወላዲ ተብሎ መመስገን ይገባዋል ።

ስብሐት ለወልድ ፤

ለወልድም ተወላዲ ተብሎ መመስገን ይገባዋል ።



ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ፤

ለመንፈስ ቅዱስም ሠራፂ ተብሎ መመስገን ይገባዋል ። አንድም ስብሐት ለአብ ልጁን በሥጋ ለላከ ለአብ መመስገን ይገባዋል ። ስብሐት ለወልድ ፤ ሰው ለሆነ ሥጋ ለለበሰ ለወልድም መመስገን ይገባዋል ። ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ፤ ለከፈለ ላነፃ ላዋሐደ ለመፈስ ቅዱስም መመስገን ይገባዋል ።

ይእዜኒ ፤ እስከ ዕለተ ሞት ።
ወዘልፈኒ ፤ እስከ ዕለተ ምጽአት
ወለዓለመ ዓለም ፤
ይህ ዓለም አልፎ በሚመጣው ዓለም ።

አሜን ወአሜን ።

አሜን በየአባባሉ ይፈታል ፤ ሃይማኖት ቢሉ አዎን ። ታሪክ ቢሉ እውነት ነው ። በረከትን ቢሉ ይደረግልን ። ማለት ነው ።

ለይኩን ለይኩን ፤ ይጽና ይደረግ ።
ቅዱስ ሥሉስ ፤

ልዩ ሦስት አለ ። ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለስልዋኖስ ። የአካል ሦስትነት ቢኖራቸው የግብር ሦስትነት የባሕርይ የህልውና አንድነት የላቸውም ። ለፀሐይ ለእሳት ለቀላይ የግብር ሦስትነት ቢኖራቸው የአካል ሦስትነት የባሕርይ የህልውና

www.ethiopianorthodox.org

አንድነት የላቸውም ፤ ሥላሴ ግን በአካል ሦስት ፤ በባሕርይ በህልውና አንድ ናቸውና ።

እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለነ ፤

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው ። ሐተታ ዘጠኙን ቅዱስ ከዚያ ተናግሮ አሥረኛውን ከዚህ አመጣው ፤ ባሥረኛው ቦታ የገባን እኛ ነንና ዘጠኙ የመላእክት ከተማ ምሳሌ ። አንድም ሦስቱን ፤ አንድ ወገን ሦስቱን አንድ ወገን አድርጎ የሦስትነት ይህ የአንድነት ምሳሌ ።

ይ ካ ፤ ይበል ካህን ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ፤

ረቂቁን ብርሃን ለሰጠን ግዙፉን ብርሃን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል ።

ይ ሕ ፤ ይበሉ ሕዝብ ።

ርቱዕ ይደሉ ፤

እውነት ነው ፤ ወይደሉ ብለህ አቅና ያውም ይገባል ። አንድም ርቱዕ ይደሉ ብለህ አቅና ለእርሱ በሚገባ ይገባል መመስገኑ ባንድነቱ ምንታዌ ፤ በሦስትነቱ ርባኤ ሳይቀላቅሉ ። አንድም ለእርሱ በሚገባ ነገር ይገባል ።

ሐተታ ሰውን ባዕል ቢሉት ንዴት ፤ ጻድቅ ቢሉት ሐሰት ፤ ኃያል ቢሉት ድካም ፤ ይስማማዋል ። እሱ ግን ባዕል ዘአልቦ ንዴት ፤ ጻድቅ ዘአልቦ ሐሰት ፤



ኃያል ዘአልቦ ድካም ነውና ። አንድም ለኛ በሚገባ ነገር ማመስገኑ ይገባናል ። ሐተታ ሰውና መላእክትን መፍጠሩ ለምስጋና ነውና ። ወበእንተዝ ፈጠሮ ለሰብእ ከመ ይትለአኮ በአምሳለ መላእክት እንዲል ።

፭/ ይካ ለከ እግዚእ ለገባሬ ኵሉ ለዘኢታስተርኢ፡
አምላክ ፤

፮/ ለና ለ አንድ ወገን ኸያ ሁለት ሥነ ፍጥረትን ለፈጠርክ ለማትመረመር ፈጣሪ ላንተ ።

ንሰፍሕ ነፍስነ ።

ሰውነታችንን እናስገዛለን ። አንድም ኃቤከ ሲል ነው ፤ ኸያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት ወደ ፈጠርክ ወደ ማትመረመር ፈጣሪ ወዳንተ ልቡናችንን በሃይማኖት ፤ ሕሊናችንን በአንክሮ በተዘክሮ እናቀርባለን ። ለእመ ኢትክል ሰፊሐ እዴከ ስፍሖ ለሕሊናከ እንዲል ።

፯/ ወስብሐተ ዘነግህ ንፌኑ ለከ እግዚእ ፤

፰/ አቤቱ የነግህ ምስጋና እናቀርብልሃለን ። ሐተታ መላእክት ተናግረውታል ቢሉ ለይኩን ብርሃን ባለ ጊዜ ነውና ነግህ የተመቸ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ተናግረውታል ቢሉ ዘመነ ወንጌልን ነግህ እያለው ይሄዳልና ነግህ አለው ። አንድም ቀሳውስት በንቅወተ ዶርሆ ይጸልዩ በቃልና አያይዞ የሚነጋ ስለሆነ ነግህ አለው ። ጥቅስ እስመ ንቅወተ ዶርሆ ይሰብክ ምጽአተ ብርሃን እንዲል

www.ethiopianorthodox.org

ኀሕተ ሙቀተ ይላል በናቱ ። አንድም በቁሙ በነግህ
ይጸልዩታልና የተመቸ ።

ለጥበበ ኵሉ ፤

የአብ የመንፈስ ቅዱስ የቃልነት ጥበባቸው ለምት
ሆን ላንተ የነግህ ምስጋናን እናቀርባለን ። ሐተታ ካንድ
ከወጣ ኵሉ ማለት ልማድ ነው ፤ ወውእቱ ዘአኀበረ
ተሰናዕዎተ ኵሉ ዘአኮ ቀሊለ ይረክብ ሰብእ በኀበ ኮኑ
አማልክት ብዙኃነ ወአጋዕዝት ብዙኃነ በሰማይ ወበ
ምድር እንዲል ። አንድም የመላእክት ዕውቀት ለም
ትሆን ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። ዝንቱ ብርሃን ኮናሙ
ጥበበ ወአእምሮ እንዲል አንድም የሰው ሁሉ ዕውቀት
ለምትሆን ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። ወመልአሙ
ጥበበ ለባስልኤል ወለኤልያብ እንዲል ። አንድም የፍ
ጥረት ሁሉ ዕውቀት ለምትሆን ላንተ የነግህ ምስጋና
እናቀርባለን ፤ ሰገኖንስ እንኳ ወከፈላ ምክረ እምጥበብ
እንዲላት ።

ኃያል ፤

ይህን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር ፤ እምኀበ አልቦ
ኀበቦ ከኢምንት ወደ ምንት አምጥተህ ለፈጠርክ ላንተ
የነግህ ምስጋና እናቀርባለን ፤ አንድም ከመኖር ወዳለመ
ኖር እምኀበ አልቦ ኀበቦ ከምንት ወደ ኢምንት ለምታሳ
ልፈው ላንተ የነግህ ምስጋና እናቀርባለን ። አንድም
ከእርሱ በቀር በወርቀ ደሙ ዋጅቶ የሚገዛ ሌላ የለምና
ኃያል አለው ።



ብዙኃ ሣህል አምላክ ፤

ይቅርታህ የበዛ ፈጣሪ ሐተታ እሠር በፍንጅ ፤ ጣል
በደጅ ፤ እሠር ፤ በግንድ ፤ ጣል በግድ አይልምና ። አን
ድም ብርሃናትን ማመላለሱን ነፋሳትን ማንፈሱን ማያ
ትን አፍላጋትን ማፍሰሱን በጋና ክረምትን ፤ መዓልትና
ሌሊትን ማፈራረቁን ሲያይ እንዲህ አለ ፤ ይህን ፍጠ
ርልኝ ብሎት ፈጥሮለታልና እንዲህ አለ ቢሉ ፤ ለባ
ሕርዩ እንዲያሻው ዐውቆ ስለፈጠረለት ፤ አንድም ጌት
ነቱ ያራራዋልና እስመ ቅንየትከ ወምልክናከ ይሬስየከ
ትሣሃል ላዕለ ኵሉ እንዲል ።

ሣራሪሃ ለነፍስ ፤

ነፍስን ለፈጠርካት ፤ ላዋሐድካት ላንተ የነግህ ምስጋና
እናቀርብልሃለን ።

፪/ ንሴብሐከ ለዘእምቅድመ ዓለም ተወልደ እምአብ ፤

፪/ ተወለድከ ሲል ነው ፤ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል
ዘእምአካል ፤ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለድህ አንተን
እናመሰግንሃለን ። አንድም ለተወለድህ ላንተ ምስ
ጋና እናቀርባለን ።

፫/ ቃል ዘባሕቲቱ ፤

፫/ የብቻው የአብ ቃል የምትሆን አንተን እናመሰግ
ንሃለን ። አንድም ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ፤ ሐተታ
አሁን ከመንፈስ ቅዱስ ሊለየው አይደለም ፤ ከፍጡራን

2*

www.ethiopianorthodox.org

ሲለየው ነው እንጂ ፤ እንዳይለየውስ ሲያጠይቅ ቃለ አብ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ወልድኒ ቃለሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ እንዲል ። አንድም አካላዊ ቃልነት ለብቻህ የሚሆን ፤ ሐተታ አትሪኮን አተርጋዎን ፤ ቦር ፎሪኮን የሚባሉ ዝርዋን ቃላት ፤ ቃላተ እንስሳ ፤ ቃላተ ሰብእ ፤ ቃላተ መላእክት አሉና ከዚያ ሲለይ እንዲህ አለ ። አንድም ትንቢተ ነቢያት የብቻህ የሚሆን ፤ ይወርዳል ፤ ይወለዳል ተብሎ የሚነገርለት ከርሱ በቀር ሌላ የለምና ። አንድም ሕገ ወንጌል ለብቻህ የምትሆን ሐተታ ምንም የሦስቱ ሕግ ብትሆን ፤ ሰው ሁኖ የሠራት መደበኛዋ እሱ ነውና ።

በቅዱሳኒሁ ዕሩፍ ፤

በምእመናኑ አድሮባቸው የሚኖር ዝንቱ ፀሐይ ዘበእንቲአሁ ይቤ አሞንዮስ ለባሴ አምላክ ለቅዱሳን ቦሙ አሐዱ ጥሪት መዓልተ ወሌሊተ ዜአሆሙ ውእቱ እንዲል ። አንድም ዕሩፍ ዘባሕቲቱ ብለህ ግጠም ብቻውን በምእመናን አድሮባቸው የሚኖር ሐተታ ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ ከአብ ፤ ከመንፈስ ቅዱስ ሲለየው አይደለም ። እመበ ዘዐቀበ ቃልየ አነ ወአቡየ ንመጽእ ኀቤሁ ወንገብር ምዕራፈ ውስቴቱ እስመ ስብሐቲሁ ወኃይሉ ለእግዚአብሔር ወመንፈሱ የዓርፍ ላዕሌከሙ እንዲል ።



፱/ ኪያከ ዘትሴባሕ እምስብሐታት ዘኢያረምም

፱/ አርምሞ ጽርዓት በሌለበት በሊቃነ መላእክት ቃል የምትመሰገን እናመሰግንሃለን ።

አንድም ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።

ወእምሠራዊተ ሊቃነ መላእክት አለቆች ያሏቸው ሠራዊተ መላእክት የሚያመሰግኑህ አንተን እናመሰግንሃለን ። አንድም ፥ ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።

፲/ ኪያከ ዘኢተገብረ በእድ ፤

፲/ በእጅ ያልተፈጠርክ አንተን እናመሰግንሃለን ። አንድም ፥ ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። ሐተታ ፥ ለአክብሮተ አዳም ጭቃ ይዞ ታየ ይለዋልና ። አንድም ፥ ለይኩን ባለው ቃል ያልተፈጠርክ አንተን እናመሰግንሃለን አንድም ፥ ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። ሀሎኑ እዴሁ ለኢዮአብ በዝ ነገርኪ ፤ በእደ ሙሴ ወአሮን ፤ ወይትኃደግ ኃጢአት በእደ ካህናት እንዲል ። አንድም ፥ በዘር ያልተፈጠርክ አንተን እናመሰግንሃለን ። አንድም ፥ ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። ደብተራ እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ ሕፅውኒ ኢገብረ ኃጢአተ በእዴሁ እንዲል ።

ፈጣሬ ኅቡዓት ዘኢታስተርኢ ፤

ኅቡዓትና ዘኢታስተርኢ አንድ ወገን ነው። ኅቡዓት ካለ ዘኢያስተርእ. ዘኢያስተርኢ ካለ ኅቡዕ ቢል በቀና ነበር ፤ የማይታዩትን ፍጥረታት የፈጠርክ አንተን እናመሰግንሃለን ።

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ። በርኅቀት በርቀት ፤ በርቀት ፤ ነፍሳት ፤ ነፋሳት ፤ መላእክትን ፤ በርኅቀት ብሔሞትን ሌዋታንን ናጌብን አድማስን ። አንድም ፈጣሪ ዘኢታስተርኢ የማትመረመር ፈጣሪ አንተን እና መሰግንሃለን ። ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።

ንጹሕ ወቅዱስ ፤

ንጹሕ ከተድኅሮ ወቅዱስ ከተፈልጦ ። አንድም ንጹሕ ከተድኅሮ ከተፈልጦ ቅዱስ ካለመመለክ ካለመስ ገድ ልዩ የምትሆን አምላክ አንተን እናመሰግንሃለን ። ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።

፲፩/ ዜናዊ ፤

፲፩/ ለይኩን ብለህ የተናገርከ ።

ዘነገረነ ጥበበ ኅቡዓተ ቅድሳቲከ ፤

ያው ግን ያንድነትህን የሦስትነትህን ምሥጢር ጥበብነቱን የነገረን ። ሐተታ ለይኩን ባለ ጊዜ መላእ ክት ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ፤ ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ብለው አመስግነዋል ። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፤ የሦስትነ ነት ምሉዕ ስብሐቲከ ፤ ያንድነት ምሳሌ ነው ። አን ድም ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኃን ብለህ የተናገርከ ያው ግን ያንድነትህን የሦስትነትህን ምሥጢር ጥበብ ነቱን የነገረን ፤ ሐተታ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለን



መጠመቃችን የሦስትነት ። አንድ ልብሰ ብርሃን ለብ ሰን መውጣታችን ያንድነት ምሳሌ ነው ። አንድም [በዘ ልዓ ሥጋየ ፤ ወሰትየ ደምየ ፤ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ብለህ የተናገርከ ያው ግን ያንድነትህን የሦስትነትህን ምሥ ጢር ጥበብነቱን የነገረን ሐተታ ፤ ኅብስቱን ከሦስት ያነቃዋል ። ዘባኑን አይለየውም ፤ ከሦስት ማንቃቱ የሦስትነት ዘባኑን ያለመለየቱ ፤ ያንድነት ምሳሌ ነውና አንድም ዘበልዓ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለ ዓለም ብለህ የተናገርከ ። ያው ግን የጌትነትህን ምሥ ጢር ጥበብነቱን የነገረን ። ሐተታ ኅብስቱን በመጀመ ሪያ ከሁለት ያነቃዋል ፤ ዘባኑን አይለየውም ከሁለት ማንቃቱ የተዓቅቦ ። ዘባኑን አለመለየቱ የተዋሕዶ ምሳሌ ነውና ።

ወብርሃነ ለነ ዘኢይጠፍዕ አሰፎከነ ፤

የማይመረመር ። ክብርን አወርሳችኋለሁ ብለህ የነ ገርከን ። አንድም ካደረ የማይለይ ሀብትን ፤ ከተሰጠ የማ ይነሣ ዕውቀትን አሰጣችኋለሁ ብለህ የነገርከን አንተን እናመሰግንሃለን ። አንድም ላንተ ምስጋና እናቀርባለን።

ስብሐተ ወአኰቴተ ንፌኑ ወቅድሳተ ንጹሐ ፤

ስቡሕ እኩት ቅዱስ እንልሃለን ። አንድም ፍጹም ምስጋና ላንተ እናቀርባለን ። ንጹሕ አለ ፤ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትምና ።

www.ethiopianorthodox.org

ንብል ንሕነ እሊዓከ አግብርት ፤

እኛ ቤተ ሰቦችህ ፤ ባሮችህ ፤ አገልጋዮችህ ፤ ባለ ሟሎችህ ፤ ቀሳውስት አንተን እናመሰግንሃለን ።

ወሕዝብኒ ኪያከ ይሴብሑ ፤

ሕዝቡም አንተን ያመሰግናሉ ፤ አንተን ባያመሰግኑ ዕድል ፈንታቸው ጽዋዕ ተራቸው ከዲያብሎስ ጋራ ይሆናል ። እሱ አመስግን ቢሉት አላመሰግንም ቢል ባደረው ጨለማ ጠቅሎ አንጦርጦስ አውርዶታልና ።

ይ ሕ ፤ ይበሉ ሕዝብ ።

፲፪/ ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ ፤

፲፪/ ሕዝቡም አቤቱ አንተን እናመሰግናለን ይበሉ ።

ይ ካ ፤ ይበል ካህን ።

፲፫/ አምላከ ብርሃን ፤

፲፫/ ረቂቁን ብርሃን የሰጠ ግዙፉን ብርሃን የፈጠረ ።

ወላዴ ሕይወት ፤ የሕይወት መገኛ ።

ርእሰ ለአእምሮ ፤



አንድም የዕውቀት መገኛ በዓይን ሌላውን ሁሉ ያዩበታል ።

እሱን ግን አያዩትም ። ቅዱሳን በእርሱ ሌላውን ያዩበታል ።

የእርሱን ባሕርዩን መርምረው አያውቁትም ። አንድም ፤ የዕውቀት ምክንያት ፤ ሐተታ የበሉትን የጠጡትን መሬት ይሸከማል ውኃ ያረጥባል እሳት እንደገና ያበስላል ፤ ነፋስ ጥሩ ጥሩውን ሽቅብ ይዞ ይወጣል ። ለሰው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት አሥራው አሉት ። ነፋስ ለስድስቱ ያቀብላል ፤ ስድስቱ ለስልሳው ። ስልሳው ለስድስቱ መቶ ያቀብላሉ ። በዚህ ሰው ዐዋቂና ሕያው ሆኖ ይኖራልና የዕውቀት ምክንያት አለ ።

፲፬/ ወሀቤ ጸጋ ፤

፲፬/ ለአዳም አካልን የሰጠህ ኢትንሥእኒ ጸጋየ ዘእንበለ እሙት እንዲል ።

ዘእምቅድመ ፍጹም ፤

ከልጅነት አስቀድሞ ። አንድም ለአዳም ልጅነትን

www.ethiopianorthodox.org

ገባሬ ነፍስ ፤

ነፍስን የፈጠርከ ፤ አንድም ያዋሐድህ ።
በቃዒ ጸጋዌ መንፈስ ቅዱስ ፤

መንፈስ ቅዱስን በመስጠት የሚረባ የሚጠቅም አንድም በቃዒ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ አንድም በቃ ዒን ለነፍስ ቀጥል ነፍስን የፈጠርህ ያዋሐድህ ።

፲፩/ መዝገበ ጥበብ ፤

፲፩/ ያንድነት የሦስትነት ባለቤት ። አንድም የሥ ጋዌ ባለቤት ። አንድም የጥበብ መገኛ ። ሐተታ ከነገ ሥታት ቤት ወርቅ ዕንቍ እንዲገኝ ከእርሱም ጥበብ ይገኛልና ። አንድም የጥበብ ወሳኝ ፤ ሐተታ ሣጥኑ ወርቁን ዕንቍን ይወስነዋል እንጂ ወርቁ ዕንቍ ሣጥኑን እንዳይ ወስነው እርሱም የቅዱሳንን ጥበብ ይወስነዋል እንጂ ቅዱሳን የሱን ጥበብ አይወስኑትምና ።

ረዳኢ ፤
ትርጓሜ እንደ ትምህርተ ኅብዓት ነው ።

መምህረ ቅዱሳን ፤

ጽኑዓን ሲል ነው የጨረቃ የፀሐይ ፈጣሪ ወር ኢኩ ረሲዓነ እንዘ ይወርዱ ውስተ መቃብር ቅዱስ እን ዲል ። አንድም የመላእክት ዕውቀት ዝንቱ ብርሃን ኮኖሙ ጥበበ አእምሮ እንዲል ። አንድም የነቢያት የሐ ዋርያት መምህር ።



መሠረተ ዓለም ፤

የዓለም መሠረት መገኛ ። ይነብር ጠፈረ ወይጸ ውር ድደ ኵሉ እኁዝ ውስተ እዴሁ አጽናፈ ዓለም በእራኁ እንዲል ።

፲፪/ ዘይትዌከፍ ጸሎተ ንጹሐን ፤

፲፪/ የንጹሐንን ጸሎት የሚቀበል ፤ ሐተታ ፍጥነ ቱን ሲያይ ነው እንጂ የኃጥአንን ጸሎት አይቀበልም አላለም ጸሎቱ ለጻድቅ እምአፍ እስከ ዕዝን እንዲል ። አንድም በንስሐ ከኃጢአት ንጹሐን ሁነው የሚያቀር ቡትን ጸሎት የሚቀበል ። አንድም ከቂም ከበቀል ንጹ ሐን ሁነው የሚያቀርቡትን ጸሎት የሚቀበል ።

ሐተታ በቂም በበቀል ሁኖ ቢጸልዩት አይቀበልምና ፤ እስመ ዘያነብር ቂመ ወበቀለ ውስተ ልቡ ጸሎቱ ኢውክ ፍት ቅድመ እግዚአብሔር ። ጸሎቱ ለመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማዕከለ አሥዋክ እንዲል ።

ለከ ንሴብሕ ወልድ ዋሕድ ፤

ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ ወልድ ዋሕድ ኪያከ ንሴ ብሕ ብለን ፤ አንተን እናመሰግንሃለን አንድም ለከ ብለን ምስጋና እናቀርባለን ።

፲፫/ ቀዳሜ በኵር ፤

፲፫/ ከዕለተ እሑድ የምትቀድም በኵረ ኵሎን ዕለታት እንዲል ፤ አንድም ከአዳም የምትቀድም በኵረ ኵሉ ፍጥረት እንዲል ፤ ቀዳማዊ ወበኵር ይላል ፤ ቀዳ ማዊ የምትሆን ወበኵር ፤ በኵር የምትሆን አንተን እና

www.ethiopianorthodox.org

መስግንሃለን ። አንድም ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።
አብነት ኪያከ ወልደ ዋሕደ ፤ ኪያከ ቀዳሚ ፤ ኪያከ በዠረ
ይላል ትርጓሜው አይለወጥም ።

ቃለ አብ ፤ የአብ አካላዊ ቃል ።

ዘለዥሉ ዚአከ ጸጋ ዘወሀብከነ ለእለ ንጼውዓከ ።
ለምንለምንህ ለኛ ለሁሉ የሚሆን ያንተን ጸጋ የሰጠ
ኸን አንድም ለዥልነ ለእለ ንጼውዓከ ። ለምንለምንህ
ለሁላችን ያንተን ጸጋ የሰጠኸን ።

፲፰/ አብ ንጹሕ ዘአልቦ ነውር ፤

፲፰/ ምቀኝነት የሌለብህ ልዩ አባት ።

ዘቦቱ ጥሪት ኅበ ፃዔ ወቊንቊኄ ኢያማስኖ ።

ብል የማይበላው ነቀዝ የማያበላሸው ብዕል ያለህ ።
ለዘበዥሉ ሕሊና ለእለ ይትዌከሉ ብከ ትሁብ ፤ ዘትሁቦ
ሲል ነው በፍጹም ልቡናቸው ለሚያምኑብህ የትምሰ
ጠው ብዕል ያለህ ። አንድም በፍጹም ልቡናቸው ለሚያ
ምኑብህ የምትገልጸው የማያልፍ ጥበብ ያለህ ። ታሪክ
እንደ አባ መቃርዮስ አርድእቱን አስከትሎ ሲሄድ ሕፃ
ናት በአደባባይ ተሰብስበው እኩሉ አንድ ወገን እኩሉ
አንድ ወገን ሁነው ቡድን ቡድን ከምን ከምን አንድ
ባለጸጋ አለ እሱ ይወደናል እኛ እንጠላዋለን አንድ ድኃ
አለ እሱ ይጠላናል እኛ እንወደዋለን ሲሉ ቁሞ ያዳም
ጣቸዋል ። አባታችን ከኒህ ሕፃናት ምን ቁም ነገር ይገ
ኛል ብለህ ቁመህ ታዳምጣቸዋለህ አሉት መንፈስ



ቅዱስ በኒህ በሕፃናት አድሮ ሲዘልፈን አትሰሙምን ፤
ባለጸጋ የተባለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ እርሱ
ይወደናል ማለት ክብሩን ሊያወርሰን መንግሥት ሰማ
ያት ሊያገባን ይወዳል ፥ እኛ እንጠላዋለን ማለት ሕጉን
እናፈርሳለን ። ደኃ የተባለ ዲያብሎስ ነው ፤ እኛ እንወደ
ዋለን ማለት እሱ የሚወደውን ኃጢአት እንሠራለን
እሱ ይጠላናል ማለት እንደሱ ፍዳ ሊያጸናብን ገሃነም
ሊያወርደን ይወዳል ብሎ ተርጉሞ ነግሯቸዋል ።

ዘያፈትዎሙ ለመላእክት የሐውጽዎ ለዘእምቅድመ
ዓለም ብርሃን ፤

ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ብርሃን ፤ ባሕርይህን ያዩት
ዘንድ መላእክትን የሚያስመኛቸው ፤ ሐተታ ያዩት የለ
ምን እንደ ገና እንዲህ ማለቱ ስለምን ነው ቢሉ ፤ ቢያዩት
ቢያዩት አይጠግቡትምና አይሰለቹትምና እንዲህ አለ ፤
አስረጅ ፤ እንዲህ ያለ ዕቃ ወጣ ብለው ለሰው ይነግሩ
ታል ፤ እስኪያየው ይቸኩላል ካየው በኋላ ግን ይሰለቸዋል
ይጠግበዋል እሱን ግን ቢያዩት ቢያዩት አይሰለቹምና ።
አንድም በእግረ ቅዳሴ ይጐበኙት ዘንድ መላእክትን
የሚያስመኛቸው ። ሐተታ ምነው ያመሰግኑት የለም
ቢሉ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ አመስግነውት
አንዱን ሰዓት ካራት ከፍለው የዕርቦውን እንኳን ያህል
ያመሰገኑት አይመስላቸውምና ። ወኢይመስሎሙ ለመ
ላእክት ከመ ዘቀደስዎ መጠነ መንፈቀ መንፈቃ ለአ
ሐቲ ሰዓት እምአመ ተፈጥረ ዓለም እስከኔሁ እንዲል ።

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ያዩት ዘንድ መላእክትን የሚያስመኛቸው ።

ዓቃቢነ ዘኢይማስን ፤

የማይለወጥ ጠባቂያችን ነው ።

፲፱/ መዝገበ ጽልመት አንተ ብነ በሥምረተ አቡከ
ኢብራህከ ለነ ፤

፲፱ በኛ የነበረውን ፍዳ ባባትህ ፈቃድ ያራቅህልን ።

ዘአውጻእከነ እማዕምቅ ውስተ ብርሃን ፤

ከጨለማ ወደብርሃን ያወጣኸን ፤ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ያወጣኸን ። አንድም ከክህደት ወደ ሃይማኖት ያወጣኸን ፤ አንድም ከኦሪት ወደ ወንጌል ያወጣኸን ፤ አንድም ከሲኦል ወደገነት ከገሃነም ወደ መንግሥተ ሰማያት ያወጣኸን ።

ወወሀብከነ ሕይወተ እሞት ፤

ከሞት አድነህ ሕይወትን የሰጠኸን አንድም ከሞት ያዳንኸን ።

ወጸጎከነ እምግብርናት ግዕዛነ ፤

ለኃጢአት አንድም ለሞት አንድም ለፍዳ አንድም ለዲያብሎስ ከመገዛት ነፃ አደረግኸን ።

ዘበመስቀልከ ፤

በመስቀልህ በመሰቀልህ ። አቅረብከነ ኀበ አቡከ
በመልዕልተ ሰማያት ፤



በጌትነት ወዳለ ወዳባትህ አቀረብኸን ። አንድም በመንግሥተ ሰማያት ለመኖር ወዳባትህ አቀረብኸን ።

፳/ በወንጌል መራህከነ ፤

፳/ በወንጌል ፍኖተ ሕይወትን መራኸን ።

ወበነቢያት ናዘዝከነ ፤

እስከዚያውም ድረስ በኦሪት አጸናኸን ፤ አረጋጋኸን ። አንድም በሐዋርያት ፍኖተ ሃይማኖትን መራኸን እስከ ዚያውም ድረስ በነቢያት አረጋጋኸን አጸናኸን ።

ዘለሊከ አቅረብከነ አምላክ ፤

አንተ ቅሉ ያቀረብኸን ፈጣሪ ። ሐተታ ቀድሞ በረድኤት ነበር ፤ ዛሬ ግን በኩነት ነውና አኮ በመል አክ ወአኮ በተንባል አላ ለሊሁ እግዚእ ይመጽእ ወያ ድኅነነ እንዲል ።

አላ ብርሃነ ሀበነ እግዚኦ ፤

ዓዲ ሲል ነው ፤ ደግመኛ አቤቱ ዕውቀትን ግለጽልን

ለከ ለአምላክነ ንወድስ ፤

ላንተ ለፈጠሪያችን ምስጋናን እናቀርብ ዘንድ ፤
አንድም አንተን እናመሰግን ዘንድ ።

ከመ ወትር በዘኢያረምም አኰቴት ፤

አርምሞ ጽርዓት በሌለበት ምስጋና መላእክት ዘወ ትር እንዲያመሰግኑህ እናመሰግንህ ዘንድ ፤ አንድም ኋላ ሙተን ተነሥተን አርምሞ ጽርዓት በሌለበት ምስጋና

እንድናመሰግንህ ዛሬም በሕይወተ ሥጋ ሳለን እናመሰ
ግንህ ዘንድ ።

ጸ፩ ንብል ንሕነ እሊአከ አግብርት ወሕዝብኒ
ኪያከ ይዌድሱ ።

ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ ።

ይሕ ይበሉ ሕዝብ

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው ።

ጸ፪/ ይካ ይበል ካህን ።

ንሜልስ ለከ ዘንተ ስብሐተ እምአፉነ ዘምስለ መን
ግሥትከ ዘለዓለም ኢየሱስ ወልደ እግዚአብሔር ዘመል
ዕልተ ኵሉ ምስለ አብ ።

ጸ፪/ ከአብ ጋራ እንደ አብ ሁሉን የምትገዛ የአብ
የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትህ የዘላለም ነው
ከማለት ጋራ በቃላችን ይህን ምስጋና ሦስተኛ ላንተ
እናቀርባለን ። አንድም ከመንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋራ
እንደ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ ሁሉን የምትገዛ የአብ
የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃላችን ይህን ሦስ
ተኛ ምስጋና ላንተ እናቀርባለን ። ወርኢኩ እሮ ትት
ከፈል መንግሥት በመዳልው እንዲል ። መንፈስ ቅዱስን
መንግሥት ሲል ነው ።

ጸ፫/ ኵሉ ፍጥረት ይሴብሑከ በረዓድ ወበፍርሃተ
መንፈስ ፤

ጸ፫/ ፍጥረት ሁሉ በረዓድ በፍርሃተ ልቡና ያመሰ
ግንሃል ።



ዘኵሉ ነፍስ ይፈርሆ ፤

በመግቦ ኵላዊት ያለ ሰው ሁሉ የሚፈራው የሚያ
መሰግነው ፤ ሊሰርቅ ሊቀማ ሲሄድ ጌታዬ የዛሬን አው
ጣኝ ይላልና፡፡ለበዓለ አስይፍትኒ ውእቱ ይረድእ እንዲል ።

ወኵሎሙ ነፍሳተ ጻድቃን ብከ ይጼወኑ ።

ጻድቃን በአንተ አምነው ጸንተው ይኖራሉ ።

ዘአዝኀንከ እምኔነ ማዕበላተ ውኂዛተ መናፍስት

ነፋሳት እየነቀነቁ ያመጡትን የጕርፉን ፈሳሽነት
ፀጥ ያደረግህልን ። አንድም ሰይጣናት አሠርተዋቸው
ኃጣውእ ያመጡትን ፍዳ ከኛ ያራቅህልን ። አንድም
አጋንንት አነሣሥተዋቸው መናፍቃን ያመጡትን ክህ
ደት ከኛ ያራቅህልን ፤

ዘኮንከነ መርሶ ሕይወት እሙስና ።

ከጥፋት አድነህ የሕይወት ወደብ የሆንኸን ።

ወዘኮንከነ ምጕያየ ዘቦቱ ተስፋ መድኃኒት ዘለ
ዓለም ፤

የዘለዓለም ድኅነት አለኝታ ያለበት መማጸኛ የሆ
ንኸን ፤ ሐተታ ከቀደመው ሀገረ ምስካይ ሲለይ ፤ ያ ከገባ
በኋላ ኃጢአቱ ተመርምሮ ወጥቶ ይደበደባል ። በመንግ
ሥተ ሰማያት ግን ከገቡ መውጣት ካገኙ ማጣት የለምና ፤
ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽኦ አፍኣ እንዲል ።

ጸ፬ በባሕር እለ ይትመነደቡ ታድኅን ፤

ጸ፬/ በባሕር ማዕበል ሞገድ ተነሥቶባቸው መር

www.ethiopianorthodox.org

ከብ ተሰብሮባቸው የተጨነቁትን የምታድን ። ቦ እለ ወጽኡ በሐብለ ሐመር ወቦ እለ ወጽኡ በሰላድው እን ዲል ።

ወለእለ በበድው በጸጋ ትፌውስ

ሐተታ በየብስ ያሉትን በቸርነትህ የምታድን ። መካነ በረድ አለ ፣ ሰው የማይደርስበት ነው ፤ በረዱን እየለየ ወስዶ ከዚያ ያፈሰዋልና ፤ ወያጸንእ ለዝናም በብ ሔረ በድው ኀበ አልቦ ሰብእ ወኢይነብሮ እንለ እመ ሕያው እንዲል ። አንድም በባሕረ ተባሕትዎ የሚጨነ ቁትን የምታድን ፣ ሐተታ ፣ ከባሕር ሁከት እንዳይታጣ ፣ ከተባሕትዎም መንፈሳዊ ሁከት አይታጣምና ፣ በየብስ ተባሕትዎ ያሉትን በቸርነትህ የምታድን ። ሐተታ ፣ ከየ ብስ እክል ተክል እንዳይገኝ ባሕታውያንም የሹትን አያገኙትምና ። ታሪክ እንደ አክሎግ አንበሳዊ ፤ ራሱን ታማሚ ነው ውኃ ሸግ አድርጎ ማን በሰጠኝ ሲል አንበሳ ሰማው ነጋድያን ብርቱን ብላቴናውን በከብት ጭነው ሲሔዱ ነጥቆ አምጥቶ ከፊቱ አቀረበለት እግዚ አብሔር ካመጣህ ወርደህ ብርቱን አውርደህ ውኃ ሸግ አድርገህ ስጠኝ አለው አድርጎ ሰጠው ከነበረበት ወስ ደህ ስጥ ብሎታል ። አንድም በባሕረ ገሃነም የሚጨነቁ ትን የምታድን ። ሐተታ ባሕር አለው ገሃነምን በባሕር ሁከት እንዳለ በገሃነምም ሁከተ ነፍስ አለና ። በየብስ ገሃነም ያሉትን በቸርነትህ የምታድን ። ሐተታ ፤ ከየብስ እህል ተክል እንዳይገኝ ገሃነምም ከወረዱ በኋላ ሃይማ



ኖት ይዞ ምግባር ሠርቶ ክብር ማግኘት መንግሥተ ሰማ ያት መግባት አይቻልምና ።

፳፫/ ወለእለ በመዋቅሕት ጽኑዓን ዘምስሌሆሙ ትሄሉ ፤

፳፫/ በግዞት ቤት ካሉት ጋራ አብረሀቸው የምት ኖር ለሰው ። ለመዋቅሕት ቅጽል ።

ዘእማዕሠረ ሞት ፈትሐነ

ማዕሠር ካልሁ ብሎ ፈትሐነ ብኋል እንጂ ሞተ ነፍስን ከሚያስፈርድ ከኃጢአት ከክህደት የለየኸን ሲል ከሞት ፍዳ ያዳንኸን ።

ዘለምስኪናን ወለልህዋን ይናዝዞሙ ፤

ምስኪናን ልህዋንን ደስ የሚያሰኛቸው ። ሐተታ ፤ ምስኪናን የሚላቸው ተገብሮ የሌላቸው ፤ ልህዋን የሚላ ቸው ተገብሮ ኑራቸው አንበጣ የበላባቸው በረድ የመ ታባቸው ናቸው ፤ ለኒህ ሁሉ ምግብ ሰጥቶ ደስ የሚያሰ ኛቸው ። አንድም ፤ ምስኪናን የሚላቸው ሀብት ኃይል የሌላቸው ፤ ልህዋን የሚላቸው ሀብተ ጸጋ ኃይል ኑሯቸው በኃጢአት የተነሣቸው ናቸው ፤ ለምስኪናን በሃይማኖት እንዲሰጣቸው ፤ ለልህዋን በንስሐ እንዲመለስላቸው አድ ርጎ ደስ የሚያሰኛቸው ።

፳፬/ ወለእለ ጻመው በመስቀሉ ይባልህ ፤

፳፬/ ይባልህ በመስቀሉ ለእለ ጻመው በመስቀሉ ብለህ ግጠም ዘኢያረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ይጸመደኒ



www.ethiopianorthodox.org

ያለውን ይዘው መከራ የሚቀበሉትን የሚያድን ። አን ድም ባሕረ ገሃነምን በመስቀል ትርክዛው እየቀዘፈ የሚ ያሻግር የሚያወጣ ። እለ ውስተ ሲኦል ፃው ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሥቱ እንዲል ።

ዘኵሎ መዓተ ይመይጥ ወያሴስል እምኔነ ለእለ ቦቱ ተወከልነ ፤

ካመንበት ከእኛ መዓቱን ሁሉ የሚያጠፋ የሚያ ርቅ ። ሐተታ ፤ ይመይጥ ወያሴስል ማለቱ ግን ስለ ጊዜው ስለ ዘለዓለሙ ። አንድም ፤ ስለ ነፍስ ስለ ሥጋ ፤ አንድም ፤ መዓተ እግዚአብሔር ፤ መዓተ ንጉሥ ፤ መዓተ አርዌ አለ ። መዓተ **እግዚ**አብሔር ፤ ወኃደገ ኵሎ መዓተከ ያለው ፤ መዓተ ንጉሥ ወተምዓ ሄሮድስ ላዕለ ሰብአ ጢሮስ ወሲዶና ያለው ፤ መዓተ አርዌ ወተምዓ ውእቱ አርዌ ለይእቲ ብእሲት ወተለወ ድኅሬሃ ያለው ነው ።

፳፯/ ዘነቢያት ወሐዋርያት አእኰቱከ በኅቡዕ ፤

፳፯/ ነቢያት ሐዋርያት በደብረ ታቦር ያመሰገኑህ ሐተታ ። ኅቡዕ ምሥጢር ስለተገለጸበት ደብረ ታቦርን ኅቡዕ አለው ። አንድም ነቢያት ሐዋርያት በልቡና ፤ ያመሰገኑህ ኅቡዕ የተመቸ ።

ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ ፤

አቤቱ አንተን እናመሰግን'ኻለን ።

ወንሴብሖከ ፤

ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።



ከመ ለቢወነ ብከ ናዕርፍ በማኅደረ ሕይወት ፤

ለቢወነ ኪያከ ብለህ ግጠም አንተን ዐውቀን በመ ንግሥተ ሰማይ እንኖር ዘንድ ። አንድም ባንተ አውራሽ ነት በመንግሥተ ሰማያት እንኖር ዘንድ ።

እንዘ ንገብር ፈቃደከ ሀበነ ንሑር በትእዛዝከ ፤

በአሠርቱ ቃላት ጸንተን በወንጌል ትእዛዝ እንኖር ዘንድ መኖሩን ስጠን ። አንድም ፤ በወንጌል ጸንተን በሌ ላው ትእዛዝ እንኖር ዘንድ መኖሩን ስጠን ።

፳፰/ ወኵሎ እግዚኦ በምሕረትከ ሐውጽ ፤

፳፰/ ሁሉን በቸርነትህ ጐብኝ ።

ንዑሳነ ወዓቢያነ ፤

ንዑሳኑን ዓቢያኑን በቸርነትህ ጐብኝ ።

መኰንነ ወሕዝቦ ኖላዌ ወመርዔቶ ፤

ንዑሳን ያላቸውን ሕዝቦ መርዔቶ ዐቢያን ያላቸውን መኰንነ ወኖላዌ አላቸው ። ንጉሡን ሠራዊቱን ኤጲስ ቆጶሱን ማኅበሩን ጠብቅ ።

እስመ ዚአከ መንግሥት ቡሩክ እግዚኦ አምላክነ ፤

አቤቱ ፈጣሪያችን ክቡር መንግሥት ያንተ ገንዘብ ነውና ።

፳፱/ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፤
እምቅድመ ዓለም ።

፳፱/ ዓለም ሳይፈጠር ለሥላሴ ምስጋና የባሕርያቸው ነው ። እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ ኢተጸርዓ

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አላ ምሉ
ውስተ ኵሉ እንዲል ።

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ለዓለም ወለትውልደ ትውልድ ፤

ይእዜኒ ያለውን ትውልድ ወዘልፈኒ ያለውን ትው
ልደ ትውልድ አለው ።

ዘኢየኃልቅ ።

ትውልድ ዘኢየኃልቅ ፤ ስብሐት ዘኢየኃልቅ ብለሀ
ግጠም ፤ ትውልድ ዘኢየኃልቅ አለ እስከ ዕለተ ምጽአት
ሲደረግ ይኖራልና ፤ ስብሐት ዘኢየኃልቅ የማይፈጸም
ምስጋና ።

ለዓለመ ዓለም አሜን ፤

እንዳለፈው ነው ።

# ኪዳን ዘነግህ

## ምዕራፍ ፪

፩/ ይካ ፤ ይበል ካህን ።

ጸጋ ዘእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ ፤

፩/ ሀብተ ውልድና ፤ ሕይወተ ልቡና ፤ ሥርየተ ኃጢ
አት ፤ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ፤ ተስፋ መንግሥተ
ሰማያት ይደረግላችሁ ።

ይሕ ፤ ይበሉ ሕዝብ ፤ ምስለ መንፈስከ ፤

እንደ ቃልህ ይሁንልን ወብነ አሐዱ መንፈስ ዘሃ
ይማኖት እንዲል ። አንድም ቢመርቃቸው ይመርቁታል
ብሎ ከአንተ ጋራ ባለመለያየት ይደረግልን ። አንድም
ባንተ ያለ መንፈስ ቅዱስ ይደርብን ።

ይካ ፤ ይበል ካህን ንሰብሖ ለአምላክነ ፤

ፈጣሪያችንን እናመስግነው ይበል

ይሕ ይበሉ ሕዝብ

ርቱዕ ይደሉ ፤

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው ።

ይካ ፤ አጽንዑ ሐሊና ልብክሙ ፤

ልቡናችሁን በሃይማኖት ሐሊናችሁን በአንክሮ ፣ በተ
ዘክሮ አጽኑ ይበል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይሕ ይበሉ ሕዝብ ።

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት ፫ ጊዜ

ልቡናችንን በሃይማኖት ፤ ሕሊናችንን በአንክሮ በተዘክሮ ብናጸና ከእግዚአብሔር ጋራ አንድነት አለንና ።

ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ፤

ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ወደ መከራ ወደ ገሃነም አታግባን ። አንድም ፡ የላይ ቤት አብነት ፥ ሥጋህን ደምህን ሳንበቃ በድፍረት ከመቀበል አድነን መንሱትኬ ነሢአ ሥጋሁ በድፍረት ወተመጥዎተ ደሙ ዘእንበለ ኃፍረት እንዘቦ ላዕሌሁ ነውረ ኃጢአት እንዲል ። ምሳሌ ሦስት መሆኑ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ ያንድነት ምሳሌ ነው ።

፩/ ይካ እግዚአብሔር አብ ወሀቤ ብርሃን ፤

፪/ ረቂቁን ብርሃን የሰጠ ግዙፉን ብርሃን የፈጠረ

ዘለኵሉ ኃይል ፤

ለሁሉ ኃይል ጽንዕ የሚሆን

ወለኵሉ ነፍስ ሐዋጺ ፤

ሰውን ሁሉ በረድኤት የሚጐበኝ ፤ እግዚአብሔር ሐወጸ እምሰማይ እንዲል ። አንድም ፡ የሰውን ልቡና መርምሮ የሚያውቅ ፤ ሐወጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ እንዲል ። አንድም ፡ የሕዝብን የአሕዛብን ሥጋ የተወሐደ ወምንትኑ እጓለ እመሕያው ከመ ተውጾ እንዲል ።



፫/ ብርሃን ዘእምቅድም ዓለመ ሐታሚ ፤

፫/ ቅድመ ዓለም የነበረ ባሕርይ ።

ይህን ዓለም በሰባት ክፍል የወሰነ ወኃተምኩኪ በስብአቱ ማኅተም እንዲል ። አንድም ፤ ይህን ዓለም የሚያሳልፍ ፤ ወገጸ ከዋክብት የኃትም እንዲል ። አንድም ይህን ዓለም በኅልፈት የሚሠውር ፤ ኅትም ወኢትጽሐፍ እንዲል ። አንድም ዓለመ ሥጋን ራሱን ያስመሰለ ። እስመ ለዝሰ እግዚአብሔር አብ ኃተሞ ወበከመ የኃትሙ እለ የኃትሙ መዓረ ግራ በማኅተመ ወርቅ እንዲል ።

መራሒ ሕይወት ፤

ሕይወትን ወደሰው ፤ ሰውን ወደ ሕይወት መርቶ የሚያደርስ ።

ወበቋዒ ተድላ ዘኢይመውት ፤

የማያልፈውን ተድላ መንግሥተ ሰማያትን የሚሰጥ አንድም በመስጠት የሚረባ የሚጠቅም

ዘአውጻእከነ እምዕቅፍተ ጽልመት ፤

ከጨለማ መሰናክል አውጥተህ ።

ወብርሃነ ዘኢይትረከብ ጸገከነ ፤

የማይገኝ ብርሃንን የሰጠኸን ሐተታ ዘኢይትረከብ አለ ፤ በሌሊት ፀሐይ የለምና ። አንድም ከድንቁርና አውጥተህ ዕውቀትን የገለጽህልን ፡ ሐተታ ፤ ዘኢይትረከብ አለ ፤ በአብዳን ዘንድ ዕውቀት አይገኝምና ። አንድም ከክህደት አውጥተህ ሃይማኖትን የገለጽኸልን ።

www.ethiopianorthodox.org

ሐተታ ፡ ዘኢይትረከብ አለ በመናፍቃን ዘንድ ሃይማኖት አይገኝምና ። አንድም ፡ ከሲኦል አውጥተህ ገነትን ፡ ከገሃ ነም አውጥተህ መንግሥተ ሰማያትን ያወረስከን ። ሐተታ ፡ ዘኢይትረከብ አለ ፤ በኃጥአን ዘንድ አይገኝምና ።

፬/ ዘእማዕሠር ለእለ የእምኑ ብከ ፤

፬/ ያመንብህ እኛን ከማዕሠረ ክህደት አውጥተህ በሃይማኖት ከለልከን ።

በሃይማኖት ያከበርከን ሐተታ ፡ ይህ ቅሉ ክብር ነውና። አንድም ፡ በሃይማኖት ከለልከነ በሃይማኖት በሚገኝ ክብር ያከበርከን ።

ዘኢይርኅቅ እምአግብርቲሁ ወትረ ዘምስሌሆሙ ይሄሉ ፤

በምእመናን አድሮባቸው ይኖራል እንጂ የማይለያ ቸው ። ትሄሉ ይላል የማትለያቸው ። ዝንቱ ፀሐይ ብለህ ጨርስ ።

ዘኢይጸመም ለዘበፍርሃት ወበረዓድ ትስእሎ ነፍስ ፤

በፍርሃት በረዓድ ሁና የምትለምነውን ሰውነት ቸል የማ ይል ። ቸልም ቢል ተላጽቆተ ስኢል እስኪያስደርገው ድረስ ነው እንጂ ቸል እንዳለ አይቀርምና ። ያረምም ከመ ዘኢይሰምዕ ያገኀዲ ከመ ዘኢይሁብ እንዲል ።

፭/ እምቅድመ ሕሊና ኵሎ የአምር ፤

፭/ የሚታሰበውን ከመታሰቡ አስቀድሞ የሚያውቅ ውእቱሰ የአምር ሕሊና ሰብእ እምቅድመ ኩነታ እንዲል



ወእምቅድመ ሕሊና ይፈትን ፤

የሚደረገውን ከመደረጉ አስቀድሞ የሚያውቅ እም ቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ እንዲል ።

ወዘእንበለ ንስአሎ ይሁብ ፍትወተነ ዘእምፈቃዱ ፤

ሳንለምነው የምንሻውን አውቆ ወዶ የሚሰጠን ፤ ሐተታ ነቢይ ክሥት ለእግዚአብሔር ፍኖተከ ፤ ሐዋር ያም ወእንዘ ተአዝዝ ክሥቱ ስእለተክሙ ቅድመ እግ ዚአብሔር ይላል ። ጌታ ከዚህ እንዲህ አለ ። የአግብር ትና የጌታ ቃል ተለያየሳ አይጣላምን ቢሉ አይጣላም ። አዲስ አማኒ ባመነ ጊዜ እንዲህ ብዬ ብለምን እንዲህ ያለ ነገር ተደረገልኝ ብሎ ሃይማኖቱ እንዲጸናለት የእግዚአብ ሔር ቸርነቱ እንዲታወቅ ነው እንጂ ነገር እንደጌታ ነው ።

፮/ ወይሰምዓነ እለ እንበለ ኑፋቄ ንጼውዖ ፤

፮/ እናገኝ እናጣ ሳንል የምንለምነውን የሚሰጠን

ዘኢይትነገር ብርሃን ፤

የማይመረመር ባሕርይ ።

ንጉሠ ሠራዊተ ሰማያት ፤

በሦስቱ ሰማያት ያሉ የመላእክት ገገ ። አንድም ፡ አለቆች ያሏቸው የሠራዊተ መላእክት ገገ ።

ሰማዒ ስብሐተ ማኅሌት ዘሊቃነ መላእክት ዘዲ ቤሆሙ የዓርፍ ።

አድሮባቸው የሚኖር ሊቃነ መላእክት ያቀረቡትን ምስጋና የሚቀበል ። አንድም ፡ ወዘዲቤሆሙ የአርፍ ሲል ነው አድሮባቸው የሚኖር ።

www.ethiopianorthodox.org

ስምዓነ ንስእለከ እግዚኦ ፤

እንለምንሃለንና አቤቱ ልመናችንን ስማን ፤

፯/ ሀበነ በትውክልት ቃለ ዘኢያረምም ፤

፯/ በሃይማኖት አርምሞ ጽርዓት የሌለበትን ቃል ግለጽልን ።

ኪያከ ንሰብሕ ፤

አንተን እናመሰግን ዘንድ ።

ኪያከ ነአኵት ፤

አንተን እንወድ ዘንድ ።

ወኪያከ ንባርክ ፤

አንተን እናከብር ዘንድ ።

ወከመ ብከ ንፀወን ፤

ባንተ አምነን ጸንተን እንኖር ዘንድ ሀበነ ብለህ እሠር ። ንሴብሐከ ማንሻ ። አንድም ፡ ንሕነ አግብርቲከ ንሴብሐከ እግዚኦ ፤ እንዳለፈው ፤ ይሕ ፤ ይበሉ ሕዝብ ።

፰/ ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ ፤

፰/ አንተን እናመሰግናለን ይበሉ ።

ይካ ይበል ካህን ።

፱/ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰምዓነ ቅዱስ ፤

፱/ አቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ቁርጽ ልመናችንን ስማን ። ሰማዕከነ እግዚኦ ብሎ አቤቱ ቁርጽ ልመናችንን ሰማኸን ።



ለበሐማን ኮኖሙ ቃለ ፤

በሐማን ሥጋን በተአምራት ፤ በሐማን ነፍስን በትምህርት እንዲናገሩ አደረጋቸው ። አንድም አደረግኻቸው

ለስቡራን ምርጉዘ ፤

ስቡራን ሥጋን በተአምራት ፡ ስቡራን ነፍስን በትምህርት እንዲሄዱ አደረጋቸው ፤ አንድም ፡ አደረግኻቸው

ለዕውራን ብርሃነ ።

ዕውራን ሥጋን በተአምራት ፤ ዕውራን ነፍስን በትምህርት እንዲያዩ አደረጋቸው ፤ አንድም ፤ አደረግኻቸው

ወለሐንካሳን ፍኖተ ፤

ሐንካሳን ሥጋን በተአምራት ፤ ሐንካሳን ነፍስን በትምህርት እንዲሄዱ አደረጋቸው ፤ አንድም ፤ አደረግኻቸው ።

ወለዘለምፅ መንጽሒ ፤

ልሙፃን ሥጋን በተአምራት ፤ ልሙፃን ነፍስን በትምህርት እንዲድኑ አደረጋቸው ፤ አንድም ፤ አደረግኻቸው

እኁዛተ ሕማማት እግዚእ ፈወስከ ፤

በጽኑዕ ደዌ የተያዙትን ፤ አንድም ፤ ደዌ የጸናባቸውን አዳንክ ።

ለጽሙማን መፈውስ ፤

ጽሙማን ሥጋን በተአምራት ፤ ጽሙማን ነፍስን በትምህርት እንዲሰሙ አደረጋቸው ፤ አንድም ፤ አደረግኻቸው ።

፲/ ለሞት ዘለፎ ፤

፲/ ሞትን ዘለፈው ።

www.ethiopianorthodox.org

ወለጽልመት ሣቀየ ፤

ጨለማን ሣቀየው በቁሙ ። አንድም ፤ ዲያብሎስን በግብሩ ሞት ጽልመት አለው ። ብሎ በዲያብሎስ ፍዳ አጸናበት ።

ዘገብረ ብርሃነ ፤

ለይኩን ብርሃን ብሎ የኅሁን ብርሃን የፈጠረ ።

፲፩/ ፀሐይ ዘኢየዓርብ ፤

፲፩/ ኅልፈት ጥፋት የሌለበት ፀሐይ ።

ወማኅቶት ዘኢይጠፍዕ ፤

የማይጠፋ ፋና ፥ ሐተታ ፥ ከዚህ ዓለም ፀሐይ ከዚህ ዓለም ማኅቶት ሲለየው ነው ፤ የዚህ ዓለም ፀሐይ የዚህ ዓለም ማኅቶት ጠፈር ደፈር ይከለክለዋል ኅልፈት ውላጤ ይስማማዋል ጨለማ ይፈራረቀዋል በሱ ግን ይህ ሁሉ የለበትምና ፤ እስመ ፀዳለ ብርሃን ዘእምውስቴቱ ይሠርቅ ወኢየዓርብ ወኢይትኃባዕ እስመ ጽልመትኒ ኢይጸልም በኀቤከ ወአልቦ ጽልመት ውስተ መክፈልታቲሁ እንዲል።

ምሳሌ ፤ ፀሐይ ማኅቶት እንደ ሰውነቱ ፥ ኢየዓርብ ኢይጠፍዕ እንደ አምላክነቱ ።

ፀሐይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን ፤

በቅዱሳን አድሮ ዘወትር ዕውቀትን የሚገልጽ ።

፲፪/ ወኵሎ ተከለ ለሠርጐ ዓለም በሥምረት እቁም፤

፲፪/ በዙና ይኑሱ ፥ አኑሱና ይብዙ ባለማለት በተወ



ሰነ ቁርጽ ፈቃድ ለዓለም ገጽ ሁሉን የፈጠረ አስረጅ ለሰማይ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት መላእክትን ፥ ለምድር ዕፀው አዕባን እንስሳት አራዊት ሰውን ፥ ለአካል ሕዋሳ ትን ፥ ለልቡና መዓርጋትን ፤ ለመምህራን አርድእትን ፥ ለቤተ ክርስቲያን ምዕመንን ነው ።

፲፫/ ገሃደ ለኵሉ ሠረቀ ለሰብእ ፤

፲፫/ ሰውን ለማዳን በኋላ በተረዳ ነገር ሰው ሆንኽ ፤ ለና ለ አንድ ወገን ነው ።

መድኃኒተ መያጢሃ ለነፍስ ፤

መድኃኒት ሁነህ ነፍስን የመለስኽት ።

ወኵሎ በዘይደሉ አቅደምከ ሐልዮ ፤

ሁሉን እንደሚገባ አስቀድመህ አውቀህ ፈጥረኽልና።

ገባሬ መላእክት ፤

መላእክትን የፈጠርህ

አበ ኵሉ ፤

የሁሉ ፈጣሪ ።

ሠርጎ ዓለም ፤

የዓለም ጌጽ አንድም ኵሉን ለሠርጉ ቀጽል ። የዓለም ጌጽ ሁሉ ። አንድም አበ ሠርጎ ዓለም ኵሎ ፤ የዓለም ሁሉ ጌጽ ፈጣሪ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ማራሪሃ ለምድር ፤

ምድርን የፈጠርኻት አንድም ያጸናኻት ።

፲፬/ ጥበብ ወአእምሮ እምአብ ዘሀሎ እምቅድም ውስተ ዓለም ተፈነወ ፤

፲፬/ ጥበብ ወአእምሮ ዘሀሎ እምቅድም እምአብ ውስተ ዓለም ተፈነወ ብለህ ግጠም ፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ጥበብ አእምሮ ወልድ ከአብ አንድነት ሳይለይ ወደዚህ ዓለም መጣ

ዝሀሉና ዘኢይትነሠት ወዘኢይተረጐም ፤

ይህ አናዋር የማይለወጥ የማይናወጥ የማይመረመር ነው

መንፈስ ዘኢያስተርኢ ፤

የማይመረመር አንድም ረቂቅ መለኮት ነው ።

፲፭/ ዜናዊ ስቡሕ አንተ ፤

፲፭/ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ብለህ የተናገርህ ምስጉን መምህር ነህ ።

ወመንክር ስምዕከ ፤

ለዚህም ምስክርህ ተአምራትህ ነው ። እስመ ስምዐ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዲል ፣ ሐተታ ፣ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ያለውን በሥራው ለማስረዳት በደረቅ ግንባር ዓይንን ፈጥሯልና ። አንድም አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ ብለህ የተናገርህ ምስጉን መምህር



ነህ ለዚህም ምስክርህ ተአምራትህ ነው ። እስመ ስምዓ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዲል ፣ ሐተታ ። አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ ያለውን በሥራው ለማስረዳት ያራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን አስነሥቷልና አንድም ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ አነ በአብ ወአብ ብየ ብለህ የተናገርህ ምስጉን መምር ነህ ለዚህም ምስክርህ ተአምራትህ ነው ። እስመ ስምዓ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዲል ። ሐተታ ፣ ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ አነ በአብ ወአብ ብየ ያለውን በሥራው ለማስረዳት ጉሕቀትን መፃጉዕን አድኑዋልና ። አንድም ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ አነ በአብ ወአብ ብየ ብለህ የተናገርህ ምስጉን መምህር ነህ ። ስምከ ብሎ ስምህም ድንቅ ነው እስመ ኢሳይያስ ሰመዮ መንክረ ስምየኒ መንክር ወመድምም ውእቱ እንዲል ።

ወበእንተ ዝንቱ ንሕነ አግብርቲከ ንዌድሰከ እግዚኦ ፤

ስለዚህ እኛ ቤተ ሰቦችህ እናመሰግንኻለን ።

፲፮/ ይሕ ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ ፤ እንዳለፈው ።

፲፯/ ይካ ፤ ንሤልስ ለከ ዘንተ ቅዱስ ስብሐተ ዘወሀብከነ ዚአከ ሃይማኖተ ዘኢይትነሠት ፤

፲፯/ የማይለወጥ ያንተን ሃይማኖት የገለጽህልን አንድም ያስተማርኸን ይህን ክቡር ምስጋና ላንተ እና ቀርባለን ።

ወቦቱ ገበርከ ለነ ንማዕ ማዕሠሪሁ ለሞት ፤

ሞተ ነፍስ የሚያስፈርድ ክህደትን በሃይማኖት ድል እንነሣ ዘንድ ድል መንሣቱን የሰጠኸን ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘፈጠርከ ሕሊናተ ርቱዓተ ለእለ የአምኑ ብከ ከመ እምሰብእ ይኩኑ አማልክተ ፤

ላመኑብህ ለመምህራን ቅን ልቡናን የፈጠርኽ ፤ ከሰው ወገን አማልክት ይባሉ ዘንድ ። አንድም ላመኑ ብህ ለምእመናን ቅኖች መምህራንን የፈጠርህ ፤ ከሰው ተለይተው አማልክት ይባሉ ዘንድ ።

፲፰/ ዘወሀብከነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላኢ ፤

፲፰/ በልቡና ፍትወታት እኩያት ኃጣውእን ድል እንነሣ ዘንድ ድል መንሣቱን የሰጠኸን ። አንድም በ ፤ በ ግዕዝ የገባ ነው ፤ አሪት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ እንዲል ። ሊቃነ አጋንንትን ሠራዊተ አጋንንትን ድል እንነሣ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን የሰጠኸን ።

ከመ ንፍታሕ ዘኢይትፈታሕ ፤

ምድራውያን ነገሥታት የማይፈቱትን እንፈታ ዘንድ ሌዋውያን ካህናት አያስተሰርዩት የነበረው ውስ ጣዊ ኃጢአትን እናስተሠርይ ዘንድ ።

ፍቅረ ለነ ኀበ አቡከ ገብርከ ወዓረቀ ማዕከሌነ ፤

አምላክ ወሰብእ ሁነህ ካባትህ ጋር ያስታረቅኸን አንድ ያደረግኸን ፤ ኅሩይ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ እንዲል ።

፲፱/ ስማዕ እግዚኦ እለ ኪያከ ይስእሉ ፤

፲፱/ አቤቱ የሚለምኑህን ስማቸው ።



እግዚኦ እለ ዘንስእለከ ኢንስተት ፤

አቤቱ የምለምንህ እኛ እንካሰስ እንጠቃ ።

አላ በስክየት ዲበ ጸላኢነ ሀሉ ፤

በመክሰስ በመጠቃት ጊዜ በጠላታችን ላይ ኑርበት እንጂ ። አኑርበት እንጂ ። አንድም ዲበ ጸላኢ ነሃሉ ይላል ። በጠላታችን ላይ ሰልጥነንበት እንኑር እንጂ ።

ሀበነ ዘወትር ጸሎተነ ፤

አስበ ጸሎታችንን ስጠን አንድም አብዝተን እንድ ንጸልይ አድርገን ።

እምሒጠተ ጸላኢ ንትዐቀብ ፤

ከጠላታችን ከዲያብሎስ ማታለል እንጠበቅ ዘንድ።

፳/ ስማዕ ዘለዓለም ንጉሥ ፤

፳/የማታልፍ ንጉሥ ልመናችንን ስማን፤ሐተታ፡ከዚህ ዓለም ንጉሥ ሲለየው ነው ፤ የዚህ ዓለም ንጉሥ አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ ነው ፤ እሱ ግን ቅድመ ዓለም ማዕከለ ዓለም ድኅረ ዓለም ንጉሥ ነውና ።

መዓስበ ናዝዝ ፤

ባሏ ሞቶባት ቤት የሚሠራ ዘር የሚዘራ የሌላትን ቤት የሚሠራ ዘር የሚዘራ ስጥተህ ደስ አሰኝ ።

እጓለማውታ ተወከፍ ፤

አባት የሞቱበትን የድኃውን ልጅ ምግብ ልብስ ሰጥተህ በረድኤት ተቀበል አንድም ፤ ከጉባኤ አሪት ከሃይማኖተ አሪት የወጣውን ጉባኤ አሪትን ሃይማኖተ አሪትን በመግለጽ ደስ አሰኝ ከጉባኤ ወንጌል ከሃይማ



www.ethiopianorthodox.org

ኖተ ወንጌል የወጣውን ጉባኤ ወንጌልን በመስጠት ሃይ ማኖተ ወንጌልን በመግለጥ ተቀበል ።

፳፩/ ሲሩያነ በምሕረትከ አንጽሕ ፤

፳፩/ ልብስ በደም ጸምር በቀለም እንዲታለል በኃጢ አት የታለሉትን በቸርነትህ አንፃ ።

ዓብዳነ አጥብብ ፤

ሰነፎችን አለብም ።

ወኀጉላነ ሚጥ ፤

ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ሂደው የተጎዱትን ወደ ጽድቅ ወደ ሃይማኖት መልስ ።

እለ ውስተ ሞቅሕ አድኅን ፤

በግዞት ያሉትን አድናቸው ። አንድም በግፍ የታሠ ሩትን አድናቸው ።

፳፪/ ወለኵልነ ኩን ፀወነ ፤

፳፪/ ለሁላችን አምባ መጸጊያ ሁነን ።

እስመ ለከ እግዚኦ አምላክነ መንግሥት ቡሩክ

አቤቱ ፈጣሪያችን ክቡር መንግሥት ያንተ ገንዘብ ነውና ።

ይ ሕ ፤ እንዳለፈው ።

አሜን ፤ እንዳለፈው ።

# ኪዳን ዘሠርክ

## ምዕራፍ ፫ ።

፩/ ይ ካ ፤ ይበል ካህን ።

ጸጋሁ ለእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ ።

እንዳለፈው ።

ይ ሕ ፤ እንዳለፈው ።

ምስለ መንፈስከ ፤ እንዳለፈው ።

ይ ካ ፤ አእኵትዎ ለአምላክነ ፤ እንዳለፈው ።

ይ ሕ ፤ ርቱዕ ይደሉ ፤ እንዳለፈው ።

ይ ካ ፤ ይበል ካህን ።

፪/ ለከ ለአብ ዘኢይማስን ፤

፪/ እስከ አሁን የወልድን ሲናገር መጥቶ ነበር ። እንግዲህ ወዲህ የአብን ነገር ይናገራል ። የማትለወጥ አንተን አብን ።

መድኃኔ ነፍስነ ፤

የነፍሳችን መድኃኒት የምትሆን አንተን አብን ።

፫/ ወመሠረተ ጥበባት ፤

፫/ የጥበባት የሕግጋት መገኛ ። አንድም ፣ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ መገኛ ። አንድም ፣ ያንድነት የሦስት ነት መገኛ የምትሆን አንተን አብን ።

www.ethiopianorthodox.org

ዓቃቤ አልባቢነ ፤

ልቡናችን ያሰበውን መርምረህ የምታውቅ አንተን አብን ።

ዘአንተ ውስጥ ዓይነነ አብራህከ ፤

ውሳጣዊ አእምሯችንን ብሩህ ያደረግህልን ። ወብነ ክ፪ቲ አዕይንት ውሳጣውያት ሀየንተ አዕይንት ሥጋ ውያት አሐቲ ዓይነ ሕሊና ወአሐቲ ዓይነ ነፍስ እንዲል ።

፬/ ወጽልመተ ሕሊናነ በዘዚአከ አእምሮ ከለልከነ አንተ

፬/ የሕሊናችንን ድንቊርና አርቀህ ካንተ በሚገኝ ዕውቀት ያከበርኸን ።

ዘተውህበ ለሙስና ዘትካት ብእሴ አድኃንከ ፤

ለጥፋት የተሰጠ የቀደመ ሰው አዳምን ያዳንከ

በመስቀሉ ለዋሕድከ ፤

በልጅህ መስቀል ። አንድም ፥ በልጅህ መሰቀል

ወሐደስኮ በዘኢይማስን ፤

አዳምን በዘኢይማስን መንፈስ ቅዱስ በዘኢይማስ ንነት ያደስከው ።

፭/ ዘስሕተታት በጠላ በትእዛዝከ ፤

፭/ ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኃን ባልኸው ። አን ድም ፥ ኵሉ ዘቦአ ውስተ አፍ ኢያረኵሶ ለሰብእ ባል ኸው ትእዛዝህ ፤ ኢትልክፍ ኢትጥዓም ያለፉ ። አንድም ፥ ዘበስሕተት በጠለ ይላል አብነት ። በስሕተት የተጎዳ አዳምን በዘኢይማስንነት ። አንድም ፥ በዘኢይማስን መን



ፈስ ቅዱስ ያደስኸው ፤ በትእዛዝከ ፤ ውረድ ተወለድ ተሰ ቀል ሙት ባልኸው ትእዛዝ ።

፮/ ወበሞተ ወልድከ ቤዘውከ ፤

፮/ በልጅህ ሞት ያዳንህ ።

ወዘተገድፈ ኃሠሥከ ፤

ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ተለይቶ የጠፋ አዳ ምን በልጅህ ህልው ሁነህ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የፈለግህ አንተን አብን ።

ወበእንተ ዝንቱ ንሕነ አግብርቲከ ንሴብሐከ እግዚአ

አቤቱ ስለዚህ እኛ ባለሟሎችህ እናመሰግንሃለን ።

ይ ሕ ፤ እንዳለፈው ።

ንሴብሐከ እግዚአ ፤ እንዳለፈው ።

ይ ካ እንዳለፈው ።

፯/ ንዌድሰከ እግዚአ ዘወትረ ይሴብሑ ስብሐተ ማኅሌት ዘሊቃነ መላእክት በኢየርምሞ እንበለ ዕረፍት ውዳሴ ስብሐት ፤

፯/ ሳናቋርጥ አርምሞ ጽርዓት በሌለበት ቃል ሊቃነ መላእክት ለሚያመሰግኑህ ላንተ ከምስጋና የሚቀድም ምስጋናን እናቀርባለን ። ሐተታ ፥ መላእክት ተናግረው ታል ቢሉ የተመቸ ፤ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ተናግረውታል ቢሉ ከምስጋና ቀጥሎ የሚሆን ምስጋና እናቀርባለን ። ከስብሐተ ሙሴ ከማኅሌተ ዲቦራ በኋላ ነውና ። አን ድም ፥ ከምስጋና የሚበልጥ ምስጋና እናቀርባለን ።ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትምና ።

www.ethiopianorthodox.org

ወአኰቴት ዘአጋዕዝት ፤

ያውም አጋዕዝት የሚያቀርቡት ምስጋና ነው ። ሐተታ ፣ ሠራዊተ ዲያብሎስ የነበሩ ከሠራዊተ ሚካኤል ተደርበዋልና ።

፰/ በማኅልይ ይሴብሑከ እግዚኦ ዘፈኖከ ምክረከ ፤

፰/ አቤቱ ያንተን ምክር ወልድን በሥጋ የላከኸው በቃል በልቡና ያመሰግኑኻል ።

ዚአከ ቃለ ፤

ያንተን ቃል ወልድን ።

ዚአከ ጥበበ ፤

ያንተን ጥበብ ወልድን ።

ወዚአከ ሕዋጼ ፤

ያንተን መጐብኘት ወልድን በሥጋ የላከኸው ።

ዘሀሎ ምስሌከ እምቅድም ፤

ዓለም ሳይፈጠር ካንተ ጋራ እንዳንተ በጌትነት የነበረ፤

ዓለም እንበለ ይትገበር ዘኢተገብረ ፤

ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ( ያልተፈጠረ ) ። ሐተታ አርዮስ ፈጥሮ ፈጠረበት ይላልና ። አንድም ፣ አሁን ዘተ ርእየ በሥጋ የሚል ነውና በባሕርዩ ያልተፈጠረ ።

፱/ ቃል ዘተርእየ በሥጋ ለመድኃኒተ ትዝምደ ሰብእ፤

፱/ ባሕርየ ሰብእን ለማዳን በሥጋ የተገለጸ አካላዊ ቃል ።



ወልድከ ወፍቁርከ እግዚእነ ኢየሱስ ፤

ልጅህ ወዳጅህ ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ዘአግአዘነ እምአርዑተ ኃጢአት ፤

በኃጢአት ከመጣ ፍዳ ነፃ ያደረገን ።

ወበእንተ ዝንቱ ንሕነ አግብርቲከ ንዌድሰከ እግዚኦ እንዳለፈው ።

፲/ ይ ሕ ፤ ንዌድሰከ እግዚኦ ፤ እንዳለፈው ።

፲፩/ ይ ካ ፤ ለከ ዘእምልብነ ውዳሴ ንሜልስ ፤

፲፩/ ዐውቀን ሦስተኛ ለአንተ ምስጋናን እናቀርባ ለን ። ወህየንተ ልብ ዘዝየ ነአምሮ ለአብ ከመ ልብ ውእቱ ። ወህየንተ ቃል ዘዝየ ነአምሮ ለወልድ ከመ ቃል ውእቱ ። ወህየንተ እስትንፋስ ዘዝየ ነአምሮ ለመንፈስ ቅዱስ ከመ እስትንፋስ ውእቱ እንዲል ።

፲፪/ ወሀቤ ሕይወት እግዚኦ ፤

፲፪/ ሕይወት ሥጋዊን ሕይወት መንፈሳዊን የሚ ሰጥ ። አንድም ፤ ደማዊት ነፍስን ነባቢት ነፍስን የፈጠረ ያዋሐደ ። ሐተታ ፤ ከዕፀው ከአዕባን ለይቶ እንስሳትን አራዊትን በደማዊት ነፍስ አክብሯል ከእንስሳት ከአ ራዊት ለይቶ ሰውን በነባቢት ነፍስ አክብሯልና ።

ሐዋፂ ነፍስ ትሑታን ፤

ሐዋፂም ይላል ። የትሑታንን ሰውነት በረድኤት የሚጐበኝ ። እንዳለፈው ። አንድም ፣ ትሑታን ያሰቡትን መርምሮ የሚያውቅ ጥቅስ እንዳለፈው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫/ መንፈሰ ምንዱበ ኢተሐየየ ፤

፲፫/ የተቸገረውን ሰውነት ቸል የማይል ። እንዳ ለፈው ።

ዘይትዌከፎሙ ለእለ ይሰደዱ ፤

ከዘመድ ባዳ ። ከሀገር ምድረ በዳ ብለው አገራቸ ውን ጥለው በሰው ሀገር የሚኖሩትን በረድኤት የሚቀበል።

ረዳኢ ፤

ትርጓሜው ሥጋዊውን ትቶ እንዳለፈው ነው ።

ወለእለ ውስተ ሠርም ይትመነደቡ መድኅን ፤

እንደ ሰማዕታት በመከራ ያሉትን የሚያድን ።

ለርኁባን ዘይሄሊ ፤

ለርኁባነ ሥጋ በተአምራት ፤ ለርኁባነ ነፍስ በትም ህርት የሚያስብላቸው ።

ወይትቤቀል ለግፉዓን ፤

ለተበደሉ የሚፈርድላቸው ። እትቤቀል ላቲ እን ዲል ።

፲፬/ ዓርከ መሃይምናን ፤

፲፬/ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ወዳጅ ። አን ድም ፥ ምእመናን የሚወዱት ። አንድም ፥ ምእመናንን የሚወዳቸው ።

መስተናግር ለጻድቃን ፤

ምእመናን የሚመሰክሩለት ። ወእነግር ስምዓከ በቅ



ድመ ነገሥት ወኢይትኃፈር እንዲል ። አንድም ለምእ መናን መስክሮ ዋጋቸውን የሚሰጣቸው ።

ወማኅደር ለንጹሐን ፤

የንጹሐን ዓለማቸው የሚሆን ። ለሊሁ ዓለሞሙ ወለሊሁ ሀገሮሙ ወለሊሁ ተድላሆሙ ወለዓለም ውእቱ ርስቶሙ እንዲል ።

፲፭/ ወለእለ በጽድቅ ይጼውዕዎ ሰማዒ ፤

፲፭/ ይጼውዕዎ በጽድቅ ሰማዒ በጽድቅ ብለህ ግጠም ። በእውነት የሚለምኑትን በእውነት የሚሰማ በሐሰት የሚለምኑትን አይሰማምና ።

ለመበለት ከዳኒ ፤

ባልዋ ሙቶባት ቤት የሚሠራ ዘር የሚዘራ የሌላ ትን ቤት የሚሠራ ዘር የሚዘራ ሰጥቶ ከመከራ የሚሠውር ።

ወባላሂ ለዕጓለ ማውታ ፤

አባት እናት የሞቱበትን የድኃውን ልጅ ምግብ ልብስ ሰጥቶ ከመከራ የሚያድን የቀረው አይለወጥም።

፲፮/ ዘይሁብ መርሐ ርቱዓ ለቤተ ክርስቲያን ዘተ ከላ ላቲ ምዕራፈ ስብሐተ ሃይማኖት ፤

፲፮/ አምነው ለሚያቀርቡት ምስጋና ማረፊያ ማሳ ረፊያ ላደረጋት ለቤተ ክርስቲያን ቅን ሥዩማንን የሚሰጥ ።

ጉባዔ መንፈስ ፤

ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ ለምትሆን ።

www.ethiopianorthodox.org

ሀብተ ጸጋ ወኃይል ፤

ወሀቢተ ጸጋ ወኃይል ሲል ነው ። ጸጋን ኃይልን ለምታድል ። አንድም ፡ በሃይማኖት ለሚገኝ ክብር ማረፊያ ማሳረፊያ ላደረጋት ለምእመን ቅን መምህራንን የሚሰጥ ጉባዔ መንፈስ ጉብዕተ መንፈስ ሲል ነው ። ሀብተ ጸጋ ወኃይል ጸጋ ኃይል ሁኖ የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ለሰበሰባት ።

፲፯/ ለከ እንዘ ንዌድስ ኢናዕርፍ ለዝሉፉ ፤

፲፯/ አንተን ስናመሰግን ፈጽመን አናቋርጽም ። አንድም ወኢነዓርፍ ለዝሉፉ ፈጽመን ሳናቋርጥ ላንተ ምስጋና እናቀርባለን ።

በአልባቢነ ፡ ናስተማስል አምሳለ ምንግሥትከ ቦቱ ።

ቦቱና በ አንድ ወገን የጌትነትህን ነገር በልቡናችን እናውቃለን ። ወእንበይነዝ ንነሥእ መንግሥተ ዘተመሰለ እንዲል ።

በእንቲአከ ፤ አንተ ስለገለጽኸልን ።

ወበእንተ ፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ፤

ልጅህ ወዳጅህ ኢየሱስ ክርስቶስም ስለገለጻልን ። አንድም የጌትነትህ ነገር ቦቱ በመንፈስ ቅዱስ ነው እንላለን ። በእንቲአከ ያንተ ሕይወት ስለሆነ ወበእንተ ፍቁር ወልድከ የልጅህም ሕይወት ስለሆነ ፤ አንድም መንግሥት መንፈስ ቅዱስ ነው ። ወርኢኩ እፎ ትትከፈል መንግሥት በመዳልው እንዲል ። የመንፈስ ቅዱስ ነገር ብከ ባንተ ነው እንላለን ። በእንቲአከ ያንተ ነገር ነው እንላለን ። ወበእንተ ፍቁር ወልድከ የልጅህም ነገር በመንፈስ ቅዱስ ነው እንላለን ። አንድም አንተን በልብ ልጅህን በቃል መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ መስለን እንናገራለን ። አንድም ፡ ለከ ለአብ ያለውን ለአብ ንዌድስከ ያለውን ለወልድ ፤ ለከ ዘእምልብነ ያለውን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥተን እንናገራለን ።



፲፰/ ዘቦቱ ለከ ፤

ያለው ያለህ ፤ ያለህ ያለው ።

ስብሐት ወእኂዝ ለዓለመ ዓለም ፤

የማያልፍ ጌትነት ጽንዕ ያለው ። አንድም ያለህ ። እስመ አኃዚ ብሂል ሠራዒ ወወሳኔ ሐልዮታት እንዲል ።

ይ ሕ ፤ ይበሉ ሕዝብ ።

አሜን ፤ በእውነት ምስጋና አለው ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፤

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ።

ሣህሉ ወምሕረቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤

የሃሉ ምስለ ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ኅቡዓት

፩

በእንተ ትምህርተ ኅቡዓት ቅድመ ዘትትነገር እምጽርስ ፎራ ፤

ታሪክ ጌታ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያስተማረው ወንጌል ይባላል ፤ ከሞተ ተነሥቶ ያስተማረው ኪዳን ይባላል ፤ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያስተማረው ወንጌል መባሉ ስለ ምን ነው ቢሉ ፤ ወንጌል ማለት ብሥራት ማለት ነው ፤ ወንጌል ብሥራት ስብከት ቢል አንድ ወገን ነው ። ወንጌል ብሂል በልሳነ ጽርዕ ዘበትርጓሜሁ ስብከት እንዲል ። ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ወልደ እግዚአብሔር እንደነገሠ ዲያብሎስ እንደ ተሻረ አዳም እንደዳነ ትናገራለችና ስለዚህ ነው ። ከሞተ ተነሥቶ ያስተማረው ኪዳን መባሉ ስለምን ነው ቢሉ ፤ ደግ ነገር ነውና ። ደጉን ነገር ሁሉ ኪዳን ይለዋልና ። እብል እንከ ዝንቱ ኪዳን ዕኑዕ ዘእምኀበ እግዚአብሔር እንዲል ። ጳውሎስ ከዚህ እንዲህ ማለቱ አብርሃም ልጆቹ የጌታን ሃይማኖት ቢያጸኑ ሕጉን ቢጠብቁ ምድረ ርስትን እንዲያወርሳቸው ፤ ጌታና አብርሃም የተካያየዱበት ነው ። ይህም ኪዳን የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ነውና ። እመቦ ዘዓቀበ ቃለ ዝንቱ ኪዳን ይሄሉ ወየሐዩ ከመ መላእክት እንዲል ። አንድም ወንጌልን ኪዳን ይለዋል ኪዳንንም ወንጌል ይለዋል ። ኪዳንን ወንጌል ሲለው በሞቱ ለሞት ደምሰሶ ብሎ ለሐ

www.ethiopianorthodox.org

ዋርያት አስተምሮበታልና ። ወንጌልንም ኪዳን ሲለው እመቦ ዘዓቀበ ቃልየ ግብረ ዘአነ እገብር ውእቱሂ ይገ ብር ወዘየዓቢ እምኔሁ ይገብር ብሎ ከሐዋርያት ጋራ ተከያይዶበታልና ። ይህን ኪዳን ማን አስተምር ብሎት አስተማረ ቢሉ ቀድሞ ወንጌልን ሲያስተምር አስተምር ያለውን አለ ፤ ወንጌልን ሰውን እንዲረባ እንዲጠቀም ዐውቆ እንዳስተማረ ይህንንም ኪዳን ሰውን እንዲረባ እንዲጠቀም ዐውቆ አስተማረ ። አንድም ቊጥራቸው ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት የሚሆኑ ቤርዜሊ ቤር ዜላ ሜልቴዳ የሚባሉ ሦስት ሴቶች ጠይቀውት አስተ ምሯል ። አንድም ማርያም መግደላዊት ዐርጋለሁ ሲል ሰምታ ጠይቃው አስተምሯል ፤ አንድም ዮሐንስ ወንጌላዊ ጠይቆት አስተምሯል ፤ አንድም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በፊልጵስዩስ ኻያ አራት ኑኀ ፤ አሥራ ሁለት ግድም ቤተ ክርስቲያን ሥሩ የሚላቸው ነውና ። አንተ ዐርጋለሁ ካልኸ ቤተ ክርስቲያን በምን ትደር ብለው ጠይቀውት አስተምሯል ። ኻያ አራቱ የካህናተ ሰማይ ። አሥራ ሁለት የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ። አንድም በናቱ አርአያሆሙ ለነቢያት ይለዋል ብሎ የነቢያት ምሳሌ ። ይህንንም ጻፉት ብሎ ሦስቱን ባለመዋሎቹን አድርጎ እንድርያስን አግብቶ እንድርያስን አውጥቶ ማቴዎስን አግብቶ ያዕቆብን አውጥቶ ቶማስን አግብቶ አጽፎታል እነዚህም ከሁለት ከፍለውታል ። ፪ቱ ገበዋቲሃ ለመጽ ሐፍ እንዲል ። አንዱ በእንተ በእንተ እያለ የሚሄድ



ነው ሃምሳ ዘጠኝ አንቀጽ ይሆናል አንዱ እንዲያው ስድ ነው የሐሳዊ መሢሕን የምጽአትን ነገር ይናገራል ። ኋላም ቊጥራቸው ከ፸ አርድእት የሚሆኑ ዶስትዮስ ሞጊ ኖስ ሲላስ አቂላስ የሚባሉ አራት ሰዎች በ፬ቱ ማዕዘን ዞራችሁ አስተምሩት ብሏቸው ዞረው አስተምረውታ ልና ። የኋላ ሰዎች ግን ወንጌል በዛ ኪዳን በዛ ያንባብ ያን አንደበታቸው ይላሻል ዓይናቸው ይፈዛል የመተር ጕማን አንደበታቸው ይላሻል ልባቸው ይደክማል ። የሰ ማዕያን ጆሯቸው ይደነግዛል ብለው ከፍለውታል ። ከፈ ሉትማ እንዳንል የጌታ ቃል አጠረ ብሎ አያክሉበት አያስረዝሙት ፤ ረዘመ ብሎ አይከፍሉለት አያሳጥሩት በዚየውስ ላይ መላው መጥቶልን የለምን ? ከዚያው ግን አንድ ቀን የሚደርስ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደ ርበት ሰባቱን ኪዳናት ለይተውልናል ። መጀመሪያ ትም ህርተ ኅቡዓትን ለይተዋል ። ምእመናን ሥጋው ደሙን ለመቀበል በመጡ ጊዜ ፤ ከታላቅ አዳራሽ ገብተን ስንዴ ዳቦ በልተን የወይን ጠጅ ጠጥተን ሄድን እንዳይሉ ። ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለ ውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር እንዲሆን ቢገኝ ኤጲስ ቆጶሱ ቢታጣ ቄሱ ተርጕሞ ሊያስተምራቸው ይገባል ብለው ። ሁለተኛ ዘጠኙን ኪዳን ለይተዋል ። ሦስቱን ኪዳን ሦስቱን ፕልስቴ አድርጎ በመንፈቀ ሌሌት ። ሦስ ቱን ኪዳን ሁለቱን ፕልስቴ አድርጎ ከሥርቀተ ፀሐይ በኋላ ። ሦስቱን የሚጨምሩ አሉ ። ግንያትን እስዚህን

www.ethiopianorthodox.org

አድርጎ በሠርክ ቄሱ ለምእመናኑ ሊጸልይላቸው ። አንዱን ጥልስቴ ወዲህ ያመጡታል ። ሦስተኛ እግዚአብሔር ዘብርሃናትን ለይተዋል ። አዲስ አማኒ የተገኘ የሆነ እንደ ሆን ሦስት ዓመት አስተምረው ይህነን እየደገሙ ያጥምቁት ። ጣዖት ሲያስመልከው ኃጢአት ሲያሠራው የነበረ ሰይጣን የለቀቀው እንደሆነ ፀጥ ያደርገዋል ። ያልለቀቀው የሆነ እንደሆን ዐይኑን ያስፈጥጠዋል ጥርሱን ያስገጥጠዋል ። አረፋቱን ያስደፍቀዋል ። ከዚህ ሁሉ ያደረስከው አንተ አይደለህምን ብለው መላልሰው ያጥምቁት ፀጥ ሲል ፍጹም ጥምቀት ያጥምቁት ፤ ቦዘይቤ ታሪክ ፤ ዲያቆን ከወደኋላ እየመጣ ይህነን እየደገመ ዓርባ ቀን ሙሉ መላልሶ ያጥምቀው ። ፀጥ ሲል ፍጹም ጥምቀት ያጥምቁት ተብሎ ሥርዓት ተሠርቶለታል ። አራተኛ በእንተ ቅድሳትን ለይተዋል በእንተ በእንተ እያለ ከአናጉንስጢስ እስከ ሊቀ ጳጳሳት ከፈደሬ እስከ ንጉሥ ። ለምእመናን ለአዝርዕት ለአትክልት ሁሉ ሊጸልይላቸው ። አምስተኛ በሰማይን ለይተዋል ። ዲያቆን ካባ ላንቃውን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ ። መስቀሉን ይዞ ከፍ ካለ ቦታ ሆኖ እመቦ ዘቦ ነውረ ሕሊና ይትከላዕ ወኢይቅረብ ። እመቦ ስዑብ ወዘኢኮነ ንጹሐ ይትከላእ መስቀለ ኢይግፋዕ እስመ ዘኢይትገፋዕ እያለ በሕዝቡ ሊያዳኝበት ። ስድስተኛ ቅዳሴ እግዚእን ለይተዋል ። ቄሱ ሥጋውን በጻሕል ደሙን በጽዋዕ አድርጎ ሊያከብርበት ። ሰባተኛ ቅዱስ ሥሉስን ለይተዋል ። ሥጋውን ተቀብለው በአፋ



ቸው ሳለ ሊጸልዩት ። ሕዝቡ የሚያውቁት እንደሆነ ፤ ሕዝቡ ፤ የማያውቁት የሆነ እንደሆነ ግን ካህናቱ ይለዩላቸው ተብሎ ሥርዓት ተሠርቷል ። ታሪክ ይህ ነው ከዚህ በኋላ ኪዳንን ቢሹ ኪዳን ዘነግህ ፤ ትምህርተ ኅቡዓትን ቢሹ በእንተ ትምህርተ ኅቡዓት ማለት ነው ።

፩/ በእንተ ትምህርተ ኅቡዓት ቅድመ ዘትትነገር እምጽርስ ፎራ ።

፩/ ኅቡዓትን ስለመማር ኅቡዓትን ስለማስተማር ሥጋው ደሙን ከመቀበል አስቀድሞ የምትነገር ትምህርት ይህች ናት ። ኅቡዓት ያላቸው አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ናቸው ። መጀመሪያ ምሥጢረ ሥላሴን ኅቡዕ ብለውታል ። ሥላሴ በአካል ሦስት በባሕርይ በህልውና አንድ ናቸው ብለው ለሰው ይነግሩታል ። አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ ፤ አንድ መሆን እንደምን ይሆናል ብሎ ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይቻልምና ። ሁለተኛ ምሥጢረ ሥጋዌን ኅቡዕ ብለውታል ። አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ረቂቁ ገዘፈ ግዙፉ ረቀቀ ምሉዑ ተወሰነ ውሱኑ መላ ብለው ለሰው ይነግሩታል ። ረቂቅ ሲሆን ግዙፍ ፤ ግዙፍ ሲሆን ረቂቅ ፤ ምሉዕ ሲሆን ውሱን ፤ ውሱን ሲሆን ምሉዕ ፤ መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይቻልምና ። ሦስተኛ ምሥጢረ ጥምቀትን ኅቡዕ ብለውታል ። ቄሱ ውኃውን በብርት አድርጎ ሥርዓቱን አድ



www.ethiopianorthodox.org

ርሶ ቡሩክ ብሎ በባረከው ጊዜ ፤ ውኃው ተለውጦ በዕ
ለተ ዓርብ ከጐኑ የፈሰሰ ማየ ገቦን ይሆናል ብለው
ለሰው ይነግሩታል ። ይህ በብርት የምናየው ውኃ
አሁን ተለውጦ እንዲህ መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ
ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይቻልምና ። አራ
ተኛ ምሥጢረ ቊርባንን ኅቡዕ ብለውታል ። ቄሱ ኅብ
ስቱን በፃሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ ቡሩክ ብሎ
በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአ
ብሔር ፤ ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር
ይሆናል ብለው ለሰው ይነግሩታል ። እምቅድመ ይቀ
ድሶ ካህን ኅብስት ወወይን ፤ ወሶበ ይቄድሶ ካህን ይወ
ርድ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ ይትመየጥ ኅብስት እምከ
ዊነ ኅብስት ኅበ ከዊነ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ።
ወከማሁ ጽዋዕኒ ይትመየጥ ወይትዌለጥ እምከዊነ ወይን
ኅበ ከዊነ ደም አምላካዊ እንዳለ ። ኅብስቱ ተለውጦ
ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ
እግዚአብሔር ። መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ ልብ
ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይቻልምና ። አምስተኛ
ምሥጢረ ትንሣኤን ኅቡዕ ብለውታል ። ሰው ከፈረሰ
ከበሰበሰ በኋላ እንደገና አካል ገዝቶ ይነሣል ብለው
ለሰው ይነግሩታል ። በቀዳሚ ንፍሐተ ቀርን ይትጋባዕ
ጸበለ ሥጋ ዘተዘርወ ውስተ ኵሉ መካን ኅበ ሀለወ
ርእስ ። ወበዳግም ንፍሐተ ቀርን ይሰፈያ አዕፅምት
ምስለ ሥጋ ወይከውን በድነ ፍጹመ ዘእንበለ አንሰሐ



ስሖ ወኢተሐውሶ እስከ ጊዜሁ ። ወበሣልስ ንፍሐተ
ቀርን ይትነሥኡ ሙታን ከመ ቅጽበተ ዓይን እንዳለ ።
ሰው ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና አካል ገዝቶ መነ
ሣት እንደምን ይቻላል ብሎ ልብ ሊመረምረው ቃል
ሊናገረው አይቻልምና ስለዚህ ኅቡዕ ብለውታል ።
አንድም ሥጋው ደሙን ኅቡዕ ብለውታል ሲለወጥ አያ
ዩትምና አንድም አሁን የሚያመጣቸው ሰባት ነገራት
አሉ እነዚያን ኅቡዕ ብሏቸዋል ። ጽርስ ፎራ አለ ጽርስ
ብሎ ሥጋ ወደሙ ፎራ ብሎ ሥጋ ወደሙ ማለት ነው ።
የልሳን መለዋወጥ ነው ጽርስ በሐማሴን ፎራ በበቅላ
አንድም ። ፎራ በሐማሴን ጽርስ በበቅላ ፎራ ጽርስ
ሲል ነው ። የተዘዋወረ ቀለም ነው ፎራ ብሎ ኅብስት
ጽርስ ብሎ ደም አንድም ፎራ ብሎ ኅብስት ማለት
ነው ። አይለወጥም ጸሎተ እንፎራ እንዲል ። ጽርስ
ብሎ ሕይወት ኅብስተ ሕይወት ሲል ነው ። አንድም
ጽርስ ፎራ ብሎ ኅብስት ማለት ነው ጥቅል ስሙ ነው።
ጽርስ ፎራ ማሴው እንዲል በኤርምያስ ። ኅብስተ ካህን
ሲል ነው ።

ለምእመናን ኅቡዓት ።

ኅቡዓት ለሚገባቸው ለምእመናን የምትነገር ትም
ህርት ይህች ናት ፤ ለሌላ ሊነግሩት አይገባምና ። ወኢይ
ደሉ ይንግርዎሙ ትርጓሜሁ ለእለ ኢየአምኑ ፤ ተነብ
ዮስ ለእለ የአምኑ ወአኮ ለእለ ኢየአምኑ እንዲል ። አን
ድም ለምእመናን ኅቡዓት ሲል ነው ለምእመናን ቅሉ

www.ethiopianorthodox.org

ኅቡዕ የሚሆንባቸው ለሌላው ቢሠወር ድንቅ አይደለምና ። እመኒ ክዱን ትምህርትነ ክዱን ውእቱ ለሕርቱማን ወለንፉቃን በዝንቱ ዓለም ፤ ወአልቦ ምንትኒ ዘይሜኒ እምዘ ያነብሮ ለነገር በመዳልው እንዲል ። አንድም ለምእመናን ኅቡዓት ሲል ነው ፤ ኅቡዓት ለሚያሰኙ ለምእመናን የምትነገር ትምህርት ይህች ናት ። ምእመናን ሲበቁ ጠፈር ደፈር አይከለክላቸውምና ። እመኒ ተልእከነ ውስተ ምድር ግብርነሰ ሰማያዊ ውእቱ እንዲል ።

ትምህርተ ኅቡዓትስ ከመዝ ንግር ።

ትምህርተ ኅቡዓትንስ እንዲህ አድርገህ አስተምር ይላሉ መምህራን ፤ አስተጋባዕያነ መጻሕፍት ፫፻ ። አንድም ትምህርተ ኅቡዓትስ ከመዝ ንግሩ ሲል ነው ። ትምህርተ ኅቡዓትስ እንዲህ አድርጋችሁ አስተምሩ ትላለች ። ደርሶስ አለሳ ስለምን ቢሉ መጽሐፍ በስ ፤ በወ ፤ በአገባብ ፤ በሥነ ፍጥረት መጀመር ልማዱ ነውና ዳዊትስ ልህቀ ወረሥዓ ወኃለፈ መዋዕሊሁ ። ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በሀገረ አውሲጢድ ዘስሙ ኢዮብ ፤ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምደብረ ኤፍሬም ዘመሴፋ ዘስሙ ሕልቃና ፤ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ እንዲል ። አንድም የቀረው የምግባር የሃይማኖት ነው ፤ ይህ ግን የሃይማኖት ብቻ ነውና ። አንድም ትምህርተ ኅቡዓትስ ከመዝ ንግር ። የባለጌ አነጋገር ትምህርተ ኅቡዓትስ



እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አይደለችም ፤ ከላይ ከእለ አብርሃም ከእለ መልከ ጼዴቅ ስትያያዝ የወረደች ናት ። ባለጌ ንግሬ ደረሰ እንዲል ። እስከዚህ አርእስት ነው እንግዲህ ወዲህ ማንሻ ነው ።

ዘቅድመ ሀሎ ወይሄሉ ።

ቅድመ ዓለም የነበረ ፤ ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ነው። ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ቅድመ ዓለም የነበረ ነው።

ዘመጽአ ።

ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ። አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣ ነው ። መጀመሪያ ይህነን ኅቡዕ ብለውታል ። ቅድመ ዓለም የነበረ ፤ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ፤ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣው ነው ፤ ማለት ኅቡዕ ነውና ። አንድም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ነው ፤ ሁለተኛ ይህንን ኅቡዕ ብለውታል ። አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣ ፤ ቅድመ ዓለም የነበረ ፤ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ነው ፤ ማለት ኅቡዕ ነውና ። ይህ ምሥጢረ ሥላሴ ያ ምሥጢረ ሥጋዌ ፤ ከምሥጢረ ሥጋዌማ ምሥጢረ ሥላሴ አይቀድምም ስለምን እንዲህ አለ ቢሉ መቅደሙንስ ይቀድማል ፤ ነገር ግን አንድነት ሦስትነት የታወቀ ጌታችን ከመቤታችን

www.ethiopianorthodox.org

ከተወለደ ወዲህ ነውና ። ወአልቦ መንዚ ዘእእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት ድንግል እንዲል ።

ዘሐመ

አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣው የታመመው ነው ፤ ሐመ ከመ ሕሙማን ያድኅን ፤ ዘተውህበ በፈቃዱ ለሕማም እንዲል ፤ ሦስተኛ ይህንን ኅቡዕ ብለውታል ፤ አንዱን አካል ሐማሚ ፤ ኢሐማሚ ነው ማለት ኅቡዕ ነውና ፤ አንተ ሐማሚ ዘከመ ዕሪናከ ምስሌነ ወአንተ ኢሐማሚ ዘከመ ዕሪናከ ምስለ አብ እንዲል ።

ወሞተ ።

የታመመውም የሞተው ነው ፤ በሞቱ ለሞት ደምሰሶ ፤ እሁብ እኩያነ ህየንተ ሞቱ እንዲል ። አራተኛ ይህነን ኅቡዕ ብለውታል ፤ አንዱን አካል መዋቲ ነው ፤ ኢመዋቲ ነው ማለት ኅቡዕ ነውና ። አንተ መዋቲ ዘከመ ዕሪናከ ምስሌነ ፤ ወአንተ ኢመዋቲ ዘከመ ዕሪናከ ምስለ አብ እንዲል ።

ወተቀብረ ።

የሞተውም የተቀበረው ነው ፤ ወበተቀብሮተ ሥጋሁ ለእግዚእነ ውስተ ምድር አሰሰለ ሙስና እምውስተ መቃብር ወመልሐ እምሥርዉ ። ወአብዕለተ ህየንተ መቅበርቱ እንዲል ። አምስተኛ ፤ ይህንን ኅቡዕ ብለው



ታል ፤ አንዱን አካል ከዚያ በዘባነ ኪሩብ ይሠለሳል ይቀደሳል ከዚህ በከርሠ መቃብር አለ ። ከዚህ በመቃብር ተወስኑዋል ፤ ከዚያ በዓለሙ ምሉዕ ነው ማለት ኅቡዕ ነውና ። አንተ ንቡር ዲበ ኪሩቤል ፤ ወአንተ ኅዱር ውስተ ከርሠ ምድር ፤ ዕዉረ ተርእየ ለተወድዮ ውስተ መቃብር እንዘ ውእቱ ይመልዕ ኵሎ እንዲል ።

ወተንሥአ ።

የተቀበረውም የተነሣው ነው ። ተንሥአ እግዚእነ ከመ ይምሐረነ ተንሥአ ሥጋቲነ እንዳለ ። ስድስተኛ ይህንን ኅቡዕ ብለውታል ። አንዱን አካል ከዚህ ከመቃብር በአፍአ አለ ። ከዚህ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ከፈቱልኝ ሳይል ከመቃብር ሰበሩን ጥሎ ተነሣ ማለት ኅቡዕ ነውና ። አፍአ ውእቱ እመቃብር ወየኃድግ ሰበነ ውስቴቱ እንዲል ።

ፃዕረ ዘሞት ፈትሐ ።

የተነሣውም የሞትን ፃዕሩን ፃዕረኝነቱን ያሰናበተው ነው ። ፃዕሩ ፍዳ ፤ ሞት ነው ፤ ፃዕረኝነቱ ራሱ ነው ፤ በግብሩ ሞት ብሎታል ፤ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ቀድሞ ሰው ሲጸንስ በዘርዕ በሩካቤ ይጸነሳል ፤ ነፍስ ትጸናለች ስትጸንስ አይቶ ዲያብሎስ ይቆራኛታል ። ኋላም ይወለዳል ። ኃጢአት ሲያሠራው ጣዖት ሲያስመልከው ይኖራል ኋላም በሞት ጊዜ ሰውየው ይታመማል ። መጥቶ በኅሡም ራእይ ይታየዋል ፤ ሰውነቱ ይቀዘቅዛል ። ነፍስ ደንግፃ ከሥጋዋ ትለያለች አንድ አንዱን እየነ

ጠቀ በእሳተ ገሃነም ያግዘው ነበረ ፤ ወለዘሞተ እምኔ ሆሙ የአሥሩ ነፍሶ ውስተ ሲኦል አሜሃ ይትፌነዋ ነፍሳት ውስተ ገሃነም እስከ ይመልዓ አብያተ ሞት እንዲል ። ኋላ ግን ጌታ ሲጸነስ ። እንበለ ዘርእ እንበለ ሩካቤ ተጸነሰ ፅንት አጣበት ቁራኝነት ቀረ ኋላም እንበለ ዘርዕ እንበለ ሩካቤ ተወልደ ። ኋላም በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣው ። ኋላም በሞተ ጊዜ አባ አመሐጽን ነፍስየ ኀቤከ ብሎ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በፈቃዱ ለየ እንዲህ አድርጎ መንገድ ለወጠበት ። እኛም ከጐኑ በፈሰሰ ማየ ገቦ ተጠምቀን ከፍዳ ነጽተናል ፤ ከቁራኝነት ተላቀናል ። ወበጥምቀተ ክርስትና ይከውን ሰብእ አግአዜ እምግብርናተ ኃጢአት ወእምሥልጣነ ዲያብሎስ ወአጋንንቲሁ ርኩሳን ወይከውን አምሳለ ትስብእቱ ለክርስቶስ እስመ መንፈሰ ክርስቶስ ይቄድሶ እምልደተ ፍትወት ለዘተወልደ በልደተ ፍትወት ወይሬስዮ ዘእንበለ ፍትወት እንዲል ። ከዚህ በኋላ ወደላይ እንጂ ወደታች መውረድ ቀርቶልናል ። እንከሰ ኢንወርድ ውስተ ሲኦል አላ ንተልዎ ፈድፋደ ለዘፈጠረነ እንዲል ። ሰባተኛ ይህን ኅቡዕ ብለውታል ። አሁን ከኛ ጋራ ባንድነት ያለውን ሥጋ የሞት ፃዕሩን ፃዕረኝነቱን ያሰናበተ ነው ማለት ኅቡዕ ነውና ።

ወዘእሙታን ተንሥአ ።

የሞት ፃዕሩን ፃዕረኝነቱን ያሰናበተውም ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ነው ። ይህንማ ተናግሮት አልነበረም ቢሉ ለማስረዳት ደገመው ለማስረዳትማ ቢሆን መላውን ይደግመው አልነበረም ብሎ እሙታን ለማለት ። የነዚያ በብሉይ ሥጋ ነው የሱ ግን በሐዲስ ሥጋ ነውና እለዚያን ሁለተኛ ሞት አግኝቷቸዋል እሱን ግን ኢይመውት እምዝ ዳግመ ይለዋልና እለዚያ አንሺ እሱን ፈልገው ነው እሱ ግን ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ ይላልና ። እለዚያ ትንሣኤ ዘጉባዔን ይጠብቃሉ እርሱ ግን ወአሕጸረ ዕድሜ ለርእሱ ይለዋልና ።



፩/ ኢኮነ ባሕቲቱ ከዊኖ ሰብአ ዘእመንፈስ ቅዱስ ።

፪/ ዘሐመ ወሞተ ብሎ ነበረና የታመመው የሞተው ብቻ ሥጋ አይደለም ፤ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሥጋን ተዋሕዶ ቃልም ሰው ሁኖ ነው እንጂ ። አንድም ፃዕረ ዘሞት ፈትሐ ወዘእሙታን ተንሥአ ብሎ ነበረና የሞት ፃዕሩን ፃዕረኝነቱ ያሰናበተው ፤ ብቻ ቃል አይደለም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቃል ተዋሕዶት ሥጋም አምላክ ሁኖ ነው እንጂ ፤ ኢኮነ ፪ተ አላ አሐዱ ውእቱ አምላክ ብሎ በእልመስጦአግያ ወስዶታል ።

ሥጋሁ ለአዳም ምስለ ነፍሱ ።

ይህንማ ተናግሮት አልነበረም ቢሉ ምስለ ነፍሱ ለማለት ደገመው ። ህየንተ ነፍስ ወልቡና ኮኖ መለኮቱ ብለው ነፍስ አልነሣም የሚሉ መናፍቃን አሉና ነፍስ እንደነሣ ለማጠየቅ ። አንድም በሥጋው ለሥጋችን በነፍሱ ለነፍሳችን እንደካሰልን ለማጠየቅ ፈድዮ ሥጋ

www.ethiopianorthodox.org

ዘእሁ ለዘበአማን ሥጋ ዘአነ ወነፍሶ ካዕበ ቤዛ ነፍሰ ኲልነ መጢዎ እንዲል ፡፡

ዘኢኃደገ ነፍሶ ውስተ ሞት ፡፡

የተዋሐደውን ሥጋ በርኅቀት አግኝቶ የተወው አይደለም ፡፡ እንበለ ርኅቀት አግኝቶ ተዋሐደው እንጂ ሞታ ለነፍስ ርኁቅ እምእግዚአብሔር እንዲል ፡፡ ንጹሕ ሁኖ ቢያገኘው ለበሰው ሲል ነው ፡፡ ወሶበ ረከበ ሥጋሃ ንጽሕተ ወነፍሳ ክብርተ ፈጠረ ሎቱ መቅደስ ሕያወ በመንፈስ ቅዱስ እንዲል ፡፡ እስከ ዕለተ ዓርብ መለኮቱ ተዋሕዶት ኖረ በዕለተ ዓርብ መለኮት ቢለየው ሥጋ ፈርቶ ኤሎሄ ኤሎሄ አለ የሚሉ መናፍቃን አሉና የተዋሐደውን ሥጋ በሞትም ጊዜ የተለየው አይደለም ፡፡ አካለ ሥጋ ወደ መቃብር በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ እንጂ ፡፡ አንድም የተወሐደውን ሥጋ በሞት የተወው አይደለም ፡፡ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ከነፍሱ ጋራ አዋሕዶ አስነሣው እንጂ ፡፡

ዘበመንፈስ ለአዳም ጸወኖ ወአሕየዎ ፡፡

በግብረ መንፈስ ቅዱስ የተዋሐደው አዳም ሥጋውን ጸወኖ አከበረው ወአሕየዎ የማይሞት ሕያወ ባሕርይ አምላክ አደረገው ፡፡

፫/ ዘለብሶ ለአዳም መዊቶ ሐይወ ፡፡

፫/ አዳም ሥጋውን የተዋሐደው እሱ ሙቶ ተነሣ አንድም መዊቶ ሕያው ፤ ሙቶ ሳለ ሕያው ነው ፤ ዘዓርገ ውስተ ሰማያት ተዋሪዶ ለሞት ፡፡



ተትሒቶ ሲል ነው ለሞት ተዋርዶ ውሳጤ መንጦላዕት ገብቶ መዓርገ መላእክትን እንደ ጫማ ተጫምቶ የኖረ ነው ፡፡ አንድም ተወሪዶ እንደ ማለት ያለ ነው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም የሞት ቀጠሮ ነበረ በትና ያንን ተወርዶ ውሳጤ መንጦላዕት ገብቶ መዓርገ መላእክትን እንደ ጫማ ተጫምቶ የኖረ ነው ፤

እምድኅረ መስቀል ሞዓ በቲኮ ማዕሠሮ ለሞት ፡፡

በመስቀሉ ከመስቀሉ በኋላ የሞት ፍዳን አጥፍቶ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ ውሳጤ መንጦላዕት ገብቶ መዓርገ መላእክትን እንደ ጫማ ተጫምቶ የኖረ ነው ፡፡ እምድኅረ መስቀል አለ ፤ የገደልህ ገደልህ የበደልህ በደልህ የቀማህ ቀማህ ልቀቅ ብሎ እንበለ ፍትሕ አላደረገውምና ፤ ጨርቅ ታጥቆ ግንድ ተሸክሞ ተዋርዶ ነውና ፡፡ ወበድልወት ኮነ ቤዛኒ እግዚእ ወአድኃነነ በፍትሐ ጽድቅ ወበርትዕ እንዲል ፡፡

በእንተ ዘተኃየለነ ዲያብሎስ ትካት ፡፡

አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ዲያብሎስ ስለተበረታታብን ዲያብሎስን ከመጣ ብለው ከዚህ ይናገሩታል ፡፡ ዲያብሎስ ማለት ያፍ ሥሩር ፤ ነድ ውዑይ ፤ ፈታዊ ማለት ነው ፤ ያፍ ሥሩር አለ ፤ ለማሳት ይፋጠናልና ፡፡ ነድ ውዑይ አለ ደዌ ትኩሳት እየሆነ ያማልና ፤ ፈታዊ አለ አምላክነትን ሲሻ ተገኝቷልና ስሙንም ከዚህ አያይዘው ይናገሩታል ፤ ጋኔን ማለት ዕሩቅ ፣ ውዱቅ ማለት ነው ፡፡ ሰይጣን ማለት መስተፃርር መስተቃ

www.ethiopianorthodox.org

ርን ባላጋራ ማለት ነው ወዐቀመ አዴርሃ ሰይጣነ እን ዲል ።

በዝንቱ ፤

አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ስለተበረታታ ብን ።

በእንተ ሕማሙ አርአየነ ሙስናሁ ፤

በሰውነቱ መከራ ተቀብሎ የዲያብሎስን ድል መነ ሣቱን አሳየን ። አንድም በዝንቱ በእንተ ሕማሙ በዚህ በመስቀሉ በሰውነቱ መከራን ተቀብሎ የዲያብሎስን ድል መነሣቱን አሳየን ።

በቲኮ ኅምዘ ኀይሉ ሠጠጠ መሥገርቶ ።

ከባሕርዩ የምትነቃ መርዝን አጥፍቶ አሽከላውን ቆረጠ ፤ ነቅዓ ሐልዮ ናት ፤ ነቅዓ ሐልዮን በመርዝ መሰ ላት መርዝ ከአካል አንድ ላይ የነካ እንደሆነ ተሠራጭቶ ሰውነትን ሁሉ ይጐዳል ። ነቅዓ ሐልዮም ከአንድ ከአዳም ተገኝታ ሰው ሁሉ ተጐድቶባታልና ወሶበ ኮነኒ ኃጢአት እምላዕለ አሐዱ ብእሲ ወጺዓ ኵሉ ተቀሥፈ ባቲ እንዲል ።

ሠጠጠ መሥገርቶ የነቢቡን የገቢሩን ኃጢአት በመረብ መሰላት ። በመረብ ብዙ ዘመድ ዓሣት ይያዙ በታልና ። በነቢብ በገቢር ኃጢአትም ብዙ ሰው ተጐ ድቶበታልና ። ወሶበ ዓለወ አቡነ አዳም ኮነ ፍናዊሁ ለዓለም መብዕስ ወጕፃጕፀ እንዲል ። አንድም በቲኮ ካልኩ ብሎ ኅምዝ ፤ ሠጠጠ ካልኩ ብሎ መሥገርት



አለ እንጂ ፤ ኃይሉን አድክሞ ጽኑትን ፤ ጽኑትን አጥፍቶ ቁራኝነትን ፤ ቁራኝነትን አጥፍቶ ፤ ነቅዓ ሐልዮን ፤ ነቅዓ ሐልዮን አጥፍቶ ፤ የነቢቡን የገቢሩን የነቢቡን የገቢሩን ፤ ኃጢአት አጥፍቶ ፍዳ ሞትን አጠፋ ሲል ነው ።

፬/ ወገጹ ዘፍጹም በጽልመት ፈርሃ ወደንገጸ ዲያ ብሎስ ።

፬/ ወዲያብሎስ ገጹ ዘፍጹም በጽልመት ሲል ነው ። ፊቱ ጨለማን የተቀባ ዲያብሎስ ፤ ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነ ገጸ ፤ ተሸበረ ፤ ይህ በ ፤ በግዕዝ ቦታ የገባ ነው ፤ አንተሰ ኢቀ ባዕከኒ በዘይት ርእስየ ቀስተ ዮናታን ኢተቀብዓት በቅ ብዕ ዘእንበለ ደመ ቅቱላን ፤ አሪት ወነቢያት ሰበኩ በክ ርስቶስ ፤ ለምሁራን ልብ በጥበብ እንዲል ። በግዓ ፍጻ ሜ እንዲል በግዓ ቅብዓት ሲል ፤ አንድም ፊቱ በጨለማ መዝጊያ የተዘጋ ዲያብሎስ ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገጸ ፤ ተሸ በረ ። እፎ፡ጽግሞ መንገዳ ወአሐጽር ፍኖታ በሶክ ፤ ወፈ ጸሙ አፈ አናብስት ወትትፈጸም አፉሃ ኵላ ዓመፃ እስመ ይትፌጸም አፍ ዘይነብብ ዓመፃ እንዲል ። አን ድም ወገጹ ዘፍጹም በጽልመት ፊቱ በጨለማ የታተመ ዲያብሎስ ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገጸ ፤ ተሸበረ ። ጌታ ቀድሞ ዲያብሎስን ሲፈጥረው ሊቀ መላእክት ፤ አኃዜ መንጦላ ዕት ፤ ቅሩበ እግዚአብሔር አድርጎ ፈጥሮት ነበረ ። ኋላ ግን ቀድስ ቢሉት ቀድሱኝ ፤ ፍጡር ነህ ቢሉት ፤ ፈጣሪ ነኝ አለ ። ብርሃኑን ገፎ በብርሃኑ ቦታ ጨለማ አጐና

www.ethiopianorthodox.org

ጽፎ ፤ እንጦርጦስ አውርዶታልና ወሀየንተ ብርሃን
ዘመላእክተ ትፍሥሕት በአርአየ ሰይጣናዊት ርኩስት
እንዲል ።

ርእየ ብሁተ ልደት በሥጋ አምላክ በሲኦል ፤

ብሁተ ልደት አምላክ ርእየ በሥጋ በሲኦል ሲል
ነው ። በልደት የሠለጠነ አምላክን በጎል ተጥሎ በጨ
ርቅ ተጠቅልሎ አይቶ ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገጸ ፤ ተሸበረ ፤
ይህ መወለዱ ካባቱ ጋራ ያስተካክለዋልና ፤ አንድም
በዚህ ስም አብ መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትምና ። አን
ድም በዚህም ዓለም በወዲያም ዓለም ወልድ እየተባለ
የሚኖር እሱ ነውና ። አንድም ብሕትወ ልደት ሲል
ነው የልደት ብቸኛ የሚሆን ወልድን በጎል ተጥሎ በጨ
ርቅ ተጠቅልሎ አይቶ ። ከዚህ ዓለም ልጅ ሲለይ ፤ የዚህ
ዓለም ልጅ ፤ እናት አባት አንድ ካልሆኑ አይወለድም
እሱ ግን ከአባት እንበለ እናት ከእናት እንበለ አባት
ተወልዷልና አንድም የዚህ ዓለም ልጅ በዘርአ ሩካቤ
ይወለዳል ፤ እሱ ግን እንበለ ዘርዕ እንበለ ሩካቤ ተወል
ዷል ፤ አንድም የዚህ ዓለም ልጅ ፤ ልጅ ተብሎ ኑሮ የወ
ለደ ጊዜ አባት ይባላል ። እሱ ግን ለዘለዓለም ወልድ
እንደተባለ ይኖራልና ። ሲኦል አለ ፤ ጉድጓዳውን
መሬት ሁሉ ሲኦል ይለዋልና ። እግዚአ አውጽእካ እም
ሲኦል ለነፍስየ ። ምድርኒ እንተ ኢትመልእ ማየ ገሃ
ነም ይእቲ ወኵሉ ዘተትሕተ እምድር መቃብር ውእቱ
እንዲል ። ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ጌታ ሊወለድ ኻያ



አራት ቀን ሲቀረው መካነ ልደቱን አስጠበቀ ጣዖታት ተሰ
በሩ ፤ አጋንንት ተባረሩ እኛንም የሚያኖረን አጣን ብለው
ሂደው ላበጋዛቻው ለዲያብሎስ ነገሩ ፤ እሱም ቀድሞ ኢሳይ
ያስ የሚባል ሰው ተነሥቶ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ
ወልደ ብሎ ትንቢት ቢናገር በምናሴ አድሬ በመጋዝ
አስተርትሬ በኩላብ አሰቅዬ አስገድዬው ነበር ። ያ ብላ
ቴና ተወልዶ ይሆን ? ያ ብላቴና ተወልዶ እንደሆን
ወዮ ለኔ ወዮ ለናንት ። እስኩ ንዑ ዑሩኒ ብሎ ተሸ
ክመው ይዘውት ወጡ ። ባራቱ ማዕዘን ዞረው አጥ
ተውት ሲመለሱ በቤተ ልሔም የብርሃን ድንኳን ተተ
ክሎ አዩ ። አይተው እንቀርባለን ቢሉ መላእክት ሐፀ
እሳት ኵናተ እሳት ይዘው የማያስደርሷቸው ሁነዋል ።
የኔ ገዳይ ዛሬ ገና ተወለደ ብሎ አዝምሮ ሸሽቷል ።
ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገፀ ፤ ተሸበረ ። አንድም ርእየ በሥጋ
ብሁተ ልደት አለ ። ሰሚዖ ሲል ነው አድንን ወልድየ
ለርእየ ሕልመ አቡከ ለርእየ ሕልመ አቡሁ ገብአ ማቱ
ሰላ ። ስምዒ ወለትየ ወርእዩ እንዲል ። በመስቀል በዕ
ለተ ዓርብ በሥጋ ኤሉሄ ኤሎሄ ሲል ሰምቶ ፈርሃ ፤ ጠረ
ጠረ ፤ ደነገፀ ፤ ተሸበረ ፤ ወአምላክ በሲኦል አምላክንም
በአካለ ነፍስ ወደሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ሲበዘብዝ አይቶ
ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገፀ ፤ ተሸበረ ።

፫/ ወሪዶ ዘእምልዑላን ሰማያት ዘኢይትነገር ወሪዶ

፬/ ወሪዶና ወሪዶ አንድ ወገን ። ከሰማየ ሰማያት
ወርዶ ከድንግል ተወልዶ በጎል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅ

www.ethiopianorthodox.org

ልሎ አይቶ ፈርሃ ፤ ጠረጠረ ፤ ደነገፀ ፤ ተሸበረ ፤ አንድም ወሪዶና ወሪዶን ለማውጣት ። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ምንም ቢወርድ ርደቱ ዘኢይትነገር መውረዱ የማይመረ መር ነው ።

ሕሊናሁ ዘኢይትከፈል ።

የአብ ሕሊናው የማይለይ ነው ። አንድም የማይለይ የአብ ሕሊናው ነው ።

በአሐቲ ምክር ምስለ አቡሁ ሰማያተ ገብረ ።

ቢጽ በሌላት ሥልጣን ካባቱ ጋራ ሰማያትን ፈጠረ ምስለ አቡሁ አክሊሎሙ ለመላእክት ፤

ካባቱ ጋራ የመላእክት ክብራቸው ነው ። ከዚህ ዓለም ነገሥታት ሲለይ ፤ የዚህ ዓለም ነገሥታት ክብ ራቸው ዕብነ ሕንደኬ ነው ። አዕባነ ሕንደኬ ያበርህ ክብርተ አርእስቲክሙ እንዲል ። የመላእክት ግን ክብ ራቸው እሱ ነው ።

ወለሊቃነ መላእክት ኃይል ።

የሊቃነ መላእክት ኃይላቸው እሱ ነው ። ከዚህ ዓለም ነገሥታት ሲለይ ፤ የዚህ ዓለም ነገሥታት ኃይላ ቸው ብዝኃ ሠራዊት ነው ፤ ኃይሉ ወክብሩ ለንጉሥ ብዝኃ ሠራዊት እንዲል ። የሊቃነ መላእክት ግን ኃይላ ቸው እሱ ነውና ። ከኃያልነታቸውም የተነሣ አንዱንም አንዱን መልአክ ወነሥአ አሐዱ መልአክ ኃያል ወጾ



ኑዕ ዕብነ ዓቢየ ከመ እንተ ማኅረፅ ወወገረ ውስተ ባሕር ይለዋልና ።

ለኃያላን አጽፍ ።

የሊቃነ መላእክት የብርሃን መጐናጸፊያቸው እሱ ነው ። ከዚህ ዓለም ነገሥታት ሲለይ ፤ የዚህ ዓለም ነገ ሥታት መጐናጸፊያቸው ካባ ላንቃ ፤ ወርቀ ዘቦ ግምጃ ነው ። የሊቃነ መላእክት ግን የብርሃን መጐናጸፊያቸው እሱ ነው ።

ወለአጋእዝተ መንፈስ ።

የሊቃነ መላእክት ርቀታቸው እሱ ነውና ። ከዚህ ዓለም ነገሥታት ሲለይ የዚህ ዓለም ነገሥታት እንሠ ወር ባሉ ጊዜ ቅጽር ቀጽረው አጥር አጥረው ድንኳን ተክለው መጋረጃ ጥለው አዳራሽ ገብተው እልፍኝ ተከ ተው ነው ። የሊቃነ መላእክት ግን ርቀታቸው እሱ ነውና ከርቀታቸውም የተነሣ አንዱንም አንዱን መል አክ ወኃለፈ መልአክ በመልአክ ይለዋልና ። አንድም ምስለ አቡሁ ሰማያተ ገብረ ፤ ካባቱ ጋራ ልዑላኑን ትሑ ታኑን አከበረ ። ምስለ አቡሁ አክሊሎሙ ለመላእክት ፤ ካባቱ ጋራ የቀሳውስት የዲያቆናት ክብራቸው ነው ። ወለሊቃነ መላእክት ኃይል የኤጲስ ቆጶሳትም ኃይላቸ ው እሱ ነው ። ለኃያላን አጽፍ ለጳጳሳትም ልጅነት እንዲቀበሉ ልጅነትን እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ።

6*

www.ethiopianorthodox.org

ወለአጋእዝት መንፈስ ።

ለሊቃነ ጳጳሳትም ምሥጢር እንዲተረጕሙ ኃይለ ቃል እንዲናገሩ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ።

ዘእምቅድመ ዓለም መንግሥቱ ሰፋኒት ።

ቅድመ ዓለም የነበረች መንግሥቱ ምልዕት ናት ። አንድም ምልዕት የምትሆን መንግሥቱ ቅድመ ዓለም የነበረች ናት ።

ለቅዱሳን እዘዝ ።

ለቅዱሳን ጽንአቸው እሱ ነው ። አንድም ዘእም ቅድመ ዓለም መንግሥቱ ሰፋኒት ። ቅድመ ዓለም የነበረች ልጅነቱ ፍጽምት ናት ። አንድም ፍጽምት የምትሆን ልጅነቱ ቅድመ ዓለም የነበረች ናት ። ለቅዱሳን እዘዝ ። ርእስ ብሎ በእልመስጠአግያ ያነበዋል ። የምእመናን በኵራቸው እሱ ነው ።

፯/ ሕሊናሁ ለአብ ዘኢይትረከብ ፤

፯/ የአብ ሕሊናው የማይመረመር ነው ። አንድም የማይመረመር የአብ ሕሊናው ነው ።

ውእቱ ጥበቡ ለአብ ፤

የአብ ጥበቡ እሱ ነው ፤ በጥበብ አንድ ናቸው ፤ ጥበቡን ይሠራበታልና ።



ውእቱ ኃይሉ ።

የአብ ኃይሉ እሱ ነው በኃይል አንድ ናቸውና ኃይሉን ይሠራበታልና ።

ውእቱ የማኑ ።

እደ መዝራዕት ካለው ይፈቷል ፤

ውእቱ ምክሩ ፤

ጥበቡ ካለው ይፈቷል ።

ውእቱ ሕሊናሁ ፤

የአብ ሕሊናው እሱ ነው ። ሦስት ጊዜ ሕሊናሁ አለ ቀድሞ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጥሮበታልና ፤ ኋላም አስቦ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ አዳምን አድኖበታል ። ኋላም አስቦ ይህን ዓለም ከመኖር ወደአለመኖር ወስዶ ያሳልፍበታልና ። ዳግመኛ ራሱ ቃል ሲሆን ለሁለቱ ሁሉ ቃላቸው ነውና ወልድሂ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ ። ቃለ አብ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ እንዲል ።

እደ መዝራዕት ዘአብ ከዊኖ እንከ ።

ሥጋም ቢሆን የአብ ቀኝ ክንድ ሁኖ ይኖራል ። አንድም እንግዴህ ይህ ሥጋ የአብ ቀኝ ክንድ ሆኖ ይኖራል ።

፯/ እንዘ ነአምን በሃይማኖቱ ንገኒ ከመ ውእቱ ብርሃን ፤

፯/ አንድነቱን ሦስትነቱን አምነን ብርሃን ዘእምብርሃን እንደሆነ እናምናለን ። አንድም ሥጋዌውን አምነን ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ውእቱ ብርሃነ መድኃኒትነ ብሎ በእልመስ
ጦአግያ ያነበዋል ። የድኅነታችን ምክንያት እንደ ሆነ
እናምናለን ። አፍኒ ዘየአምን ቦቱ ይገኒ ለመድኃኒት
ወኵሉ ሕሊና ይግነይ ለእግዚአብሔር እንዲል ። እን
ድም ብርሃን ዘእምብርሃን እንደሆነ ዐውቀን ወዲህም
በዓቂበ ሕግ እንገዛለን ።

ሕጽበተ መድኃኒት ።

የድኅነት መታጠቢያችን እሱ ነው ። ወይቄድሱ
ሥጋሆሙ ለእለ ረኩሱ ካለው ሲለይ ፤ ያ ሥጋዊ ይህ
መንፈሳዊ ፤ ያ ፤ አፍአዊ ይህ ውሳጣዊ ፤ ያ ፤ ምድራዊ ይህ
ሰማያዊ ነውና ። ተሐጽቦሰ ዘዝየ እኮ ዘሥጋ ዳዕሙ ዘነ
ፍስ ወሕፁብ ሥጋነ በማይ ንጹሕ እፎ ያነጽሕ ሕሊናነ
እምግብር ምውት እንዲል ።

ምሥዋር ።

ራሱን በራሱ የሚሠውር ፤ ለሊከ ኪያከ አንጦላ
ዕከ ፤ ወለሊከ ብከ ተከደንከ ፤ ሥውር ብከ ዕበይከ
በኃይልከ እንዲል ። አንድም ጻድቃንን በክብር የሚሠ
ውር ። ወይሤውር ኅሩያኒ በደመና እንዲል ። አንድም
ከመከራ የሚሠውር ፤ እስመ ሠወረነ ወረድአነ እንዲል ።
አንድም ኀጥአንን በንስሐ የሚሠውር ። ከባቴ አበሳ መፍ
ቀሬ ንስሐ ይለዋልና ።

ረድኤት ።

ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ፤ ከሁለት አካል
አንድ አካል ሆኖ ሰውን የሚያድን ። መጽአ ወረድ



አሙ ለእለ ይትኤገሎሙ ሰይጣን ። እስመ በከመ አሕ
መምዎ ወበከመ አመከርዎ ክህለ ረድኤቶሙ ለሕሙ
ማን ፤ ወረድአነ በከመ ምክረ ፈቃዱ እንዲል ። አን
ድም ሰብአ ዓለምን የሚረዳ ፤ ሽፋጭ ለተነሣበት ዳኛ
ላደላበት ዋስ ጠበቃ በመስጠት ፤ ዋስ ጠበቃ በመሆን
የሚረዳ እሱ ነውና ። በምግብ ጊዜ ሐሩር ላስቀረበት
በረድ ለመታበት አንበጣ ለበላበት ምግብ በመስጠት
የሚረዳ እሱ ነውና ። አንድም ባሕታውያንን የሚረዳ
ከፍትወታት ከእኩያት የሚረዳቸው እሱ ነውና ። በም
ግብ ጊዜ ዛፍ እንዲያፈራላቸው ቶራ እንዲታለብላቸው
የሚያደርግላቸው እሱ ነውና ። አንድም ሰማዕታትን
ሥቃይ በማቃለል የሚረዳ ፤ ጠል አውርዶ ፤ ነበልባል
አብርዶ ፤ አንበሳ አሰግዶ ፤ የሚረዳቸው እሱ ነውና ።
አንድም ዓላውያን ነገሥታት ዓላውያን መኳንንት ካሉ
በት ሂደው ምሥጢር እንዲተረጕሙ ፤ ኃይለ ቃል እን
ዲናገሩ የሚያደርጋቸው እሱ ነውና ።

ወመምህር ዘይትቃወም ለነ ።

ተከራክሮ የሚረታልን መምህር እሱ ነው ። በሠለ
ስቱ ምዕት አድሮ አርዮስን ፤ በሁለቱ መቶ ሊቃውንት
አድሮ ንስጥሮስን ፤ በመቶ ሃምሳ ሊቃውንት አድሮ መቅ
ዶንዮስን ፤ እስከ ምጽአት ድረስ በሚነሡ መምህራን
አድሮ እስከ ምጽአት ድረስ የሚነሡ መናፍቃንን ተከ
ራክሮ የሚረታልን መምህር እሱ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘየዓሚ ተወካፌ ፡፡

መምህር ዘየዓሚ ትምህርቱን የሚገልጽ ያንን
ዋጋ አድርጎ የሚቀበል ፡፡ የዚህ ዓለም መምህር የሆነ እን
ደሆነ ይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ ይለኛል ብሎ ደመ
ወዙን እየተቀበለ እየበላ እየጠጣ ያስተምራል ፤ እሱ ግን
የሚገልጽ እሱ ነውና ያንንም ዋጋ አድርጎ ይቀበለዋ
ልና ፡፡ አንድም አካሉን ለተዋሕዶ የሚሰጥ ተወካፌ የሰው
ፍዳ ኃጢአቱን የሚቀበል ፡፡ በእንተ ኃጢአተ ሕዝብየ
በጽሐ እስከ ለሞት ወበእንተ ዘተወፈየ ትእዛዘ ሕዝብ
እንዲል ፡፡ አንድም ዘየዓሚ ሥጋውን ደሙን የሚሰጥ
ዘበልዓ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ብሎ ተወካፌ ፤ ያንን ዋጋ
አድርጎ የሚቀበል ተወካፌ መሥዋዕት ምስለ አቡሁ ወመ
ንፈስ ቅዱስ ይለዋልና ፡፡ አንድም ዘየዓሚ ከባለጸጎች
ጋራ ሁኖ የሚሰጥ ፤ ተወካፌ በነዳያን አድሮ የሚቀበል
ዘገበርክሙ ለአሐዱ እምእሉ ንዑሳን አኃው ሊተ ገበር
ክሙ ይላቸዋልና ፡፡ እንግዲህ ወዲህ ተወካፊን ያስቀድማል፡፡
ተወካፌ የሰውን አሥራት ጾሙን አሥራት ጸሎቱን የሚ
ቀበል ወኢይትከሃል ያቅርቡ ፤ ወኢምንተኒ ዘእንበለ
በአራቅያኒሁ ለወልድ እንዲል ፡፡ ወዘየዓሚ በዚያ ዋጋውን
የሚሰጥ አንድም ሰውን በሃይማኖት የሚቀበል ለዘመ
ጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽኦ አፍአ እንዲል ፡፡ ወዘ
የዓሚ በዚያ ዋጋውን የሚሰጥ አንድም ሰውን በንስሐ
የሚቀበል ኢይብለከ እስከ ስብእ አላ እስከ ሰብአ በበሳ
ብእ እንዲል ፡፡ ወዘየዓሚ በዚያ ዋጋውን የሚሰጥ ፡፡
አንድም ሰውን በሞት የሚቀበል ፤ ትገብእ ነፍስ ኀበ



ፈጣሪሃ ወታቀድም ሰጊደ ለልዑል እንዲል ፡፡ ወዘየዓሚ
በዚያ ዋጋውን የሚሰጥ ፡፡

ምጽንዓተ ቅጽርነ ፡፡

ጽኑዕ አምባችን እሱ ነው ፡፡ አምባን በሦስት
ነገር ያጸኑታል በበር ፤ በድር ፤ በላባ ፤ ፊት ለፊት ታይቶ
የመጣውን በበር ይመልሱታል ፤ ተሠውሮ የመጣውን
በድር ይመልሱታል ፤ በላይ የመጣውን በላባ ይመልሱ
ታል ፤ ፊት ለፊት የመጣውን በበር እንደመመለስ ኢት
ፍርህዎሙኬ ለእለ ይቀትሉ ሥጋክሙ ወለነፍስክሙሰ
ኢይክሉ ቀቲሎታ ፍርህዎሰ ለዘቦ ሥልጣን ከመ ይቅ
ትል ነፍስ ወሥጋ ኅቡረ ውስተ እሳተ ገሃነም ብሎ ያጸ
ናቸዋልና ፡፡ ተሠውሮ የመጣውን በድር እንደመመለስ
ተዓቀቡ እምሐሳውያን ነቢያት እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ
በአልባሰ አባግዕ ወእንተ ውስጦሙ ተኵላት መሰጥ
ብሎ ያጸናቸዋልና ፡፡ በላይ የመጣውን በላባ እንደመ
መለስ ስምዖን ስምዖንሁ ስኢለ ሰዓለ ሰይጣን የሐንፅክሙ
ወየሐንፍጽክሙ ከመ ኢለስ ወአንሰ ሰአልኩ በእንቲአ
ክሙ ኢይድክም ሃይማኖትክሙ አንተኒ ተመይጠከ ጸን
አሙ ለአኃዊከ ብሎ ያጸናቸዋልና ፡፡

ውእቱ ኖላዊ ፡፡

በጎ ጠባቂያችን እሱ ነው ፡፡

ኖኅት አንቀጽ ፤

በር አማጋ ፡፡ በግን ከዱር ያውሉታል ማታ ሰብስ
በው ከአማጋ ያሰፍሩታል ከአማጋ በበር አድርገው

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ጋጥ ያገቡታል ። ከዱር እንደ መሰብሰብ ሐዋርያት ምእመናንን ከሕዝብ ከአሕዛብ ከሀገር ከሀገሪት ከሐቃል ከሮቢት ሰብስበዋቸዋል በአማጋ እንደማስፈር አሳምነ ዋቸዋል በበር አድርጎ ወደ ጋጥ እንደ መግባት ወንጌ ልን አስተምረው አጥምቀው ለሥጋው ለደሙ አብቅ ተው ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገቧቸዋል ለዚህ ሁሉ መደበኛ እሱ ነውና ።

ፍኖተ ሕይወት ፤

የሕይወት ጐዳና ። የሞት ጐዳና አለና ከዚያ ሲለይነው።

ፈውስ ሲሳይ ፤

ሥጋው አዳኝ ምግብ ነው ።

መስቴ መኰንን ፤

ደሙ ግን ፈራጅ መጠጥ ነው ። አሁን ደሙ ብቻ የሚፈርድ ሥጋው የማይፈርድ ሁኖ አይደለም ። በአክብ ርዎ ፍርሀዎ በፍርሀዎ አክብርዎ እንዳለ ። ሁሉም በሁሉ አለ ። ሥጋውም ይፈርዳል ደሙም ይፈርዳል ። እንዲፈር ድስ ለማጠየቅ መንሱትኬ በሊዓ ሥጋሁ በድፍረት ወተመጥዎተ ደሙ ዘእንበለ ኃፍረት ወለእመ ኢያእመረ ሥጋ እግዚእነ ኢኮነ ንጹሐ ነፍሱ በልዓ ደይናe ወመቅ ሰፍቶ ለርእሱ ይላል ። አንድም መስቴ መኰንን ብሎ ያነብ በዋል የፈራጅ መጠጥ ሲል ነው ። ጌታ ጽምዓ ነፍስ ይለ ፍላቸው ብሎ ይሰጣቸዋልና ። አንድም ቄሱ ቅድሳት ለቅዱሳን ብሎ ይሰጣቸዋልና ። አንድም ሰውየው በቅቻ ለሁ ልቀበል ብሎ ተፈርዶ ይቀበለዋልና ።



፪

፰/ ነአምን ሕማሞ ለዘኢየሐምም ።

እስካሁን ድረስ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር እየተ ናገረ መጥቶ ነበር ። ዘቅድመ ሀሎ ብሎ ምሥጢረ ሥላሴን ፤ ዘመጽአ ብሎ ምሥጢረ ሥጋዌን ፤ ሕጽበተ መድኃኒት ብሎ ምሥጢር ጥምቀትን ፤ ፈውስ ሲሳይ ብሎ ምሥጢረ ቍርባንን ፤ ወተንሥአ ብሎ ምሥጢረ ትንሣኤን ፤ ከዚህም በኋላ ይህንን እየመላለሰ ይሔዳል እንጂ ሌላ ነገር እያገ ባበትም ፤ ነአምን ሕማሞ ለዘኢየሐምም ፤ በአምላክነቱ የማይታመም በሰውነቱ የታመመ የሱን ሕማሙን እና ምናለን ።

ዘተወልደ በሥጋ ዘኢይትወለድ ።

በአምላክነቱ የማይወለድ በሰውነቱ የተወለደ የሱን ሕማሙን እናምናለን ፤ በሰውነት እንጂ በአምላክነቱ አት ወልደውምና ። አኮ ወልደ ማርያም በመለኮቱ ዘእንበለ ዳዕሙ በትስብእቱ እንዲል ። አንድም ከአምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን አስቀድሞ ያልተወለደ አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም የተወለደ ፤ አይሁድ ካይላ ፈላሻ እንደ ገና ይወርዳል ይወለዳል የሚሉት እን ግዲህ ወዲህ የማይወርድ የማይወለድ እስላም ተንባ ላት አላህ አንድ ነው አይወርድም አይወለድም የሚሉት

www.ethiopianorthodox.org

አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም መጥቶ የተወለደ የሱን ሕማሙን እናምናለን ።

መዊቶ ሕያው ወልደ አብ ፤

የአብ የባሕርይ ልጅ ሙቶ ሳለ ሕያው ነው አንድም መዊቶ ሐይወ ፤ ሙቶ ተነሣ ።

ተገምረ ዘኢይትገመር ፤

የማይታመመው ታመመ ትላለህ ይህ እንደምን ይሆናል ትለኝ እንደሆነ የማይወሰነው እንጂ ተወሰነ ፤ የማይወሰነው ከተወሰነ የማይታመመውም ታመመ በል ።

ዘኃጢአተነ ነሥአ እንዘ አልቦ ኃጢአት ።

በባሕርዩ ኃጢአት ሳይኖርበት የኛን ኃጢአት የተቀበለ ነው ። ተኖለቈ ምስለ ጊጉያን እንዲል አንድም ፍዳ ኃጢአታችንን የተቀበለ ነው ወበእንተ ኃጢአተ ሕዝብየ በጽሐ እስከ ለሞት ወበእንተ ዘተወፈየ ትእዛዘ ሕዝብ እንዲል ።

መዊቶ ሐይወ ።

ሙቶ ተነሣ ፤ አንድም መዊቶ ሕያው ሙቶ ሳለ ሕያው ነው ።

፱/ እምሰማያት እምኀበ አብ አይኀዓ ፤

በጌትነት ካለ ከአብ ወደዚህ ዓለም መጣ ፤ አንድም ከሰማያት ከአብ ወደዚህ ዓለም መጣ ፤ አንድም እምሰማያትና እምኀበ አብ አንድ ወገን ከአብ አንድነት ወደዚህ ዓለም መጣ አለ ። ከልዕልና ወደ ትሕትና ከምልዓት ወደ



መወሰን ከርቀት ወደ ግዘፍ መጣ ተወለደ ሲል ነው ። ተወለደ ሲል ተሰብአ ተሰገወ ወረደ አይኀዓ ይለዋል ።

በሕማማተ ሥጋሁ ቤዘወነ ።

መጥቶ በሰውነቱ መከራ ተቀብሎ አዳነን ።

ወደሞ ክቡረ መንፈሰ ሕይወት ።

ሕይወተ መንፈስ ሲል ነው ።

ወቅድሳተ መንፈስ ወሀበነ ።

የነፍስ ክብር የነፍስ ሕይወት የሚሆን ክቡር ደሙንም ሰጠን ፤ አንድም በእልመስጦአግያ ወመንፈስ ቅድሳት ብሎ ያነበዋልና ብሎ ሀብተ ንጽሕ ሀብተ ክብር የሚሆን ሥጋውንም ሰጠን ።

ወማየ መንጽሔ ዚአነ ።

ማየ መቍረርንም ሰጠን ይህንንስ ከመ ኢይንጥብ እምአፍ ይለዋልና ብሎ ማየ ገቦን ሰጠን ።

፲/ ዘያበርህ ውስተ አልባቢሆሙ ለእለ ይፈርህዎ ፤

በሥጋቸው ይቀስፈናል በነፍሳቸው ያጠፋናል ብለው ፈርተው በሚያመልኩት አድሮ ዕውቀት የሚገልጽላቸው እሱ ነው ። ሶበ አኮ በፍርሃተ ይስሐቅ እንዲል ።

እስመ ምስሌሆሙ ለዝላፉ ሀሎ ።

ለዘለዓለሙ ፈጽሞ አድሮባቸው ይኖራልና ዝንቱ ፀሐይ ዘበእንቲአሁ ይቤ አሞንዮስ ለባሴ አምላክ ለቅዱ

www.ethiopianorthodox.org

ሳን ቦሙ አሐዱ ጥሪት መዓልተ ወሌሊተ ከመ ዚአሆሙ እንዲል ፤

ዘረሰየነ ነኪራነ እምኵሉ ፍኖተ ሰይጣን ።

ከሰይጣን ሥራ ልዩ ያደረገን እሱ ነው ለሰይጣን ምን ጐዳና አለውና እንዲህ አለ ቢሉ እሱ የሚኖርበት ክህደት ፤ ሰውን የሚወስድበት ኃጢአት ነውና ። አንድም ከሁሉስ ምን አጥቶለት እሱም በኃጢአት በክህደት ይኖራል ሰውንም ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ይወስዳል በምን ዐውቆ ቢሉ ቁራኝነት ሲቀር አይቶ

ሐዳፌ ነፍሳት ፤

የነፍሳት መምህራቸው እሱ ነው ። እለሰ አልቦሙ ሐዳፍ ይወድቁ ከመ ቈፅል ፤ ዘሰ አጥረየ ሐዳፈ የአምር ምሳሌ ወሥውረ ነገረ እንዲል ። አንድም በመስቀል ትር ክዛው ባሕረ ገሃነምን እየቀዘፈ ነፍሳትን የሚያሻግር እሱ ነው ። ንዑ ነሐድፍ እንዲል ። አንድም አምስት ሽህ ከአምስት መቶ ዘመን በዝገተ ነፍስ የነበሩትን ነፍሳት የሚያድሳቸው እሱ ነው ። ሐድፌዮ እንዲል ትግሬ ። ሐዳሴ ነፍሳት የሚል አብነት ይገኛል ትርጓሜው አይለወጥም ።

ዘቦቱ ኵልነ ንትዌከል ዘንተ አምላከ ።

አብን የምናምንበት እሱ ነው ። አንድም ዝንቱ አምላክ ብሎ ይህ የምናምንበት አምላክ ነው ፤ አንድም የምናምንበት አምላክ ይህ ነው ።



ከዊኖ እምቅድመ ዓለም ምስለ አብ ።

ዘሀሎ ሲል ነው ቅድመ ዓለም ከአብ ጋራ ባንድነት ሳለ ።

ርእዮ ለዓለም በማዕሠረ ኃጢአት እንዘ ይትኃጐል ።

ሰው በኃጢአት ፍዳ ተይዞ ሲጎዳ አይቶት ።

በኃይለ ጥበቡ አርዌ ይትከየድ ።

በጥበቡ ባመጣው ግብር አርዌ ዲያብሎስ ድል ይነሣ ዘንድ ።

በኢያእምሮ ጌጋይ ለሞት ተቀንየ ።

ኃጢአት ሳይሠራ ሞቶ ። አንድም ቅድመ ዓለም ከአብ ጋር ባንድነት ሳለ ዓለም በኃጢአት ፍዳ ተይዞ እንደተጐዳ ዐውቆ አርዌ ዲያብሎስም በጥበቡ ባመጣው ግብር ድል እንዲነሣ ዐውቆ ኃጢአት ሳይሠራ ሞተ ። ወበ እንተ ኃጢአተ ሕዝብየ በጽሐ እስከ ለሞት እንዲል ።

፲፩/ ፈቂዶ ይፈውስ ትገዝምደ ሰብእ ።

ባሕርየ ሰብእን ነገደ ሰብእን ሊያድን ወዶ

ተገምረ በማኅፀነ ድንግል ተኃቢኦ ለኵሉ ኃይል እለ በሰማያት ማኅደር ፤

ማኅደራት ባለ በቀና ነበር ። መጽሐፍ ምሥጢር ይጠነቅቃል እንጂ አንድና ብዙ ሴትና ወንድ ሩቅና ቅርብ አይጠነቅቅምና እንዲህ አለ በሰማያዊ ቤቱ ካሉ መላእክት ተሠውሮ በድንግል ማኅፀን ተወሰነ ። ወአልቦ ለዘአእመረ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ምሥጢረ

www.ethiopianorthodox.org

ምጽአቱ ለቃል መልአክኒ ኢያእመረ ዕለተ ትስብእቱ ለቃል እንዲል ምነው እስከ ምጽንዓት ሐምስ ሚካኤል ተለውኮ እንዲል በአምሳለ ሊቀ ካህናት እስከ አምስተ ኛው ሰማይ ተከትሎት ሔደ ይል የለም ቢሉ ። የደረሰ በትን ስላላወቀ ነው ።

ወለእለ ይትቃወማ ኃይል በኢያእምሮ ሠወሮሙ ።

ሥልጣኑን የሚቃወሙ አጋንንትንም ባለማወቅ ሠወ ራቸው ። ዐውቀው ቢሆን የሰውን ሁሉ ጽንስ ያውኩ ነበርና ። አንድም ለእለ ይቀውማ ሲል ነው ። በቅዳሴ ጸንተው የሚኖሩ መላእክትንም ባለማወቅ ሠወራቸው ። ተከፍለው ያላወቁ አሉና ።

ሥጋ ለብሰ ዘይማስን ወዘኢይማስን ።

ዘይማስን ሥጋን ዘኢይማስን ነፍስን ተዋሐደ አንድም ዘኢይማስን መለኮት ዘይማስን ሥጋን ተዋሐደ ። አንድም ዘይማስን ዘኢይማስን ሥጋን ተዋሐደ ። ሐተታ በቀደመ ግብሩ ዘይማስን በኋላ ግብሩ ዘኢይማስን አለው ።

ለሥጋ መዋቲ ረሰዮ ዘኢይማስን ፤

የመዋቲ ያዳም ሥጋን ። አንድም መዋቲ ሥጋን የማይሞት አደረገው ።

ዘበአርዓያ ሥጋ ዘመዋቲ አዳም ።

የመዋቲ አዳም በሆነ ሥጋ ባሕርይ ያለ ሞትን የሚሞት ሥጋን የማይሞት አደረገው ። አንድም ለሥጋ መዋቲ ረሰዮ ዘኢይማስን ። የሚለወጥ አዳም ሥጋን አን



ድም የሚለወጥ ሥጋን የማይለወጥ አደረገው አንድም ዘበአርዓያ ሥጋ ዘመዋቲ አዳም የሚለወጥ አዳም በሆነ ሥጋ ባሕርይ ያለ መለወጥን የሚለወጥ ሥጋን የማይለ ወጥ አደረገው ።

አርዓያ ዘኢይማስን ዘቦቱ በአርዓያ ዘይማስን ተነሥተ።

የማይለወጥ ባሕርይ ያለው መለኮት መለወጥ ባለው ባሕርይ ሞተ ። ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ እንዲል ። አንድም የማይለወጥ ባሕርይ ያለው ዲያብሎስ መለወጥ ባለው ባሕርይ ድል ተነሣ ። ወነሰቶሙ ለኃያላን እምና ብርቲሆሙ እንዲል ።

፲፫/ ወትእዛዛተ ጽድቅ በወንጌል መጠወ ።

፲፫/ ደገኛውን ትእዛዝ በወንጌል ሰጠ ። ደቂቅየ ተፋ ቀሩ በበይናቲክሙ ብሎ አንድም ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን ዘበለዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ብሎ ፤ አንድም ጽንዑ እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም ብሎ እንደበጎ ባላገር ፤ በጎ ባላገር መዲውን አይቶ በዚህ ግቡ ይላል ጌታም ድል ነሥቶ ድል ንሡ አለ

ዘውእቱ ጸዋዒ ።

ጌታ ቢሉ ወደ ወንጌል ፤ ወንጌል ቢሉ ወደ ጌታ ጠርቶ የሚያደርስ ።

ዘበመንግሥት ንሕየው ተምሂረነ ።

በወንጌል ያለውን ተምረን በወንጌል ጸንተን እን ኖር ዘንድ አንድም ዘተምሂረነ ንሕየው በመንግሥት

www.ethiopianorthodox.org

ወንጌልን ተምረን በመንግሥቱ ሰማያት ጸንተን እንኖር ዘንድ ፤

ወበውእቱ ወንጌል ማእሠረ ሰይጣን ተበትከ ፤

በዚኸውም ወንጌል የሰይጣን ቁራኝነት ጠፋ ተነድገ ለከ ኃጢአተከ ፤ ተነደገ ለኪ ኃጢአተኪ ፤ ሁር ሃይማኖትከ አሕየወተከ እያለ ።

ከመ እሞት ሕይወተ ንትካፈል ወእምነ ኢያእምሮ ልቡና ንንሣእ ።

ከሞት ወጥተን ሕይወትን እንታደል ዘንድ ከድንቁርና ወጥተን ዕውቀትን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ዳግኛውን ትእዛዝ በወንጌል ሰጠ ። ውእቱሂ ማንሻ አንድም ከሞት ወጥተን ሕይወትን መታደላችን ከድንቁርና ወጥተን ዕውቀትን ገንዘብ ማድረጋችን ።

፲፬/ ውእቱሂ ከዊኖ ሰብአ ወልደ እግዚአብሔር አምላክ ዘተወልደ እምአዳም መዋቲ ።

፲፬/ ከመዋቲ አዳም የተወለደ ወልደ እግዚአብሔር አምላክ ሰው ቢሆን ነው ።

በአምሳሉ ተሰዊጦ ነሥአ ዘቀዳሚ ።

ንግበር ሰብአ በአርዓያነ ወበአምሳሊነ ያለውን ሥጋ ተዋሕዶ ጥንተ አምላክነቱን ገንዘብ አደረገ ተውህቦ ለእግዚአብሔር ቃል በሰብእናሁ ስም ዘበህላዌሁ ይሰመይ እንዲል ። አንድም በአዳም አምሳል ሥጋን ተዋ



ሕዶ ጥንተ አካልን ገንዘብ አደረገ ። ሕፃናት በሚጸነሱበት አካል እርሱ ባወቀ ነው ። ተሥዕለ በጥንተ አካል እንዘ ይትዋሐድ ቃል ምስለ ሥጋ እንዲል ። አንድም በዲያብሎስ አምሳል ሥጋን ተዋሕዶ ጥንተ ጥሪቱ አዳምን ገንዘብ አደረገ ሕሱም አርአያዬን ፤ ጸሊም ገጼን ገልጩ የሔድሁ እንደሆነ የማያውቅብኝ የለም ? ብሎ በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ መጥቶ አዳምን እንዳሳተው ፤ እርሱም ባሕርየ መለኮቱን ገልጩ የሔድሁማ እንደሆነ ያውቅብኛል ብሎ በሥጋ ብእሲ ተሠውሮ መጥቶ ዲያብሎስን ድል ነሥቶታልና ። ወበከመ ኮነ ተኃብዓ ሰይጣን ውስተ ሥጋ ከይሲ በጉሕሉቱ እስከ ተሠልጠ ወጸንዐ ላዕለ ፍጥረትነ እምቀዲሙ ከማሁ ኮነ ድኅነትን በተሠውሮተ ቃለ እግዚአብሔር ዲበ ዘመድነ እንዲል ።

ለተወልዶ ተጸንሰ ብእሴ ።

ሰው ሁኖ ለመወለድ ተጸነሰ ። እንደ ማድጋ ውኃ እንደ መስኖ ውኃ ገብቶ ወጣ የሚሉ መናፍቃን አሉና አንድም ለተወልዶ ተጸንሰ ብእሲ ብእሲ ጌታ ለመወለድ ተጸነሰ አጥንት ሁኖ ደም ሁኖ መቅረት አለና ።

፲፭/ ዘውእቱ አምላክ ዘበአማን ።

፲፭/ ብእሲ ብሎት ነበርና በስልት እንዳይሔድበት ዕሩቅ ብእሲ እንዳይልበት ብእሲም ያልኩት የባሕርይ አምላክ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ዘበነቢያት አቅደመ ተዓውቆ ።

የባሕርይ አምላክነቱን አስቀድሞ በነቢያት ያናገረ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ አኮሁ አንተ ትቤ እግዚኦ አመ ፈጠርካሃ ለምድር እዴየ ሣረረታ ለምድር ወየማንየ አጽንአቶ ለሰማይ ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገርየ አየኑ ቤተ ተሐንፁ ሊተ ለማኅደርየ ወአየኑ መካነ ለምዕራፍየ አኮኑ እደውየ ገብራ ዘኵሎ ብሎ ፤

ወበሐዋርያት ተሰብከ ።

የባሕርይ አምላክነቱን በሐዋርያት ያናገረ አንሰ እሜህረክሙ ከመ ታምልክዎ ለእግዚአብሔር ዘገብረ ዓለመ ወምድረ ወኵሎ ዘውስቴቶሙ እንዲል ።

ወእመላእክት ተአኰተ ።

የባሕርይ አምላክነቱን በመላእክት አስቀድሞ ያናገረ ። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ እንዲል ።

ወእምነበ ኵሉ ተሰብሐ ።

በሁሉ ዘንድ የተመሰገነ ። አንድም ወእምአበ ኵሉ ተሰብሐ ከሁሉ አባት ከአዳም ዘንድ የተመሰገነ ። አንድም ሥጋዌውን በነቢያት ያናገረ ፤ ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ፤ ወነገርነሂ ከመ ሕፃን ወከመ ሥርው ዘውስተ ምድር ጽምዕት ጽጌ አስተርአየ በውስተ ምድርነ እንዲል ። በሐዋርያትም ያናገረ ቃል ሥጋ ኮነ ተብሎ ፤ ውስተ ኵሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ እንዲል ። በመላእክትም ያናገረ



ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እንዲል ። ወእምኀበ ኵሉ ተሰብሐ ፤ ከሁሉ ዘንድ የተመሰገነ አንድም ወእምአበ ኵሉ ሁሉን በፈጠረ በአብ ዘንድ የታወቀ የተነገረ አንድም ወእምአብ ኵሎ ተሰብሐ ታይቶ መግዛትን ታይቶ መፍረድን ሁሉ ካባቱ ዘንድ ገንዘብ ያደረገ በሰውነቱ የሠራውን ሁሉ ተሰብሐ ይለዋል ወእንበይነ አቅመ ትስብእት ይትበሀል ከመ ውእቱ ተሰብሐ እንዲል ።

፫

፲፯/ ተሰቅለ በእንቲአነ ፤

፲፯/ ለኛ ብሎ ተሰቀለ ሐተታ ስቅለተ ሥጋ ነው ቢሉ እንደ ሁለት ወንበዴዎች ስቶ እንደ ሰማዕታት ዕሤት ሽቶ አይደለምና ለኛ ብሎ ተሰቀለ አለ ፤ ስቅለተ ሕሊና ነው ቢሉ የተመቸ ጥቅም ያለበት ነውና ።

ወበመስቀሉ ኮነ ሕይወትነ ጽንዕነ ቤዛነ ።

በመስቀሉ ጽንዕነ ቤዛነ ሲል ነው ጽንዓችን ቤዛችን በሚሆን በመስቀሉም በመሰቀሉ ሕይወታችን ተደረገልን አንድም ወጽንዕነ ቤዛነ ጽንዓችን ቤዛችንም ተደረገልን ።

ዘውእቱ ምሥጢር ኅቡዕ ፍሥሐ ዘኢይትዌዳዕ ዘቦቱ ።

ይኸውም የማይፈጸም ተድላ ደስታ ያለበት ረቂቅ ምሥጢር ነው ። መሌሊተ ሥጋ ሲሰቀል ሲቸነከር አይቶ

www.ethiopianorthodox.org

መሌሊተ መለኮት አብሮ ተሰቀለ ተቸነከረ ማለት ረቂቅ ምሥጢር ነውና ። አ አእዳው እለ ለሐኳሁ ለአዳም እፎ ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል ። አ እእጋር እለ አንሶስዋ ውስተ ገነት እፎ ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል እንዲል ። ስቅለተ ሕሊና ነው ቢሉ ኀቡዕ የተመቸ ፤

፲፯/ ዘሉ ነፍስ ፍትወተ ሰብእ ያርኅቅ እምእግዚአብሔር ኢይክል ።

ሰው ሁሉ ሥጋዊ ፈቃድ የሚሻ ሰውነቱን ከእግዚአብሔር ይለይ ። ቆርጦ ይጣል ማለት አይደለም ግብሩን ይተው ሲል ነው ። ይጽላእ ነፍሶ እንዲል ። አንድም ሰው ሁሉ ሥጋዊ ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ያርቅ ። ሥጋዊ ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ካላራቀ ፍሥሐ ዘኢይትዌዳዕ ዘቦቱ ያለውን ማግኘት አይቻለውምና ። አንድም ኢይክል ያርኅቆ ።

ኪያሃ እንዘ ትፀውር ወትረ ፤

ሰው ሁሉ እሷን ተዘክሮተ መስቀልን ይዞ ከተገኘ ሥጋዊ ፈቃዱ ከእግዚአብሔር ሊለየው አይቻለውም ። ካልሰረቀ ካልቀማ ድምበር ካላፈረሰ ቢያርስ ቢቆፍር ቢነግድ ለምግበ ሥጋ ታዟልና ።

ዛ ይእቲ ስብሐት ፤ ይህችውም ደግ ክብር ናት ። ፍቅር እምእግዚአብሔር ኢታሴስል ።

ሰውን ከእግዚአብሔር የማትለይ አንድም ኢታስስል እስዋ ከእግዚአብሔር የማትለይ ፍቅር ናት መሰቀሉን ማሰብ ተሰቃዩን ማሰብ ነው ።



፲፰/ ወበእላ ከናፍር ያታ ነገር ኢይትከሃል ጥንቁቀ ።

በሊህ ከናፍር ያምስቱን አዕማደ ምሥጢር ስልትስልታቸውን ለይቶ ጠንቅቆ መናገር አይቻልም አንድም ወበእላ ከናፍር ያታ ። መንታ በሚሆኑ በላይና በታች ባሉ በነዚህ ከናፍር አምስቱን አዕማደ ምሥጢር መናገር አይቻልም

ዘእምትካት ኅቡዓ ኮነ

ቀድሞ ረቂቅ ምሥጢር ነበረና

ይእዜሰ ክሡተ ምሥጢረ ኮነ ለምእመናን

ዛሬ ግን ለምእመናን የገላ የተረዳ ምሥጢር ሁኗልና ፤ ምንም ቢሆን ኢይትከሃል ጥንቁቀ

አኮ ከመ ይትረዓይ አላ ከመ ይትሐለይ ፤

ይእዜሰ ክሡተ ምሥጢረ ኮነ ፤ ለምእመናንም ብለን ብንል በዓይነ ሥጋ ሊታይ አይደለም ፤ በዓይነ ሕሊና ሊታሰብ ነው እንጂ ።

ውእቱ ዝንቱ መስቀል ።

ዛ ይእቲ ስብሐት ። ፍቅር እያለ ሲያጓድዳት መጥቶ ነበረና ይኸውም መስቀል ነው ብሎ ገለጸው ።

ወቦቱ ንትመካህ ከመ ንሰብሖ ።

እንሰግድለት ዘንድ የምናከብረው እናከብረው ዘንድ የምንመካበት መስቀል ነው ። በሁለቱ ወንበዶች

መሌሊተ መለኮት አብሮ ተሰቀለ ተቸነከረ ማለት ረቂቅ ምሥጢር ነውና ። አ አእዳው እለ ለሐኳሁ ለአዳም እፎ ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል ። አ እእጋር እለ አንሶስዋ ውስተ ገነት እፎ ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል እንዲል ። ስቅለተ ሕሊና ነው ቢሉ ጎቡዕ የተመቸ ፤

፲፯/ ኵሉ ነፍስ ፍትወተ ሰብእ ያርኅቅ እምእግዚ አብሔር ኢይክል ።

ሰው ሁሉ ሥጋዊ ፈቃድ የሚሻ ሰውነቱን ከእግ ዚአብሔር ይለይ ። ቆርጦ ይጣል ማለት አይደለም ግብ ሩን ይተው ሲል ነው ። ይጽላእ ነፍሶ እንዲል ። አንድም ሰው ሁሉ ሥጋዊ ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ያርቅ ። ሥጋዊ ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ካላራቀ ፍሥሐ ዘኢ ይትዌዳዕ ዘቦቱ ያለውን ማግኘት አይቻለውምና ። አን ድም ኢይክል ያርኅቆ ።

ኪያሃ እንዘ ትፀውር ወትረ ፤

ሰው ሁሉ እሷን ተዘክሮተ መስቀልን ይዞ ከተገኘ ሥጋዊ ፈቃዱ ከእግዚአብሔር ሊለየው አይቻለውም ። ካልሰረቀ ካልቀማ ድምበር ካላፈረሰ ቢያርስ ቢቆፍር ቢነግድ ለምግበ ሥጋ ታዟልና ።

ዛ ይእቲ ስብሐት ፤ ይህችውም ደግ ክብር ናት ። ፍቅር እምእግዚአብሔር ኢታሴስል ።

ሰውን ከእግዚአብሔር የማትለይ አንድም ኢታስ ስል እስዋ ከእግዚአብሔር የማትለይ ፍቅር ናት መስቀ ሉን ማሰብ ተሰቃዩን ማሰብ ነው ።



፲፰/ ወበእላ ከናፍር ያታ ነገር ኢይትከሃል ጥን ቁቀ ።

በሊህ ከናፍር ያምስቱን አዕማደ ምሥጢር ስልት ስልታቸውን ለይቶ ጠንቅቆ መናገር አይቻልም አን ድም ወበእላ ከናፍር ያታ ። መንታ በሚሆኑ በላይና በታች ባሉ በነዚህ ከናፍር አምስቱን አዕማደ ምሥጢር መናገር አይቻልም

ዘእምትካት ኅቡዓ ኮነ

ቀድሞ ረቂቅ ምሥጢር ነበረና

ይእዜሰ ክሡተ ምሥጢረ ኮነ ለምእመናን

ዛሬ ግን ለምእመናን የገሖላ የተረዳ ምሥጢር ሁኗ ልና ፤ ምንም ቢሆን ኢይትከሃል ጥንቁቀ

አኮ ከመ ይትረዓይ አላ ከመ ይትሐለይ ፤

ይእዜሰ ክሡተ ምሥጢረ ኮነ ፤ ለምእመናንም ብለን ብንል በዓይነ ሥጋ ሊታይ አይደለም ፤ በዓይነ ሕሊና ሊታሰብ ነው እንጂ ።

ውእቱ ዝንቱ መስቀል ።

ዛ ይእቲ ስብሐት ። ፍቅር እያለ ሲያጓድዳት መጥቶ ነበረና ይኸውም መስቀል ነው ብሎ ገለጸው ።

ወቦቱ ንትመካህ ከመ ንሰብሖ ።

እንሰግድለት ዘንድ የምናከብረው እናከብረው ዘንድ የምንመካበት መስቀል ነው ። በሁለቱ ወንበዶች

www.ethiopianorthodox.org

መሰቀል እንመካምና ፤ ጽድቅኑ በዘተላጸቀ ወበዘተቃረበ ይደሉት ከመ ይሰባሕ ስብሐተ እንተ ትደሉ ለእግዚአ ብሔር እንዲል ።

፲፱/ ወቦቱ እለ ይጠመቁ ምእመናን ፍጹማን ።

በዚህ መስቀል አምነው የሚጠመቁ ሰዎችም ምእመ ናን ፍጹማን ናቸው ። አንድም በዚህ መስቀል አምነው ተጠምቀው ምእመናን ፍጹማን የሚሆኑ ሰዎች ።

እምኵሉ ዘተነግረ ዘያስተርኢ ዘኢኮነ በአማን አድ ኃኑ ነፍሶሙ ፤

ዕዌሁ ዘኢይነውም ፤ እሳቱ ዘኢይጠፍዕ ተብሎ ከተ ነገረ ፤ የሚታይ ካይደለ ሁሉ በውነት ሰውነታቸውን አዳኑ ። አንድም በእልመስጦአግያ እምግባራት ኃላፊያት ይለዋልና ብሎ ዕዌሁ ዘኢይነውም እሳቱ ዘኢይጠፍዕ ተብሎ ከመነገሩ የተነሣ ዘያስተርኢ ዘኢኮነ በአማን ፤ በውነት ቀዋሚ ካይደለ ነገር ሁሉ ሰውነታቸውን አዳኑ አለ ከፍትወታት ከእኩያት ነው ።

፳/ በዝንቱ እለ ትጸንዑ ሒቱ ርእሰክሙ ፤

፳/ በዚህ መስቀል አምናችሁ ጸንታችሁ የምትኖሩ ሰዎች ሰውነታችሁን መርምሩ ።

አጽምሙ እዕዛኒክሙ ወእለ ይትረአያ አዑኑ አዕ ይንቲክሙ እለ በገሃድ ፤

ጆሮችሁንም ከመስማት ከልክሉ በአፍአ ያለ ዓይ ናችሁንም ከማየት ከልክሉ ፤ አሁን ዓይናችሁን አጥፉ



ጆሮቻችሁን አደንቁሩ ማለት አይደለም ሰምታችሁ አልሰማንም አይታችሁ አላየንም በሉ ሲል ነው እንጂ ። ዓይነ ሥጋ ካልታወረ ዓይነ ነፍስ አያይምና ዕዝነ ሥጋ ካልደነቆረ ዕዝነ ነፍስ አይሰማምና ። አንድም በአፍአ ያለ ጆሮቻችሁን ከመስማት ከልክሉ ወእለ ይትረዓያ አዑኑ የሚያይ ዓይናችሁንም ከማየት ከልክሉ ።

፳፩/ ከመ ታእምሩ ፈቃዶ ለኢየሱስ ክርስቶስ ።

፳፩/ የኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱ ወንጌልን ታውቁ ዘንድ ።

ወኵሎ ምሥጢረ መድኃኒትክሙ ።

ድኅነታችሁን የምታገኙበት አምስቱ አዕማደ ምሥ ጢርንም ታውቁ ዘንድ ። አንድም ፈቃደ ነፍሳችሁን ታውቁ ዘንድ ፤ ወኵሎ ምሥጢረ መድኃኒትክሙ ፤ ከጽ ማዊ እስከ ከዊነ እሳትም ያለውን ሀብት ታውቁ ዘንድ። ሰው ፈቃደ ነፍስን ገንዘብ ያደረገ እንደሆነ ሁሉ ይገለ ጽለታልና ፤ ወእምከመ ረከበ ብእሲ አሐተ ፈቃደ እንተ ትተልዎ ለእግዚአብሔር አሜሃ ይትወሀቦ አእምሮ ምሥ ጢራት ወነጽሮ ኅቡዓት እንዲል ።

ብእሲ ወአንስት ቅዱሳት እለ ሀሎክሙ ውስተ ተመ ክሆ በእግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር አባታችን መንግሥተ ሰማያት ርስ ታችን ብላችሁ በመመካት ያላችሁ ንጹሓት ክቡራት የምትሆኑ ሴትም ወንድም አጽምሙ አዑኑ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፱/ ያጽምዕ ዘንተ ውስጡ ለሰብእ ።

፳፱/ የሰው ውስጣዊ አእምሮው አጽምሙ አዕዛኒ ክሙ አዑሩ አእይንቲክሙ የተባለውን ያስተውል ። አን ድም ያጽምእ ዘንተ ውስጡ ለሰብእ ፤ ንጹሓት ክቡ ራት የምትሆኑ እግዚአብሔር አባታችን መንግሥተ ሰማያት ርስታችን ብላችሁ በመመካት ያላችሁ ሴትም ወንድም የሰው ውስጣዊ አእምሮው የሚታነጽበትን ግብር ያዙ ።

ክርስቶስ ጸመደነ ለኀበ አቡሁ አቅረበነ ።

ክርስቶስ ጽምድ እንደ በሬ ቀንት እንደ ገበሬ አድ ርጎ በባለሟልነት ወደ አባቱ አቀረበን ።

መጺኦ እምድኅረ ሐመ ፤

አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ወደ ዚህ ዓለም መጥቶ በሰውነቱ መከራ ከተቀበለ በኋላ ።

ወሪዶ ውስተ ሲኦል ዘውእቱ ነፍሰ ምውታን ዔወወ ለሕይወት ።

ነፍሰ ምውታን ነፍሳተ ምውታን ይላል ። ወደ ሲኦ ልም ወርዶ የሙታንን ነፍስ ለሕይወት ከማረከ በኋላ አቅረበነ አንድም አቅርቦናልና አጽምዑ ። ወመጺኦ እምድኅረ ሐመ ወደዚህም ዓለም መጥቶ በሰውነቱ መከራ ከተቀበለ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ የሙታንን ነፍስ ለሕይወት የማረከ ነው ። የነ ናቡከደነፆር የነ ስል ምናሶር ምርኮ የሞት ምርኮ አለና ከዚያ ሲለይ ።



፬

፴/ ርእየ ሞት እንዘ ይወርድ በሥጋ

፴/ እስከ አሁን ያዩ ያላዩ የሰሙ ያልሰሙ የነ በሩ ያልነበሩ ያወቁ ያላወቁ አሉና ያዩ ላላዩ የሰሙ ላልሰሙ የነበሩ ላልነበሩ ያወቁ ላላወቁ ነግረዋቸዋል ። ከዚህ በኋላ ግን ጌታና ዲያብሎስ የተነጋገሩት ነውና እሱ ባወቀ ያመጣዋል ፤ ዲያብሎስን ነው ፤ በግብሩ ሞት ብሎታል በአካለ ሥጋ ወደ ሲኦል ሲወርድ አይቶ ጌገዮ ፤ ሳተው ።

ወአምሰሎ ወቦቱ በከመ ያለምድ ውሂጠ ።

ቁራኝነትን ያስለመደበት ዕሩቅ ብእሲንም አስመ ሰለው ። ወደ ሲኦልማ የወረደ በአካለ ነፍስ አይደለምን ቢሉ ነፍስን በሥጋ ሥጋን በነፍስ መጥራት ልማድ ነውና ። ኢትቅትል ነፍሰ እንዲል ፤ አብረው ካሉስ ይሁን ከተለያዩ በኋላስ ቢሉ በለመደው ጠራው ። አንድም በሥጋ ተዋርዶ አፉን ለምረረ ሐሞት እጁን እግሩን ለተሳለ ቀኖት ሲሰጥ አይቶት ሳተው ፤ ምን ይስተዋል ይስተውማ ዘንድ አሁን ስንኳን መኑ መኑ እያለ እንጂ ይቀባጥር የለ ? ፤ ብሎ ርእዮን ቅሉ ሰሚዖ ሲል ነው አጽ ንን ወልድየ ለርእየ ሕልመ አቡከ ወርእየ ሕልመ አቡሁ ገብአ ማቴሳላ ፤ ስምዒ ወለትየ ወርእዩ እንዲል ። በሥጋ ተዋርዶ በመልዕልተ መስቀል ሁኖ ኤሎሄ ኤሎሄ ሲል ሰምቶ ስሑት ነህ አለው ።

www.ethiopianorthodox.org

ዕሩቅ ብእሲንም አስመሰለው ወቦቱ ከመ ያለምድ ውሂጠ ቁራኝነትን በሌላ እንዳስለመደ በሱም ላድርግ አለ ፤ ቃጣው ።

ርእየ በላዕሌሁ ስነ መለኮቱ ጸርሐ በቃል ዓቢይ ። በበላዩ ያለ ባሕርየ መለኮቱን አይቶ አሰምቶ ተናገረ ። ወቀፈጸ ምክዳኖ እንዲል ባሕርየ መለኮቱን ብልጭ አድርጎበታልና ። አንድም የጌትነቱ ጌጽ የሚሆኑ መላእክትን በመስቀሉ ዙርያ እንደ ሻሽ ተነጽፈው እንደ ቅጠል ረግፈው እንደ ግንድ ተረብርበው አይቶ አሰምቶ ተናገረ ። ወርኢኩ ኃይላተ ሰማያውያን ድኑናነ ወድንጉፃነ ዲበ ዓውደ መስቀል ቅዱስ ወስቡሕ እንዲል ።

እንዘ ይብል መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘእምሥልጣንየ ሰብአ ለቢሶ ሊተ ሞዓኒ ።

መኑ የአንክሮ ፤ የመመራመር ፤ የመጠራጠር ፤ አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን በኔ ሥልጣን ተይዞ የነበረ ሥጋን ተዋሕዶ እኔን ድል የነሣኝ ይህ ማነው ። አንድም ዘእምሥልጣንየ ሊተ ሞዓኒ ሥጋን ተዋሕዶ እኔን ከሹመቴ የሻረኝ ከልዕልናዬ ያዋረደኝ ይህ ማነው።

፳፬/ መኑ ዝንቱ ዘእምሥልጣንየ ተውህቦ ሥጋ ለኃጕል ይምሥጠኒ ፤

፳፬/ በግብሩ ኃጕል ብሎታል ኃጕል እኔን ያጠፋኝ ዘንድ ፤ አንድም እኔን ወደ ጥፋት ያደርሰኝ ዘንድ ፤ በኔ ሥልጣን ተይዞ የነበረ ሥጋ የተሰጠው ይህ ማነው ።



መኑ ዝንቱ ዘምድረ ለብሰ ።

ሥጋን የተዋሐደ ይህ ማነው ። መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት ያለው ለሁሉ ነውና ፤ እንዲያውም አዳምን በኩፋሌ እስመ ምድር አንተ ይለዋልና ።

ውእቱኬ ሰማያዊ ውእቱ ።

እሱስ ሰማያዊ ኑሮ እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ ። አንድም እሱማ አልቦ ዘዓርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ብሎ ነግሮኝ አልነበረም ? እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ ።

መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘበሙስና ተወልደ ።

መለወጥ ባለው ባሕርይ የተወለደ ይህ ማነው ።

ውእቱሰ ኢይማስን ።

እሱስ የማይለወጥ ኑሮ እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ ። አንድም እሱማ እስመ አነ እምላክ ዘኢይትዌለጥ ። እመቦ ዘዓቀበ ቃልየ ኢይጥዕም ለሞት ብሎ ነግሮኝ አልነበረም ? እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ ።

፳፭/ መኑ ዝንቱ ዘነኪር እምሕግየ ።

፳፭/ ከኔ ሕግ ልዩ የሚሆን ይህ ማነው ። ምን ሕግ አለውና እንዲህ አለ ቢሉ ጌታ አትሥሩ የሚለውን እሱ ሥሩ ። ጌታ ሥሩ የሚለውን እሱ አትሥሩ ይላልና ዘነኪር አለ በምን ዐውቆ ቢሉ ቁራኝነት ሲቀር አይቶ ።

መኑ ዝንቱ ዘእምዚአየ ይዔውው ።

ከኔ ወገን እየማረከ የሚወስድ ይህ ማነው ። እምዚአየ ብሎ በከፊል ተናገረ ። መምለክያነ ጣዖት አልወ

www.ethiopianorthodox.org

ጡምና ። ወኀደጎሙ ለእኩያን ህየ ውስተ ትውክልና ምስለ መላእክቲሆሙ እስከ ዕለተ ደይን እንዲል ።

መኑ ዝንቱ ዘበኃይለ ነደ እሳት ምስለ ሞት ይት በዓስ ።

ነደ እሳት በሚሆን ኃይል ከኔ ከሞት ጋራ የሚሰ ላለፍ ይህ ማነው ። አንድም ነደ እሳት ከምሆን ከኔ ከሞት ጋራ የሚሰለፍ ይህ ማነው ።

መኑ ዝንቱ ዘሞያ ለጽልመት ፤

በግብሩ ጽልመት ብሎታል እኔን ጽልመትን ድል የነሣኝ ይህ ማነው ።

መኑ ውእቱ ዝንቱ ስብሐት ሐዲስ ዘበአርአያዝ ተከልዓኒ ገቢር ዘእፈቅድ ።

ዘበርእየዝ ሲል ነው ። ወርኢኩ አርአያ ባሕቲትየ እንዲል ። እሱን በማየት እምወደው ሥራ የተከለከለብኝ ይህ እንግዳ ብርሃን ማነው ። ብርሃንስ የባሕርዩ ነው ፤ ስለ ሥጋ እንግድነት ነው እንጂ ፤ ከመ ይትአመን አም ላክ ሐዲስ በትስብእቱ እንዲል ። አንድም ዘእፈቅድ ገቢሮት በዚህ ባሕርይ ማድረጉን የምወደው ሥራ የተ ከለከለብኝ ይህ እንግዳ ብርሃን ማነው ።

፳፪/ መኑ ዝንቱ እንበለ ኃጢአት ዘሞተ ፤

፳፪/ ኃጢአት ሳይሠራ የሞተ ይህ ማነው ። ሐተታ በሐልዮ እንዳልሠራ ለማጠየቅ ይመጽእ መልአኩ ለዝ



ንቱ ዓለም ወኢይረክብ በላዕሌየ ብኋል ። በነቢብ እንዳ ልሠራ ለማጠየቅ ኢገብረ ኃጢአተ ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ። ብሎ ነቢይ መስክሮለታል ። በገቢር እንዳልሠራ ለማጠየቅ ። መኑ እምኔክሙ ዘይዛለፈኒ በእ ንተ ኃጢአት ብኋል ። ከዚህም ጠላቱ ዲያብሎስ እንዲህ ብሎ መሰከረለት ። ከሁሉም የሱ ይበልጣል አዎን ብሎ የተረታ ባለጋራ ከሥሩ የተነቀለ ወይራ እንዲሉ ። የጠ ላት ምስክር የታመነ ነውና እስመ ስምዐ ጸር እሙን ውእቱ እንዲል ፤

መኑ ዝንቱ ዘበብዝኀ ብርሃኑ ለጽልመት አያሮ ።

በብርሃኑ ብዛት በብዙ ብርሃኑ ጽልመትን ዕውር ያደረገው ይህ ማነው ፤ ለሲኦል ጨለማ ብርሃኑዋ ብርሃን ጨለማዋ ነውና ። አንድም ያጸናው ሲል ነው ከጨለማ ቦታ ፋና አብርቶ ገብቶ ፋናው በጠፋ ጊዜ ጨለማ እንዲ ጸና ጌታ ገብቶ ከወጣ ወዲህ ጨለማ ጸንቶባቸዋልና ።

ዘኢኃደገኒ ለእሊአየ እስፍን ።

ለወገኖቼ እሥለጥንላቸው ዘንድ ያልተወኝ ፤ አንድም በወገኖቼ እሠለጥን ዘንድ ያልተወኝ ይህ ማነው ።

አላ ዝሎ ለነበ ሰማያት ይስሕብ እለ ተውህባኒ ነፍሳተ ።

አላ ዝሎ ነፍሳተ እለ ተውህባኒ ለነበ ሰማያት ይስ ሕብ ሲል ነው ። አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን በኔ ሥልጣን ተይዘው የነበሩ ነፍሳትን በክብር በግብር ወደ ላይ ያወጣል እንጂ አንድም እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

እሱማ እምከመ ተለዓልኩ እምድር እስሕብ ኵሎ ኀቤየ ብሎ ነግሮኝ አልነበረም ? ።

፳፺/ መኑ ዝንቱ ስብሐት ዘይከልዕ ሥጋ ኢትማስን ፤

፳፺/ ሥጋ እንዳትፈርስ እንዳትበሰብስ የሚከለክል ይህ ብርሃን ማነው ።

መኑ ዝንቱ ዘለኪፎቶ ኢይክል ።

መንካቱ መዳሰሱ የማይቻለኝ ይህ ማነው ።

ምንትኑ ዝንቱ ዘየዓውዶ ስብሐት ዘኢይትአተትዝ

ዘኢየሐፅፅ ፤ ዝ ዘኢይነትግ ፤ ዝ ሲል ነው ። ከተሰጠ የማይነሣ ካደረ የማይለይ ብርሃን የከበበው ይህ ማነው ። የጌታ ተዋሕዶ የባሕርይ እንጂ የጸጋ ፤ የኩነት እንጂ የኀድረት አይደለምና ። እስመ ዘብዕለ እምዘ አልቦ ይነዲ ዘተውህበኒ ይሠዓር ወዘተረብሐኒ ይትኃጐል እንዲል ።

ተኃጐልኩ እምዝንቱ ፤

ከዚህ ብርሃን የተለየሁ ።

ወእምእሊአሁ ፤

ከወገኖቹ ከምእመናንም የተለየሁ ።

ዘአማስን በላዕሌሆሙ አልብየ ።

እንግዲህ ወዲህም ሠልጥኜ የምገዳው የለኝም አን ድም ተኃጐልኩ እምዝንቱ ። ወይኔ አይነኩ እነካ ብዬ በለልኩ ጠፋሁ ከሱ የተነሣ ።



ወእምእሊዓሁ ፤

ከወገኖቹ ከምእመናን እንግዲህ ሠልጥኜ የምገዳው የለኝም ።

፳፰/ ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰቅለ ።

፳፰/ እኔ አላውቅ ብዬ ነው እንጂ እሱስ እኔ ያሰ ቀልኩት ኢየሱስ ክርስቶስ ኑሮ ። የየካሽ መላሽ ሁኖ ይናገራል ። አንድም ጌታ ይመልሳል ምን ያስቀባጥርኻል ያሰቀልከኝ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ ይላል ። እንደ ጐበዝ ጐልማሳ የዘመዶቹን ጠላት ገድሎ ቤቱን አቃጥሎ ከብ ቱን ዘርፎ ሲሄድ በዱር በገደል ያሉ ሰዎች የሆነስ ሆነና ኧረ ማነህ ጠላታችንን እንወቅህ ይሉታል ፤ የነእገሌ የነእገሌን ደም እማላስቀር እኔ እገሌ ነኝ ። ሌላውን አትሙ ብሎ አዝምሮ ይሔዳል ። እንደዚህም ሁሉ ጌታም የአባቴ የአዳምን የናቴ የሔዋንን ፍዳ የማላስቀር በገዳም በሦስቱ አርእስተ ኃጣውዕ ግንባር ግንባርክን ብዬ ድል የነሣሁ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ ብሎ መልሶለታል ።

ዘቦቱ ጸጋማይ የማናየ ኮነ ።

በግራ የነበረ አዳም ወደ ቀኝ ያለፈበት ፤ አንድም ደካማ ሥጋው ኃያል መለኮት የሆነበት ፤ አንድም ደካማ ሰው ኃያል መልአክ የሆነበት ።

ወታሕታይ ከመ ዘላዕላይ ።

ወደታች ወርዶ የነበረ አዳም ወደላይ የወጣበት ፤ አንድም ትሑት ሥጋ ልዑል አምላክ የሆነበት ፤ አንድም ትሑት ሰው ክቡር መልአክ የሆነበት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወደኃራይ ከመ ዘቀዳማይ ።

ደኃራዊ ሥጋ ቀዳማዊ አምላክ የሆነበት ። ደኃራዊ ሰብእ ቀዳማዊ መልአክ የሆነበት ። ወንዑስ ከመ ዘዓቢይ የሚል አብነት ይገኛል ፤ ትርጓሜው አይለወጥም ።

፳

፳፱/ እሙታን ተንሢአ ሲአለ ከይዶ ።

፳፱/ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ በግብሩ ሲኦል ብሎ ታል ፤ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ ፤

በሞቱ ለሞት ደምሰሶ ።

በሞቱ ሞትን አጠፋው ፤ ከሙታን ተለይቶ የተነሣ እሁድ ዲያብሎስን ድል የነሣ ዓርብ ማታ ስለምን እን ዲህ አለ ቢሉ ። በመገለጫው ተናገረው ፤ ወአልቦ ዘይ ክል ብሂለ እግዚእነ ኢየሱስ ዘእንበለ ዘመንፈስ ቅዱስ ላዕሌሁ እንዲል ። አንድም ሲአለ ከይዶ እሙታን ተን ሢአ ሲል ነው ዲያብሎስን ድል ነሥቶ ከሙታን ተለ ይቶ ተነሥቶ በሞቱ ሞትን አጠፋው ።

እምድኅረ ተንሥአ በሣልስት ዕለት አእኰቶ ለአብ

ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ከተነሣ በኋላ አብን አመሰገነው ።

እንዘ ይብል ዘአምላክ ቃል ጥዕጡዕ ከመዝ ።

ያንተ ሞት የዓለሙ ሕይወት ያንተ ኀሣር የዓለሙ ክብር ይሁን ብሎ የተናገረበት የአምላክ ቃል እንዲህ የተከናወነ ነው ?



ብሎ ። አንድም ጥዕጡዕ ከመዝ አካላዊ ቃል አብን አመሰገነው በአካላዊ ቃልማ መመስገን እንጂ ምን ማመ ስገን አለበትና እንዲህ አለ ቢሉ ምሥጋናው በወዲህ ነው ። አንድም በወዲያኛው ቅሉ መመስጋገን አላቸውና ዛቲ ቃል ትኬልሀ ወትብል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እን ዲል ። ይኸማ መበላለጥ እንጂ ቢኖር ነው ቢሉ መበላለ ጥስ የለም እርስ በራሳቸው መተዋወቃቸውን መናገር ነው ።

፴/ አአኰተከ አብ ፤

አብ አመሰግንኻለሁ

አኮ በዝንቱ ከናፍር ውዱዳት ፤

እማመሰግንህ በሊህ ባጥንትና በጅማት በተሰማሙ ከናፍር አይደለም ።

ወአኮ በልሳነ ሥጋ ዘባቲ ጽድቅ ወሐሰት ይወጽእ ።

ሐሰትና እውነት በሚነገርባት በዚች ሥጋ አንደበት አይደለም ። እውነት ይናገራል እንጂ ሐሰት ይናገራልና እንዲህ አለ ቢሉ በሰው ልማድ ። አንድም ጽድቅን ሲሻ የመጣ ነው እወን ተከትሎ የመጣ አልቦ እወ ሁኖ እን ዲፈታ ፣ እስከ ማእዜኑ ተሐንክሱ በክልኤሆን ጌጋያቲክሙ እመኒ ቤል አምላክ ኪያሁ ትልው ወእመኒ እግዚአብሔር አምላክ ኪያሁ ትልው እንዲል ።

ወኢበዝ ቃል ዘበኪነ ነፍስት ግብር ይትገበር ።

በአእምሮ ጠባይዕ ሥራ በሚሠራበት በዚያ ቃልም አይደለም ። አንድም ግብረ ይገብር በአእምሮ



www.ethiopianorthodox.org

ጠባይዕ ሥራን በሚሠራ በዚያ ቃልም አይደለ ። አንድም ነፍስተ ግብር ይትገበር ሥራ ባለው አእምሮ ጠባይዕ ሥራ በሚሠራበት በዚያ ቃልም አይደለ ። አንድም ግብረ ይገብር ሥራ ባለው አእምሮ ጠባይዕ ሥራን በሚሠራ በዚያ ቃልም አይደለ ።

አንድም ዘበኪነ ነፍሳተ ግብር ይትገበር በሰዎች አእምሮ ሥራ በሚሠራበት በዚያ ቃልም አይደለ ዘበኪነ ነፍሳት ግብረ ይትገበር በሰዎች አእምሮ ሥራን በሚሠራበት በዚያ ቃልም አይደለ ። አንድም ነፍሳተ ግብር ይትገበር ሥራ ባላቸው ሰዎች አእምሮ ሥራ በሚሠራበት በዚያ ቃልም አይደለ ነፍሳተ ግብር ግብረ ይገብር ሥራ ባላቸው ሰዎች አእምሮ ሥራን በሚሠራ በዚያ ቃልም አይደለ ።

አላ በዝኩ ቃል ፤ አቆየው ።

፴፭/ አእኰተከ ንጉሥ ዘብከ ይትወቅ ለኵሉ ።

፴፮/ ንጉሥ ባንተ ህልው ሁኖ ለሁሉ በሚታወቅ በዚያ ቃል አመሰግንሃለሁ እንጂ አለ ለበቁ ።

ወእንተ ኢይትዓወቅ ፤

ላልበቁ ። አንድም ባንተ ሥልጣን ታድሶ ለሁሉ በሚታወቅ በዚያ ቃል አመሰግንኻለሁ እንጂ አለ ። ለመረመሩ ፤ ወእንተ ኢይትዓወቅ ላልመረመሩ ፤ ዘብከ ይትዓወቅ ለኵሉ ወእንተ ኢትትዐወቅ ባንተ ሁሉ የሚታወቅብህ አንተ የማትታወቅ ። ንጉሥ በዚያ ቃል አመሰግንሃለሁ



አንድም ዘብከ ትትዐወቅ ለኵሉ እንተ ኢትትዐወቅ የማትታወቅ መንግሥተ ሰማያት ባንተ ለሁሉ የምትታወቅብህ ንጉሥ በዚያ ቃል አመሰግንኻለሁ ።

ወእንተ ኢትመጽእ ውስተ መናፍስት ዘሥጋ ።

በዓይነ ሥጋ የማትታይ ።

፴፯/ ዘበዕዝነ ሥጋ ኢተኃልፍ ።

፴፰/ ወደ እዝነ ሥጋ የማትገባ ወኃለፈት ሰንበት እንዲል ፤

ወእንተ በዓለም ኢሀለወት ።

ይህነን ዓለም የማትመስል ።

ወበምድር ኢትትኃደግ ።

በዚህ ዓለም የማትገለጽ ።

አላ በዝኩ ቃል ዘበላዕሌነ መንፈስ ።

አላና አላ ዝኩና ዝኩ አንድ አንድ ወገን ነው ። በኛ ህልው ሁኖ ያለ መንፈስ ቅዱስ በገለጸው በዚያ ቃል ነው አለ ፤ ራሱን ከአብ አግብቶ ። አንድም በኛ አድሮ ያለ መንፈስ ቅዱስ ባደሰው በዚያ ቃል ነው አለ ፤ ራሱን ከምእመናን አግብቶ ። ይህስ ቃል የወዴት ቃል ነው ቢሉ ሕፃናት በማኅፀን ሁነው የሚያመሰግኑበት ቃል ጻድቃን ከበቁ በኋላ የሚያመሰግኑበት ቃል ፤ ነፍሳት በገነት ሁነው የሚያመሰግኑበት ቃል ፤ አዳም ሰባት ዓመት ምሉ በገነት ሳለ ያመሰግንበት የነበረ ቃል ፤ መላእክት

www.ethiopianorthodox.org

የሚያመሰግኑበት ቃል ነው ። አንድም እነሳቸው ባወቁ የሚመሰጋገኑበት ቃል ነው ።

ዘለከ ለባሕቲትከ ይትናገር አብ ።

ዘሊተ ለባሕቲትየ ትትናገር ሲል ነው ። አብ ለኔ ብቻ በምትናገርበት ገሃንቱ ውእቱ ወልድየ ብለህ ።

፴፫/ ዘኪያከ ያፈቅር አብ ።

፴፫/ ዘኪያየ ያፈቅር ሲል ነው እኔን ብቻ በምትወድበት ዘሠምረት ነፍስየ ብለህ ፤

ወዘኪያከ ይዌድስ ።

ኪያየ ትዌድስ ሲል ነው እኔን ብቻ በምታመሰግንበት ። ስባሕኩከሂ ወዓዲ እሴብሐከ ብለህ ።
ዘቦቱ ኵሉ ማኅበረ ቅዱሳን ፍጹማን ኪያከ ይጼውኡ አርከ ።

ኪያየ ሲል ነው ባንተ መምህርነት ባንተ ምስክርነት ማኅበረ ቅዱሳን ፍጹማን ሁሉ እኔን አርከ መሃይምናን ብለው በሚጠሩበት ።

ኪያከ አበ ፤

አብ ለዕጓለማውታ ፤

ኪያከ መጋቤ ፤

መጋቤ ኵሉ ።

ወኪያከ ረዳኤ ፤

ረዳኤ ኵሉ ብለው በሚጸሩበት ። አንድም እትናገር ሲል ነው እኔ ላንተ ለብቻህ በምናገርበት አቡየ ፈነወኒ ብዬ



ወዘኪያከ አፈቅር አንተን በምወድበት አንሰኬ አፈቅሮ ለአብ ብዬ ። ወዘኪያከ እዌድስ አንተን በማመሰግንበት ስባሕኩከሂ ፈጺምየ ግብረ ዘወሀብከኒ ብዬ ። ዘብየ

ማኅበረ ቅዱሳን ፍጹማን

ሁሉ በኔ መምህርነት ፤ በኔ አብነትነት ፤ አንተን አርከ መሃይመናን ብለው በሚጸሩበት አንድም በኛ ሀልውና ያለመንፈስ ቅዱስ ላንተ ብቻ በሚናገርበት አለ ። የሚያናግር ስለሆነ ልሳነ ዓለም ጳራቅሊጦስ ተራድአኒ ከመ እንብብ ዘውስተ ዓለምከ እንዲል ፤ ወዘኪያከ ያፈቅር የሚያስወድድ ስለሆነ ወዘኪያከ ይዌድስ የሚያስመሰግን ስለሆነ ፤ ዘቦቱ ኵሉ ማኅበረ ቅዱሳን ፍጹማን በርሱ ቃኝነት ማኅበረ ቅዱሳን ፤ ፍጹማን ሁሉ አንተን አርከ መሃይምናን አብ ለዕጓለ ማውታ መጋቤ ኵሉ ረዳኤ ኵሉ ብለው በሚጸሩበት በዚያ ቃል አመሰግንሃለሁ እንጂ ።

፴፬/ አምላከ ኵሉ ፤

፴፬/ የሁሉ አምላክ ነህ ።

እስመ ለከ ኵሉ ፤

ሁሉ ላንተ ይገዛልና

ወኵሉ ብከ ፤

ሁሉ ባንተ ተገኝቷልና

ዘሀሎ ለከ ፤

ያለው ፍጥረት ሁሉ አንተን ለማገልገል ነውና ፤

www.ethiopianorthodox.org

አልቦ ካልዕ ዘኢኮነ ዘዚአከ ፤

ያንተ ያይደለ ሌላ ልዩ ፍጥረት የለምና ። አንድም የሁሉ አምላክ ሁሉ ላንተ ይገዛልና ። ሁሉ ባንተ ተገኝቷልና ፤ ያለውም ፍጥረት ሁሉ አንተን ለማገልገል ነውና አልቦ ካልዕ ዘኢኮነ ዘዚአከ ።

ያንተ ያይደለ ሌላ ልዩ ፍጥረት የለም ።

ለባሕቲትከ ዘሀሎከ ለዓለመ ዓለም ።

ለብቻህ ለዘለዓለም ዋሕደ ባሕርይ ሁነህ የምትኖር።

፴፫/ ያእምር እንከ ኖላዊ ዘኵሉ ነፍሳተ ምሥጢር

፴፫/ የሁሉ መምህር ቄሱ ኤጲስ ቆጶሱ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር መማር የሚገባቸው ምእመናንን ይወቅ አንድም ዘነፍሳት ምሥጢረ ፤ ምእመናን ሊማሯቸው የሚገቡ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ይወቅ ፤ አንድም የአምስቱን አዕማደ ምሥጢር ስልት ስልታቸውን ለይቶ ይወቅ ።

እምድኅረ ጸለየ ለአብ ።

ዕቀቦሙ በስምከ ቀድሶሙ በጽድቅከ ብሎ ከጸለየ በኋላ ።

ከመ ታእምሩ ወትርአዩ አዓርግ ይቤ ኢየሱስ ።

ታውቁ ትረዱ ዘንድ ጌታ ወደ መስቀል እወጣለሁ ብሏልና ወደ መስቀል ሳልወጣ አልቀርም ብሏልና ወደ መስቀል ሳልወጣ አላርግም ብሏልና ወደመስቀል ከወጣሁ በኋላ ሳላርግ አልቀርም ብሏልና ።



፴፬/ ወበእንተዝ ይበል ኖላዊ መፍትው እንከ ነገረ ኅቡዓት ፤

፴፬/ ማወቅ የሚገባ ስለሆነ ፤ በሊቀ ካህናት እግር ስለተተካ ጌታ አብነት ስለሆነው ይንግር ይምሐር ቄሱ ኤጲስ ቆጶሱ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ያስተምር ዘንድ አገባብ ነው ።

ከመ ታእምሩ መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት ።

ሥጋውን ደሙን በመቀበል ጊዜ ማንንም ማንንም እንድትዘመዱ ታውቁ ዘንድ ። የማንን ሥጋ ተቀብላችሁ ከማን ጋራ ትዘመዳላችሁ ብሎ ይጠይቃቸዋል ። ያወቁ እንደሆነ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ተለይቶ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ባሕርያችንን ባሕርይ አካላችንን አካል አድርጎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ሰጥቶን ያነን ተቀብለን ከሦስቱ ጋራ አንድ እንሆናለን ብለው ይመልሳሉ ። ያላወቁ እንደሆነ እንዲህ ብሎ ሊነግራቸው ይገባልና ።

ወለመኑ ትገብሩ ተዝካሮ በአኰቴት ፤

በጸሎትም ጊዜ ማንንም ማንንም እንድትዘመዱ ታውቁ ዘንድ የማንን ስም ጠርታችሁ ማንን ትዘመዳላችሁ ብሎ ይጠይቃቸዋል ። ያወቁ እንደሆነ የሦስቱን ስም ጠርተን ከሦስቱ ጋራ እንዘመዳለን ብለው ይመልሳሉ ፤ ያላወቁ እንደሆነ እንዲህ ብሎ ሊነግራቸው ይገባልና ። አንድም ይበል መፍትው ነገረ ኅቡዓት ከመ ታእምሩ ። አምስቱን

www.ethiopianorthodox.org

ዕማደ ምሥጢር ታውቁ ዘንድ አገባብ ነው ይበላቸው ወይበል መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት ፤ ሥጋውን ደሙን በመቀበልም ጊዜ የማንን ሥጋ በልታችሁ ማንን ትዘመዳላችሁ ይበላቸው ። ሐተታ እንዳለፈው በጸሎትስ ጊዜ የማንን ስም ጠርታችሁ ማንን ትዘመዳላችሁ ይበላቸው ። ሐተታ እንዳለፈው ።

፴፯/ ወዓዲ ይንግር እንዘ ይብል ፤

፴፯/ ያቍራቦቹን ተናግሮ የቈራቦቹን አመጣ ይኸንንስ ወከመዝ ይበሎሙ ለግዩራን ብሎ በእልመስጠ አግያ ያነበዋልና ብሎ የሐዲስ አማኒ ሰዎችን አመጣ ። ዳግመኛም ከጣዖት ከሚርት ፈልሰው የመጡትን እንዲህ ይበላቸው ።

ንሕነሂ አኃውየ ቦቱ ንፀወን ።

ወንድሞቼ እኛም በሱ አምነን ጸንተን እንኑር ።

ዘባሕቲቱ ሀብተ ተምሂረነ ኪያሁ ንንሣዕ ።

የብቻው ስጦታ የምትሆን ወንጌልን ተምረን እሱን በሃይማኖት ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ።

፴፰/ ዘይቤ ከመ የሀበነ ።

፴፰/ ይሰጠን ዘንድ ያናገረ ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ብሎ ፤ ለሃይማኖት ቢቀጽሉ ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽአ አፍአ ብሎ ።



ዘዓይን ኢርእየ ወእዝነ ኢሰምዓ ፤

ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው ።

ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ ፤

በሰው ልቡና ያልታሰበ ።

ዘአስተዳለወ እግዚአብሔር ለእለ ያፈቅርዎ ።

እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀላቸው ምነው አይተውት የለም ቢሉ አይተው ስላላመኑበት ። አንድም የሚያወርሰው ክብር የማይመረመር ስለሆነ ፤ ለሃይማኖት ቢቀጽሉ የተመቸ ሃይማኖት ዋጋ ሲያሰጥ ነው እንጂ የሚያየው የለምና ። ምነው የኀድር ነምር ምስለ ጠሊ ወተኲላ ምስለ በግዕ ይል የለም ቢሉ ፤ ጊዜው ስለ አልታወቀ ነው ። አንድም የብቻው ስጦታ የምትሆን ሃይማኖት ተምረን ልጅነትን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ፤ ዘይቤ ከመ የሀበነ ይሰጠን ዘንድ ያናገረ እሰውጥ እምነ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ ብሎ ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው በሰው ልቡና ያልታሰበው ። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀላቸው ልጅነት ፤ ክብር ሲያሰጥ ነው እንጂ የሚያየው የለምና ። ምነው በአምሳለ ነፋስ በአምሳለ እሳት ለሐዋርያት ፤ በውኃ ምክንያት ለምእመናን ሲሰጥ ታይቶ የለም ፤ ቢሉ ጊዜው ስላልታወቀ ። አንድም ልጅነትን ገንዘብ አድርገን ሥጋውን ደሙን እንቀበል ዘንድ ፤ ዘይቤ ከመ የሀበነ ይሰጠን ዘንድ ያናገረ ዘበልዓ ሥጋየ ፤ ወሰትየ ደምየ ብሎ ዓይን ያላየው ፤ ጆሮ ያልሰማው ፤ በሰው

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ልቡና ያልታሰበው እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀላ
ቸው ። ሥጋው ፤ ደሙ ሲለወጥ የሚያየው የለምና ።ታሪክ
እንደ ሁለቱ አኃው ከበረሃ የሚኖሩ ናቸው ፤ አንዱ የበቃ
ነው ፤ አንዱ ያልበቃ ነው ፤ ያልበቃው ኅብስቱ
ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ
ወልደ እግዚአብሔር መሆን እንደምን ይቻላል እያለ
እየተጠራጠረ ይኖራል ፤ እንዳይናገር ይፈራል ። የበ
ቃው አውቆበታል ፤ ነገሩን ለመግለጽ ወንድሜ እኔንስ
የሥጋ የደሙ ነገር ረቅቆብኝ ይኖራል ። ኅብስቱ ተለውጦ
ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ
እግዚአብሔር መሆኑ እንደምን ይቻላል ብሎ ጠየቀው ።
ያልበቃውም አንተን ብፈራህ ነው እንጂ ፤ ይህስ እኔንም
ይልቅ ረቅቆብኝ ይኖራል ብሎ መለሰለት ። የበቃውም
እስኪ ከሚቀድሱበት ቤተ ክርስቲያን እንሂድ ብሎት
ተያይዘው ሔዱ ፤ ቆመው ሲያስቀድሱ ቄሱ ሀበነ ንኅ
በር ሲል በአምሳለ በግዕ ሲያርደው ሲያወራርደው አሥሩ
ጣቶቹ ሁሉ በደም ተነክረው አይቶ ያልበቃው ደንግጦ
ወድቋል ለሁሉ በሚቻል መታየቱ ነው እንጂ ዘወትር
እንዲህ እሆናለሁ ብሎ ድምፅ አሰምቶታልና ።

አንድም የብቻው ስጦታ የሚሆን ሥጋውን ደሙን
ተቀብለን መንግሥተ ሰማያትን እንወርስ ዘንድ ዘይቤ
ከመ የሀበነ ይሰጠን ዘንድ ያናገረ ፤ እንተ ኢትትዐወቅ
ዘእስተዳለወ ብሎ ዓይን ያላያት ፤ ጆሮ ያልሰማት በሰው
ልቡና ያልታሰበች እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት ፤



የሚያወርሰበትን ጊዜ የሚያውቅ የለምና ምነው እንዲህ
አለ ዘመኑ የሐንስ ወርኁ ወርኃ መጋቢት ዕለቱ ዕለተ
እሑድ ፤ ጊዜው መንፈቀ ሌሊት ነው ይሉ የለም ቢሉ
ብዙ ወርኃ መጋቢት ፤ ብዙ ዕለተ እሑድ ፤ ብዙ መን
ፈቀ ሌሊት አለና ።

፴፱/ በከመ ይቤ ሙሴ ።

፴፱/ ለሃይማኖት ይጠቅሳል ፤ ሙሴ ነቢየ ያነሥእ
ለክሙ እግዚአብሔር እምአኃዊክሙ ዘከማየ ወሎቱ ስም
ዕዎ እንዳለ ።

ባዕዳንሂ ነቢያት ።

ሌሎችም ነቢያት ጻድቅ አ በአሚን የሐዩ ወዘሉ ዘጸ
ውዐ ስመ እግዚአብሔር ይድኅን እንዳሉ ። አንድም ሁለ
ተኛ ለሃይማኖት ይጠቅሳል ፤ በተአምኖ ልሒቆ ሙሴ ክህደ
ከመ ኢይበልዎ ወልደ ወለተ ፈርዖን ወአብደረ ይሕምም
ምስለ ሕዝበ እግዚአብሔር እምይደለዉ ለሰዓት ወይኪውኖ
ኃጢአተ እስመ አእመረ ከመ የዐቢ ትዕይርተ መስቀሉ
ለክርስቶስ እምኵሉ መዛግብቲሆሙ ለግብፅ እንዲል ።
ሐተታ ይህንማ የተናገረው ሐዋርያው አይደለም ቢሉ ፤
እሱስ እንዲያውን ተናግሮታልን አ እግዚኦ ስምዖ ጽድቆ
ለሌዊ ዘይቤሎሙ ለአቡሁ ወለእሙ አንሰ ኢየአምረክሙ
ወበደቂቁኒ ኢለበወ ያለውን ይዞ እንጂ ነው ፤ ሌሎችም
ነቢያት ሠለስቱ ደቂቅ አ ንጉሥ ለምስል ዘወርቅ ዘገበ
ርከ ኢንሰግድ ለከ አላ ሀሎ አምላክነ ዘፈጠረ ኪያከ
ወኪያነ ወኪያሁ ናመልክ ንሕነ ወውእቱ ይክል አድኅኖ

www.ethiopianorthodox.org

ተነ እምእዴከ ወእምእቶነ እሳትሂ ዘይነድድ እንዳሉ ሃይማኖትን ገንዘብ እናድርግ ፤ ለሃይማኖት ጨርሶ ለልጅነት ይጠቅሳል ፤ በከመ ይቤ ሙሴ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ እንዳለ ሌሎችም ነቢያት እሠውጥ እምነ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ ወመንፈሰከ ቅዱሰ ኢታውጽእ እምላዕሌየ እንዳሉ ፤ ልጅነትን ገንዘብ እናድርግ ፤ ለልጅነት ጨርሶ ለሥጋው ለደሙ ይጠቅሳል ። በከመ ይቤ ሙሴ ወኅሩያኒሆሙ ለእስራኤል ዘአልቦ ዘይመስሎሙ አስተርአዩ በውእቱ መካን ይበልዑ ወይሰትዩ እንዳለ ሌሎችም ነቢያት ናሁ አስተዳለወ መሥዋዕቶ ወቀደሶሙ ለኅሩያኒሁ በምድር ገነተ ተድላ እንዳሉ ።

አንድም ሁለተኛ ለሥጋው ለደሙ ይጠቅሳል ። ሙሴ ፤ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ ወይእዜ የኀ ያሉ ዕል እዴሁ ወይነሥእ እምዕፀ ሕይወት ይበልዕ ወየሐዩ ለዓለም እንዳለ ። ሌሎችም ነቢያት ቀዳሚ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወማይ ወይን ወሥርናይ ለዘኢ.ይሰቲ ወይነ ምንትኑ ሕይወቱ እምፍሬ ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኃ እንዳሉ ። ሥጋውን ደሙን ገንዘብ እናድርግ ። አንድም ለሥጋው ለደሙ ጨርሶ ለመንግሥተ ሰማይ ይጠቅሳል ። በከመ ይቤ ሙሴ ወሰድኮሙ ወተከልኮሙ ውስተ ደብረ መቅደስከ እንዳለ ሌሎችም ነቢያት ሐነፀ መቅደሶ በአርያም በምድር ገነተ ተድላ እንዳሉ መንግሥተ ሰማያትን ገንዘብ እናድርግ ። አንድም የታ



ችኛውን ጨርሶ ለላይኛው ይጠቅሳል በከመ ይቤ ሙሴ ፤ ሙሴ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እንዳለ ሌሎችም ነቢያት ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም እንዳሉ ።

ንሕነኒ ቦቱ ተወኪለነ ሎቱ ነሀብ ስብሐተ ።

እኛም በሱ አምነን ጸንተን ለእሱ ምስጋና እናቅርብ፤ ዘሎቱ ስብሐት ወጽንዕ ለዓለመ ዓለም አሜን ፤ የዘለዓለም ጌትነት ከሃሊነት ላለው ለሱ ምስጋና እናቀርብ ።

ተፈጸመ ትርጓሜ ትምህርተ ኅቡዓት ወኪዳን በሰላም እግዚአብሔር አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org